# የዘመነ መሳፍንት ክስተት

በእናቱ በወለተ-ቤርሳቤህ (ዋቢ) በኩል ኦሮሞ የነበረውን አጼ ኢዮአስን ከገደሉ በኋላ ራስ ሚሕለ-ሚካኤል ሥሑል እሻንጉሊት ንጉሥ እንግሠው በቅርፅም ሆነ በይዘቱ ከዛሬው የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣን በጣም በሚበልጠው በ ‹‹ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት›› በጦርነት አስከሚባረሩ ድረስ አዛዥ ናዛዥ ሆነው ገዝተዋል፡፡ ዘውድ ያልደፉበት ምክንያት፣ ምንም እንኳ የአጼ ፋሲል ተወላጅ ቢሆኑም የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ቀጥተኛ ዝርያ ነኝ የሚሉበት ምንም ሰበብ ስላልነበራቸው ህዝቡን በመፍራታቸው ነው፡፡ የአጼ ኢዮአስን ሞት ተከትሎ የደረሰ ምንም ቀውስ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም "ባለ-ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆን ያለብኝ እኔ ነኝ" የሚል ማንኛውም ጉልበት ያለው መስፍን ሳልጋው ያስጋሉ ተብለው የሚታሰቡ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባላት ተግዘው/ታስረው/ ከሚጠበቁበት ከ"ወህኒ አምባ" እሥር ቤት አንዱን ልዑል ጎትቶ አምጥቶ ለስሙ ዘውድ ጭኖለት በዙፋኑ ላይ ያስቀምጠውና ራሱን "ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ" ብሎ የእውነተኛው ሥልጣን ባለቤት በመሆን ኢትዮጵያን ማዘዝና መግዛት የሚችልበት ወቅት ስለነበረ ነው፡፡

ንጉሥ ሹዋሚና እና ሻሪ የሆኑት እንደራሴዎቹ ራሳቸው ዘውድ ደፍተው፣ ዙፋን ላይ የማይቀመጡበት ምክንያት ሰፊው ሕዝብ "ዘውድ ነጣቂ" ብሎ ይቀጣናል ብለው ይፈሩ ስለነበረ ነው፡፡ በፊውዳሏ ኢትዮጵያ የተለመደው የወቅቱ ስልት እንደዚያ ነበር፡፡-- ከወህኒአምባ አንዳንድ አቅመ-ቢስ ልዑላንን ጎትተው አያመጡ እነሱን ለይስሙላ አልጋው ላይ አስቀምጠው መግዛት፡፡ የእያንዳንዱ መስፍን ምኞትና ተግባር የዘመኑ ፈሊጥ ይኸው ነበር፡፡

ከነዚህ ገናና መሳፍንት መካከል አንድ ቤተሰብ የሆኑ የየጁ ኦሮሞዎች ይገኙበታል፡፡ የሴሩ ጉዋንጉል ዝርያ የሆኑት እነዚህ የየጁ ኦሮሞዎች ከትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ ድረስ ያሉት፣ ካሳ ኃይሉ (ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ) ትንሹ ራስ ዓሊን ድል አድርገው ንጉሠ-ነገሥት ተብለው በ1847 ዓ.ም ዘውድ እስከ ደፉበት የትንሹ ራስ ዓሊ ዘመን ፍፃሜ ድረስ ‹‹ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ›› እየሆኑ በተከታታይ ኢትዮጵያን በከፊል የገዙ መሳፍንት ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን በከፊል ለ61 ዓመታት የገዙ 11 ‹‹ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴዎች›› አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ምንም እንኳ ሁለቱ የአማራ ስም ቢኖራቸውም ስምንቱ ኦሮሞዎች ናቸው፡፡ አንዱ ቀደም ሲል የተጠቀሱት የትግሬው ሚሕስ-ሚካኤል ሥሑል ሲሆኑ ሁለቱ ከላስታ ነበሩ፡፡ የሁሉም መሳፍንት ስም እንደ ቅደም ተከተላቸው ቀጥሎ ቀርቧል፤

ራስ ሚሕስ-ሚካኤል ሥሑል (ትግሬ)፤ ራስ ጎሹ (የቦረና ባላባት ኦሮሞ)፤ ራስ ዓሊና ራስ ዓሊጋዝ (ኦሮሞ)፤ ራስ ዓሥራት እና ራስ ወልደ-ገብርኤል (ላስታ አገው ወይም አማራ)፤ ራስ ጉግሳ ራስ ይማም (ኦሮሞ)፤ ራስ ማርዬ (ኦሮሞ)፤ ራስ ዶሪ (ኦሮሞ)፤ ራስ ዓሊ ትንሹ (ኦሮሞ)፡፡ ሁለቱ ላስታዎች አማራ ካልሆኑ ከነዚህ ገዢዎች መካከል አንድ እንኳ አማራ የለም ማለት ነው፡፡ አገውም እንዲሁ፡፡ ምንም እንኳ የየጁ ቤተ-ኦሮሞ የሆኑት የሴሩ ጓንጉል ልጆች የአረብ ስም ያላቸው ቢሆኑም ጥብቅ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን አባል ነበሩ፡፡ የአረብኛዎቹ ስሞቻቸው ያሳስታሉ፡፡ አንድ ሰው በአረብኛዎቹ ስሞች ተመርቶ ሰዎቹ ሙስሊሞች ናቸው ብሎ መደምደም የለበትም፡፡ አብያተ-ክርስቲያናትን የሚያስገነቡ፣ ገንዘባቸውንና ርስታቸውን ለቤተ-ክርስቲያናት የሚቸሩ ጥብቅ ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ ትንሹ ራስ ዓሊ ብቻ በዋና ከተማቸው በደብረ-ታቦር አምስት ቤተ-ክርስቲያኖችን አሠርተዋል፡፡ እነዚህ የኦሮሞ ዝርያ ያላቸው መሳፍንት ኦሮምኛን ቢያቀላጥፉም አማርኛ አጥርተው የሚናገሩ፣ በግዕዝ ፊደል የሚፅፉ፤ ለብዙሃኑ መግባቢያ የአንድ ብሔራዊ ቋንቋ አስፈላጊነት የገባቸው ብልሆች ሰዎች ነበሩ፡፡ አማርኛ ብዙ የተስራጨና ተወዳጅ መሆኑን በመረዳታቸው የመንግሥታቸው ቋንቋ አድርገውታል፡፡ ፍጹማዊ ሥልጣን ስለነበራቸው ኦሮምኛን ብህዝቡ ላይ መጫን ይችሉ ነበር፡፡ እነሱ ግን ያንን ማድረግ ጠቃሚ መስሎ ስላልታያቸው አማርኛን መንግሥታዊ ቋንቋ አደረጉት፡፡

ትግሬው አጼ ዮሐንስ ዐራተኛውም እንዲሁ ነበር ያደረጉት። ለንግግርም ሆነ ለጽሑፍ በአደባባይ በአማርኛ፣ በግላቸው ደግሞ በትግርኛ ይጠቀሙ ነበር። የወቅቱ ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ መንግሥትም አማርኛን የመሥሪያ ቋንቋው በማድረጉ፣ አጼ ዮሐንስ ዐራተኛ ያደረጉትን ነው እየተገበረ ያለው። የኢህአዴግ መንግሥት ለህልውናውና ለጥቅሙ ሲል እስካሁን ያደረገው ብልህነት ሲሆን ለወደፊቱም የሌሎች ነገዶች ቋንቋዎችን በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ በአብላጪው ህዝብ የሚነገረውን ኦሮምኛን ከአማርኛ ጎን ለጎን እንዲበለጽግ እሱም ሆነ እሱን የሚተካው መንግሥት ማበረታታት ይኖርበታል። የማይናቅ ጉልበት ስለነበረው ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ቢፈልግ ኖሮ ትግሪኛን ብሄራዊ ቋንቋ ለማድረግ ምንም የሚያግደው ኀይል ባልነበረም ነበር። ለቀለጠፈ አስተዳደር ነገሩ እንደማያዋጣ በብልህነት በመገንዘቡ እና የማያስፈልግ ቅዋሜንም ለመጋበዝ ስላልፈለገ ግን የተለመደውን እና አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚናገርበትን ከተወለደ ከ 3600 ዐመታት የማያንሰውን አማርኛን እንዲቀጥል አደረገ። ወደፊት የሚመጣውም መንግሥት ሥራውን ሊያቀላጥፍ የሚችለው ይህን ከአደረገ ብቻ ነው። አላይ እንዳልኩት እንደ ሁለተኛ የሥራ ቋንቋ ከአማርኛ ጎን ለጎን ቀስ በቀስ ኦሮምኛንም ማዳበር ይቻላል።

የተከበሩትን ታላቁን የኦሮሞ መሪ ትልቁ ራስ ዓሊን መሪው እንዲሆኑ ያጫቸው የጎንደር ሕዝብ ሲሆን የሳቸው ዘመድ የሆኑት እዛዥ ጉግሳም የተሾሙት በላስታው ራስ ወልደ-ገብርኤል ነበር። ትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ዛሬ ባለው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በሰፊው ሕዝብ መልካም ፈቃድ ሥልጣን የያዙ የመጀመሪያው መሪ ሳይሆኑ አይቀሩም። አጼ ተክለ-ጊዮርጊስ ለስሙ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት በነበሩበት ወቅት ከባድ ግብር በመጫንና ሌሎች በደሎችንም በማድረስ የጎንደርን ሕዝብ ያለ ርኅራኄ ጨቁነውት ነበር። እንደራሴያቸው ትልቁ ራስ ዓሊ ግን የጎንደር ሕዝብ በንጉሠ-ነገሥት ተክለ-ጊዮርጊስ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ እንዳች ለመወሰን ባደረገው ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተው የንጉሠ-ነገሥቱን ኢፍትሐዊነት ተቃውመው ለሕዝቡ ያላቸውን ድጋፍ ገለፁ። ሕዝቡም ሥልጣኑን ራሳቸው ወስደው እንዲታደጓቸው ትልቁ ራስ ዓሊን ተማፀናቸው። በዚህ የተነሳም ትልቁ ራስ ዓሊ «የጁ ሄጄ የታመሙ እናቴን ለመጠየቅ ፈቃድ ይሰጠኝ፣»





ብለው ንጉሠ-ነገሥቱን ለመኑ። ተፈቅዶላቸው ሄዱና ከየጁ በሺ የሚቆጠሩ ፈረሰኞችን አምጥተው ቤተ-መንግሥቱን አስከበቡና አጼ ተክለ-ጊዮርጊስን ከሥልጣን አወረዷቸው። ራስ ሚካኤል ሥሑል እንዳደረጉት አሻንጉሊት ንጉሥ እንግሠው ባለሙሉ-ሥልጣን እንደራሴ ሆኑና ከፊል ኢትዮጵያን ራሳቸው ማስተዳደር ጀመሩ። ይህም የኦሮሞ መሳፍንት ሥርወ-መንግሥት ጅማሮም ሆነ። ቢሆንም ኦሮሞ ያልሆኑት የሴት ዘመዳቸው፣ የከፋይ ሴሩ ጓንጉል ልጅ ራስ ጉግሳም በሴሎች ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነው ተሹመው ነበር። ራስ ወልደ-ገብርኤል በሚል ስም የተሾሙ ላስቴ ነበሩ። ራሱ ከገዛ ወንድማቸው ከራስ አሥራት ጋር ጦርነት ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እህታቸውን ወ/ሮ ሎሚትን ለእዛዥ ጉግሳ ዳሩና ተጠባባቂ ባለ-ሙሉ ሥልጣን እንደራሴያቸው አድርገው ሾሟቸው። ጦርነቱ በዚህ ቀረ።(23) እድል ከራስ ወልደ-ገበርኤል ወደ እዛዥ ጉግሳ ፊትዋን አዙራ ራስ እረፉ እና እዛዥ ጉግሳ ራስ ተብለው አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥቶችን በኢትዮጵያ ላይ እንደፈለጉ የሚሾሙ የሚሽሩ ኦሮሞ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆኑ።ቀድሞ እናቱ ኦሮሞ በነበረችው አፄ ኢዮአስ ላይ አብቅቶ የነበረው በሰለሞን ስርወ-መንግሥት ስም ኢትዮጵያን ያስተዳደረው የኦሮሞ አመራር፤ አዲስ ስልት ቀይሶ አሁን ደግሞ የኦሮሞ መሳፍንትን አስልጣን ማማ ላይ አስቀመጣቸው።

ኦሮሞዎች ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እየሆኑ በኢትዮጵያ ላይ ሲያዙ ኦሮሞ ያልሆኑት ባላባቶች ቀኑባቸው፣ ጠሏቸው፣ ከሥልጣን ሊያወርዷቸውም አሰቡ። ምንም እንኳ ያልተሳካ ቢሆንም አንዳንነዶቹ ጦርነት አነሱ። እርስ በርሳቸውም ለሥልጣንና ለግዛት መሬት ብለው ይዋጉ ጀመር፤ ሁሉም «ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ» መሆን አማራቸው። በባላንጣዎቹ ተጠላም ተወደደ የኦሮሞ መሳፍንት "ሥርወ-መንግሥት" ኢትዮጵያን ከ60 ዓመት በላይ በደንብ ገዝቷል። ለዚያ ስኬት ያበቃቸው ምስጢር ምንድነው? ምስጢሩ ሌላ ሳይሆን የነበራቸው ብልጠት እና ያስፈኑት መልካም አስተዳደር ነው። ብልጠታቸው ምንድነው? ያንዱን ግዛት ቆርሰው ለሌላው በመስጠት ታማኝ ከሆኑላቸው የበለጠ እንደሚለግቸው ቃል እየገቡ ተቀናቃኞቻቸውን እርስ በርሳቸው ማናከስ መቻላቸው ነው። ያስፈኑት መልካም አስተዳደርስ ምንድነው? የሚገዙትን ሕዝብ አለመጨቆናቸው፣ ዜጎቻቸውን ከጥቃት እየጠበቁ መንከባከባቸው፣

አብያተ-ክርስቲያናትን ማስራታቸው እና ለህዝቦቻቸው ደህንነት የሚያስቡ መሆናቸው ነው።

የሴሩ ጓንጉል ልጆች ሥርወ-መንግሥት በጎጃም፣ በጎንደር እና በትግራይ በሚገዛበት ወቅት ከነዚህ ክልሎች ውጪ በወሎ፣ በሸዋ እና በጊቤ ወንዝ ዙሪያ የነበሩ የኦሮሞ ባላባቶችና የጎሣ መሪዎች ግዛቶቻቸውን ለማስከበር እየታገሉ የየግል ኑሮአቸውን በመኖር ላይ ነበሩ። የሸዋ ኦሮሞዎች የተደራጀ የመንግሥት መዋቅር ስላልነበራቸው በእናቱ ከቱሉ በዴሳ ልጅ ከኦሮሞዋ ከንግሥት ናኦድ ሞገሳ ለሚወለደው ለአጼ ልብነ-ድንግል ልጅ ይገብሩ ነበር። አጼ ልብነ-ድንግል ከአህመድ ኢብራሂም መሓመድ ግራኝ ሸሽተው ወደ አማራ ሳይንት እና ወደ ትግራይ ከመሰደዳቸው በፊት አቤቶ ያቆብ የተባለ ልጅ ነበራቸው። በዘመነ-ግራኝ ነፍሱን ለማትረፍ ሌላ ሰው ተመስሎ በሸዋ ውስጥ ተደብቆ ይኖር ነበር። ወንድሙ አጼ ገላውዴዎስ አህመድ ግራኝን ድል ካደረጉ በኋላ ወደ ደንገዝ ሄዶ ከወንድሙ ከአጼ ገላውዲዎስ እና ከመደባይ/ኦሮሞ እናቱ ከንግሥት ሰብለ-ወንጌል ጋር ተገናኘ። ወንድሙ እና እናቱ አቤቶ ያቆብን ከፍ ባለ ሹመት ሾሙትና የመንግሥታቸው ተወካይ እንዲሆንላቸው መልሰው ወደ ሸዋ ላኩት። ሸዋ መጥቶ የንጉሥ ሣህለ-ሥላሴ፣ የሃይለ-መለኮት እና የዳግማዊ ምኒልክ ስሮች የሚሆኑ በርካታ ልጆችን ወለደ። እነዚህ ልጆችም ‹‹የኦሮሞይቱ የጊፍቲ መንዲያ እና የኦሮሞው ንጉሠ-ነገሥት የአጼ ልብነ-ድንግል ልጅ የአጼ ይኩኖ-አምላክ ዝርያ በመሆናችን ህዝባችንን መግዛት መብታችን ነው!›› እያሉ የሸዋን ኦሮሞ እና አማራ ገባራቸው አደረጉት። ዳግማዊ አጼ ምኒልክም ይህንኑ የኦሮሞ-ሰለሞናዊ አግአዚ ደም ካርድ መዘውና "የይሁዳ ነገድ" ነኝ ብለው ነው የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ለመሆን የበቁት። የሸዋ መሳፍንትና ነገሥታት ግን በራቸውን ጥርቅም አድርገው ዘግተው ለጎንደሩ መንግሥት ምንም ሳይገብሩ በፍጹም ነጻነት ነው የኖሩ።





# የንግሥተ-ሳባ ማንነትና ስለ መኖር አለመኖርዋ

ወላጅ እናትዋ አዝሚና "ኤትያኤል" ያለቻትን ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘችውን ንግሥተ-ሳባን በተመለከተ አንዳንድ ሰዎች ከናካቴው መፈጠርዋንም ይክዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ የአረቦች በተለይም የዛሬዋ የመን ንግሥት ያደርጓታል። አሁን ዋናው ጥያቄ ‹‹በርግጥ ንግሥተ-ሳባ በሕይወት ነበረች ወይ?›› ነው። አዎ! በርግጥ ነበረች። እንደ ሃይማኖት የለሽ አረመኔ የሚቆጥሯትን በአረቦች የተከለሰውን *ክብረ-ነገሥት* ንና አንዳንዶችንም የኢትዮጵያን ልዕልና የሚቀናቀኑ ዐረቦችን ፅሁፎች ቁምነገር ብለን ባንቀበላቸውም እንኳ ሌሎች አስተማማኝ ምንጮች ሊካዱ አይችሉም። በአንደኛው ክፍለ-ዘመን የነበረውን ጆሴፈስ የተባለውን አይሁድ-ሮማዊ የታሪክ ጸሐፊ እና መጽሐፍ ቅዱስንም ባናምን እንኳ በመግቢያዬ ላይ የተጠቀሰውን የልዑል አክሉማይ ሲራክ ሥራ የሆነውን "ታሪክ-ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ" የተሰኘውን መጽሐፍ ግን እምነት የጣልኩበት አስተማማኝ ምንጭ ስለሆነ የምጠቅሰው ይሆናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ እስከዛሬ ድረስ የሚመዘዘው የዘር ሐረጓ ለሕልውናዋ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊት ለመሆኗም የማያወላዳ ማስረጃ ነው።

ከ 2000 ዐመት በፊት የኖረው የአይሁድ ደም የነበረው ዝነኛው ባለታሪክ ፍላቪዮስ ጆሴፈስ በመጽሃፉ ውስጥ ንግሥት ሳባ ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ስላደረገችው ጉዞ መታሰቢያ አንድ ሙሉ ገጽ ጽፏል። የኢትዮጵያና የግብፅ ንግሥት እንደነበረች ባንዱ ገጽ ላይ

ሁለት ጊዜ ከትቦአል። (F. *Josephus, Jewish Antiquities*, ed. J. Thaceray and R. Marcus, Loeb Classical Library, London, 1961, Vol. VIII, pp. 165-175)። የሱ አፃፃፍ ከኦሪት ዘ ፍጥረት አፃፃፍ ጋር ይገጣጠማል (I Kings X: 1-10)። ኦሪት ዘ ፍጥረት ንግሥት-ሳባ ብሎ ይጠራታል። ከሺ ዓመታት በኋላ ጆሴፈስም የኢትዮጵያ እና የግብፅ ንግስት መሆንዋን አረጋግጦ አመልክቷል። ይህም ፍፁም እውነት ነው። ጌታ እየሱስ ክርስቶስም ቢሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ለ ሦስት ዓመታት ስለነበረ እና ከ ክብረነገሥት ፀሐፊም ሆነ ከፍላቪዮስ ጆሴፈስ በላይ ኢትዮጵያን ስለሚያውቅ "የእዝቦ ንግሥት" በማለት ማንነትዋን በትክክል ገልጧል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እየሱስ ክርስቶስ ለሕልውናዋ እውቅና መስጠት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊት መሆኗንም አረጋግጧል። በማያሻማ አባባል "የአዘቦ ንግሥት" ሲል ጠርቷታል። "አዜብ" የሚለው ቃል ከየት የመጣ ነው? ከንግሥት ሳባ ህልውና 900 ዓመት በፊት ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረ ንጉሥ ስም ነው። የዘር ሐረጉ እንደደሚከተለው ቀርቧል፤

የኢትዮጵያ መስራች እና ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥንተ-አባት የነበረው ቀዳማዊ ኢትዮጵ ከ4000 ዓመት በፊት ከጥንተ-እናታችን ከእንዮጳ-ግዮን አቲባን ወለደ።አቲባ ከንግሥት ቂቂ አዜብን ወለደ። አዜብ አዛል/አዳል/ ይባላልም። የአዜብ ዝርያዎች ከዐአመታት በኋላ "አዜብ" ወይም "አዘቦ"ይባሉ ጀመር። አዜብ ከአባይ መነሻ ጀምሮ እስከ ሶዳም ድረስ ለተዘረጋው ሰፊ አገር ንጉሥ ተብሎ ሲነግስ የነገሠበትን ሰፊ አገር "አዜብ" ብሎ ጠራው። ልጆቹ እና የልጅ ልጆቹ እዚህ እንዲኖሩም በሕግ ደነገገ። ንግሥተ ሳባ ወይም በትክክለኛው እናትዋ አዝሚና ባወጣችላት መጠሪያዋ ኢትያኤል በምትገዛበት ዘመን አዜቦዎች ወይም አዘበዎች ትልቅ ነገድ ነበሩ። ራሷ የወጣችው ከዚህ ነገድ ነበር። የሳባ ንግሥት ሆና እንኳ የአዜብ ንግሥትም ነበረች። ሳባ ከአያትዋ የወረሰችው ከተማ ነው። የአዘቦ ህዝቦች እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ለዚህ ነው እየሱስ ክርስቶስ ስለ ኢትያኤል ማንነት ርግጠኛ ሆኖ "ንግስተ-እዜብ" ሲል በትክክል የጠራት(ማቴ.12፡2፣ሉቃ.11፡31)። የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ቢጠቀሙ የተሻለ ነው። የእንግሊዝኛው ቅጂ "የደቡብ ንግሥት" ብሏታል። ከእብራይስጥ ወደ እንግሊዝኛ የመለሰው ተርጓሚ "እዜብ" የሚለውን ቃል የተረዳው "ደቡብ" በሚል ነው። በአማርኛ ወይም





በግዕዝም ታዲያ "አዜብ" የሚለው ቃል ከምዕራብ እስከ ደቡብ ያለውን ቦታ ለማመልከትም ይውላል። የስርወ ቃሉ ፍቺ ግን የአዘቦ ህዝቦችን፣ የንጉሥ አዜብን ዝርያ እና የንግሥት ሳባን ዘመዶች የሚያመለክት ነው። ኢትዮጵያ ከእስራኤል በስተደቡብ ስለምትገኝ ተርጓሚው ያንን መጥቀሱም ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ከላይ የቀረበው ገለጻ የኢትያኤልን ማንነት በተመለከተ በትክክል ያስቀመጠ ነው። እየሱስ "ንግስተ-ሳባ" ያላለበት ምክንያት በሱ ጊዜ ሳባ ከተማ ስላልነበረች ነው። በኃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ከምድረ-ገጽ ጠፍታ ነበር። የአዘቦ ሰዎች በሱ ጊዜ ስለነበሩ "አዜብ" አለ። በተጨማሪም እየሱስ የኢትያጵያን መልክአ-ምድር በዝርዝር ያውቀዋል። ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት እድሜው ከ22 እስከ 25 በነበረበት ወቅት በመላ እትዮጵያ በየብስ በባህርዋ፣ በወርድ በስፋትዋ ለ 3 ዓመት ተመላልሶባታል። ኢትዮጵያ አልሄደም ቢባልም እንኳዋን የዐለሙ ሁሉ ፈጣሪ ነውና ኢትዮጵያን ቀርቶ የድፍን ዐለምን ካርታ በመዳፉ ውስጥ ጨብጦ ይዞ ያውቃል።

በፊት እንዳመለከትኩት፥ የብሉይ ኪዳኑ ኦሪት ዘ ፍጥረት ነገሥት ምዕራፍ 10 ቁጥር 1 ንግሥት ሳባ ሥጦታ ይዛ ንጉሥ ሰለሞንን ለማየት እንደሄደች ይናገራል። ነግሥተ-ሳባ ከኢትዮጵያ መሆኗን ይህ አመልካች ነው። በዚሁ ምዕራፍ ስንኝ 11 እና 12 ንግሥት ሳባ የኦፊር ወርቅ፤ ከርቤ፣ ሰንደል ሽቱ እና ውድ ሥጦታዎችን ይዛ መሄዷን ይዘረዝራል። በዓለም ላይ ምርጥ የሆነው የኦፊር (አፋር) ወርቅ ምንጩ አፋር፣ ኢትዮጵያ ነው። ኢትያኤል ለሰለሞን እስጭና ለወሰደችው የሰንደል እንጨቱም እንዲሁ ምንጩ ኢትዮጵያ ናት። እስዋ በግመል እስጭና ለሰለሞን ይዛ ከሄደችው ማናቸውም ሥጦታ በተጨማሪ የኦፊርን ወረቅ ጨምሮ ሌሎች ውድ ብርቅየ ሥጦታዎችንም በመርከብ አስጭና ወስዳለታለች።

እንደ እውነቱ ከሆነ ኢትያኤል ከመሄድዋ በፊትም ሰለሞን ቤቱን ለመሥራት እና ለማስዋብ እነዚህን ቁሳቁሶች እንዲሁም እንስሶችን ከኢትዮጵያ ይገዛ ነበር። ይህን እውነታ አስመልክቶ ኦሪቱ እንደሚከተለው ብሏል፤--

"ንጉሱ ከታርሲስ / አፋር፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረች የወደብ ከተማ/ ወደብ ከሂራም የጦር መርከቦች ጋር አብረው የሚነሱ የንግድ

መርከቦች ነበሩት። የታርሲስ የንግድ መርከቦች ወርቅ፣ብር፣ የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣዎች እና ዝንጀሮዎች ጭነው በየሶስት ዓመቱ አንድ ጊዜ (ወደ ኢየሩሳሌም) ይመጣሉ። (መጽሐፍ ቅዱስ፤ ነገሥት 1:22) ንግሥት ሳባ ኢትዮጵያዊት ስመሆንዋ ይህ ሌላው ጠንካራ ማስረጃ ነው። ከሰሎሞን በኋላ በጀሆሳፋት ጊዜም አፋር ወርቋን በንግድ መርከቦች እየጫነች ለኢየሩሳሌም ማቅረበዋን ቀጥላለች። ጀሆሳፋት ወርቅ ስመጫን ወደ ኦፊር የሚሄዱ የንግድ መርከቦችን አሠርቶ ነበር። ሆኖም ጨርሶ አልቀዘፋም። ምክንያቱም በኤዚዮን ገበር ስጥመው በመሰባበራቸው ነው" (1 ነገስት፤ 22:48)። ኤዚዮን ገበር ኢትዮጵያ ውስጥ የአፋር/ኦፊር/ የነበረች ወደብ ናት። ይህም እንዲሁ ንግሥት-ሳባ የኢትዮጵያ ንግሥት እንደነበረች ያረጋግጣል። የሳባን እምነት በተመለከተ አረቦች ስሟን ለማጥፋት እንደሚሞክሩት ሃይማኖት-የለሽ አልነበረችም። በኖኅ፣ በሳሌም/ኢየሩሳሌም/ ንጉሥ በመልከጼዴቅ፣ ኢትዮጵያን በመሰረተው በኢትዮጵ እና ዙፋኑን በወረሰችው በታላቁ ንጉሠ-ነገሥት በአጼ/ኤስያኤል/ እምላክ ታምን ነበር። እነዚህ ንጉሶች ሁሉም ወደ እስራኤል ሄደው ስጦታ ሊያበረክቱለት የመሲሁን መወለድ የሚጠባበቁ ነበሩ። ሳባ በአጼ/ኤስያኤል/ ቤተ-መንግሥት እንደ እናትዋ እንደ አዝሚና እንደ መቆየትዋ እና የኢትዮጵ ዝርያ የሆነው አያትዋ ቤት ውስጥ እንደማደግዋ በዚህ እምነትና እውቀት ታንፃ ነበር። በመሆኑም ስለሰሎሞን ዝና ስትሰማ መሲሁ መስሏት ነበር። ስለዚህ ወደ እስራኤል ተጉዛ ሥጦታ የማበርከቱን ክብር ተሽቀዳድማ ለመውሰድ ወሰነች። አማካሪዎቿ ግን ሰሎሞን የንጉሥ ዳዊት ልጅ ነው እንጂ መሲሁ አይደለም ሲሉ ነገሯት። በዚህም ምክንያት ጉዞዋን አዘገየችው። በመጨረሻ ግን እውነቱን ራሷ ማረጋገጥ ስለፈለገች በመሄዷ ፀናች። ኢየሩሳሌም ስትደርስ ሰሎሞን መሲሁ አለመሆኑን አረጋገጠች። ሆኖም በጥበቡ እና በ ስርዐተ ቤተመንግሥቱ ተደነቀች፥ ተማረከች እና አግብታው ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳለት ተመለሰች። ስለዚህ በጨረቃ እና በከዋክብት የምታምን ጣኦት አምላኪ ነበረች የሚባለው ፍፁም ስህተት ነው።

ደቡብ አረቢያዎቹ "ቢልቂስ የኛ ንግሥት ነበረች" ሲሉ በከፊል እውነታቸውን ነው። በርግጥም የሁዋላ ሁዋላ የነሱ ንግሥት ነበረች። ነገር ግን የመንን በንግሥትነት የገዛችው አባትዋ ከሞተ ብዙ ቆይታና





በንግሥት ሳባ ፈቃድና በአግአዚዎች የጦር እገዛ ነበር። ታሪክዋ እንደሚከተለው ነው፤--

የቢልቂስ ዘረ ምንጭ ኢትዮጵያ ናት። በኛ መረጃ መሰረት አባትዋ አዲላዛር ይባላል። የየመን ንጉሥ ነበር። የመን የኖረ አንድ አውሮጳዊ እንደዘገበው እናትዋ ኢኬዩ/እትዩ?፣ አቴጌ?፣/ አዜብ፣ እንዲት የኢትዮጵያ ንግሥት ናት። በስመ ሞክሼነት እንጂ የንግሥት-ሳባዋ አዜብ አይደለችም። (N.Pearn and V. Barlow, *Quest for Sheba*, London, 1964), pp. 250-251. የቢልቂስ እናት፥ ሌላ አዜብ ናት ማለት ነው። እዎን ኢትያኤል አይደለችም።

ፕሮፌሰር ስርግው ሃብለስላሴም ኮማንደር ክራውፈርድ የተባለውንና የየመኑ ኢማም አማካሪ የነበረውን አውሮጳዊ አመልክተው እነዚህን ሁለት ጸሐፊዎች ይጠቅሷቸዋል። ኮማንደሩ ስለ ቢልቂስ የተወሰነ መረጃ የያዘ ጥንታዊ ጽሁፍ አግኝቻለሁ የሚል ነው። ፕሮፌሰር ስርግው ሃብለስላሴን እንጥቀስ፤

"ኮማንደር ክራውፈርድ ለየመኑ ኢማም የረጂም ጊዜ አማካሪ የነበረ በንዲት ቆንጆ ንግሥት እየተመራ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ስለሚተምም የግመሎች መንጋ የሚናገር አድማ ጠገብ ጽሑፍ አግኝቻለሁ" ብሏል። ስምዋ ቢልቂስ ይባላል። የሻር ሃቢል ልጅ ናት። እናትዋ የኢትዮጵያ ንግሥት ኢኬዬ አዜብ ናት። በልጅነትዋ በእናትዋ አገር ብዙ ዐመታትን አሳልፋ አባትዋ ከመሞቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ወደ ማሪብ ተመልሳለች። እንደታሪኩ ከሆነ ቢልቂስ ለሳቢያን ዘውድ የተወዳደረች የመጀመሪያዋ እንስት ናት።" (ስርግው ሃብለስላሴ፤ *የጥንታዊ እና መካከለኛ ኢትዮጵያውያን ታሪክ እስከ 1270* (ገጽ 38-39)።

ክራውፋርድ ካገኘው ጽሑፍ ቢልቂስ ከኢትዮጵያ ጋር ዝምድና እንዳላት እንረዳለን። ስዕለ-ሁኔታው አሁን ግልጽ ነው፤ ቢለቂስ ከእናትዋ ጋር በኢትዮጵያ ውስጥ አድጋለች። ይህም ኢትዮጵያ ውስጥ መወለድዋን ያሳያል። በርግጥ እናትዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ከኖረችና ቢልቂስም ኢትዮጵያ ውስጥ እናትዋ ጋ ካሳደገች ሌላጋ የት ታድጋለች? እውነት ነው፥ አባትዋ በኢትያኤል /ንግሥት ሳባ/አዜብ/ ሥር ያለ ንጉሥ ነበር። ምክንያቱም ያን ጊዜ ደቡብ አረቢያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበር። ንግሥት አዜብ ንጉሥ ሻር ሃቢልን

አግብታ ቢልቂስን ወልዳለች። የተጋቡት እሱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ይሁን ወይም እሷ ወደ እሱ ሄዳ የታወቀ ነገር የለም። አንድ ነገር ብቻ ግልጽ ነው፣ አብረው ብዙ አልቆዩም። ሳይፋቱ አልቀሩም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖረች ልጅዋን ቢልቂስን ታሳድግ ነበር። ቢልቂስ ራስዋም ባንድ ወቅት ካባትዋ ጋር አብራ ኖራለች። ማስረጃውም ደቡብ አረቢያ ውስጥ ባል አግብታ ነበር። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ባሏን ገድላ ወደ ኢትዮጵያ ኮበለለችና ከእናትዋ ከአዜብ ጋር ትኖር ጀመር። ባልዋን ገድላ ከየመን ሸሽታ ኢትዮጵያ ውስጥ ምትኖርበት ሰዐት የአዘቦና ቆቦ ንግሥት ከነበረችው ከሳባ ዘመድ ከንግሥት ሣሀይ ጋር ንግሥተ-ሳባን አጅባ ንጉሥ ሰለሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳለች።

ድንግል የነበረችው ኢትያኤል ንጉሥ ሰሰሞንን አገባችና የህግ ሚስቱ ሆነች። ዝሙት እንደፈጸመች ይህን መቁጠር ስህተት ነው፤ ምክንያቱም አግብታዋለች። ሴሎቹ ሁለቱ እንስቶች ቢልቂስ እና ሳሀይ የሰለሞን እቁባቶቹ ሆኑ፤ ምክንያቱም ሰለሞን ሴትን እማላይ ሰው ነበር። ቢልቂስን ያስረግዝ አያሰረግዝ ማስረጃ የለንም። ኢትያኤል እና ሣሀይ ግን ከሰሰሞን ጸንሰው እንደቅደም ተከተላቸው ቀዳማዊ ምኒልክን እና ዜጋዬን ወለዱ። በኋላ ቀዳማዊ ምኒልክ ዜጋዬን "ዛጉዬ" ሲል ጠራውና የእዘቦና የላስታ ንጉሥ አድርጎ በናቱ ዙፋን አነገሠው። ኢትያኤል እና ሣሀይ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ቢልቂስ ግን ሰመመለስ ምክንያት ስላልነበራት እዛው ቀርታ ስትኖር በኢትያኤል እና በቀዳማዊ ምኒልክ ትዕዛዝ አግአዚዎች ወደ የመን ወሰዷት እና አባትዋ ከሞተ በኋላ የመጀመሪያዋ የደቡብ አረቢያ ንግሥት አድርገው አነገሷት። ሰዚህ ነው አረቦች እንደ ንግሥታቸው የሚቆጥሯት እና ከኢትያኤል ወይም ከንግሥት ሳባ ጋርም የሚያምታቷት። ኢትዮጵያውያን የየመን ንግሥት አድርገው ባያነግሷት ኖሮ ወደ እረቢያ የመመለስ ተስፋ ሳይኖራት የሰሰሞን ቁባት ሆና በኢየሩሳሌም በቀረች ነበር። ምክንያቱም አረቦች እንደ ኢትዮጵያውያን ባለ ነፃ አእምሮ ሰላልሆኑ ሴት ልጅ ንግሥት እንድትሆን ፈጽሞ ስለማይፈቅዱላት ነው። ኢትያኤል ወይም ንግሥት ሳባ ራሷም አረባዊት ብትሆን ኖሮ ንግሥት ባልሆነች ነበር፤ ህቁም፥ አረቦች በታሪካቸውም ሴትን አንግሠው አያውቁም። ኢትዮጵያ ናት ቢልቂሰን





እንዳነገሠችው ሁሉ በአረቦች ላይ ሴቶችን የምታነገሥባቸው፣ወይም የምታነግሥላቸው።

ሰለዚህ ኢትያኤል(ንግሥት ሳባ) አረባዊት መሆን አትችልም፤ አልሆነችምም። ኢትያኤል (ንግሥት ሳባ) አረባዊት ሳትሆን ያሰጥርጥር ኢትዮጵያዊት ናት። ቢልቂስም እንዲሁ በናትዋ በኩል ኢትዮጵያዊት ነች። "ሳባ" ኢትዮጵያ ውስጥ በአጼ እስያኤል የተመሰረተች ከተማ ነበረች። አረቢያ ውስጥ ያለችው "ሳባ" ግን ኢትዮጵያውያን ደቡብ አረብን በቅኝ ገዢነት በሚገዙበት ወቅት ዋና ከተማቸውን ለማስታወስ የሰየሟት ሌላ ከተማ ናት። ሰመሆኑ መቸ ነው አረብ ኢትዮጵያን በቅኝ ገዢነት የገዛና ያስለጠነው? በፍጹም ተደርጎም አያውቅ። ህቁ የተገላቢጦሹ ነው። ይህ ነው ፣የንግሥት ሳባ (የኢትያኤል) እውነተኛው ታሪክ።

ከኢትዮጵያ ታሪካውያን ሃውልቶች፣ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እና በየመን ውስጥ ከሚገኘው መረብ ወንዝ ጎን ለጎን ኢትዮጵያውያን በየመን ውስጥ ሰነበራቸው ተሳትፎ ሌላው ማስረጃ የመን ያን ጊዜ "ናግራን" መባልዋ ነው።(ና በግራ በኩል፤ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የመንን ቅኝ በሚገዙበት ወቅት ወታደራዊ ማዘዣ ቃል ነበር። የመን የሚሰውም ቃል "የ ማን?" ከተሰኘው አማርኛ የፈለቀ ነው።)

ቀዳማዊ ምኒልክንና ወንድሙን ዜጋዬን በተመለከተ በርግጥ በወላጅ እናቱ እግር የአዘቦና የላስታ ንጉሥ አድርጎ ሲያነግሠው ምኒልክ ነው ዜጋዬን "ዛጉዬ" ብሎ የሰየመው። (ከዚህ የተነሳ ነው የቀዳማዊ ዛጉዬ ተወላጅ፣መራ ተክለ-ሃይማኖት ዳግማዊ ዛጉዬ ተብሎ በላስታና ላሊበላ ላይ የነገሠው እና ይኩኖ አምላክ ዙፋኑን እንደገና ወደ ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እስከሚመልሰው ድረስ ኢትዮጵያን የገዛውን የዛጉዬ ሥርወ-መንግሥትን የመሰረተው።)

ሴቶችን ንግሥት እያልን የማንገሥ ባሕላችን ደግሞ ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው ኢትዮጵያውያን በጾታ እኩልነት ያምኑ እንደነበረ ያሳያል። ሳባ ወይም ኢትያኤል የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ንግሥት አልነበረችም። ለምሳሌ ከሷ በፊት ንግሥተ-ነገሥታት የነበረች ንግሥት ነበረች። ኢቲግዝያ ትባላለች። የኢትዮጲስ 3ኛ ልጅ ነበረች። ስመ-መንግስትዋ ሰንደቅ-ጃን ይባላል። አባትዋ ኢትዮጲስ 3ኛ

በጣም ይወዳት ስለነበረ በመላ ኢትዮጵያ ንግሥተ-ነገሥት አደረጋት። ይኸውም ኢትያኤል ከመወለዷ ከብዙ ዐመታት በፊት ነበር። ለ45 ዓመት ገዝታለች። ከሷ በተጨማሪ ኢትዮጲስ ሌሎች ሁለት ሴቶች ልጆቹንም ንግሥቶች አድርጎ አንግሷቸዋል። አንዷ አሊና የተባለችው የኤደን ንግሥት ነበረች ። ከ 2900 ዓመት በፊት ደግሞ አክሱማይት የተባለው የንግሥት ሳባ የልጅ ልጅ ኢትዮጵያውያን ንግሥቶችን "ሕንደኬ" በሚል የማዕረግ ስም በኑቢያ፣ በግብፅ እና በሲቢያ ላይ ያነግሥ ነበር። በ1000 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከአክሱቱ ጀምሮ የ13 ንግሥታት ታሪክ ተመዝግቧል። እነሱም፡-

1. አዚት (የአክሱማይት አክስት).

2. ኒኒ

3. ቅንዳቅስ

4. ስማርታ

5. ካሺታ (የፈርዖን ቲሬሃቅ እናት)

6. ሙዝልብያ (ሴሳው መጠሪያዋ አሚን ሪትስ የነበረ፣ የፍቅር ዓምላክ ተደርጋ የተቆጠረች፣ 240 ባሎች የነበሯትእና 130 ዓመት የኖረች)

7. አንጥያ (የሙዝልብያ ልጅ)

8. አንስጥያ (የአንጥያ ልጅ)

9. አንስጣጥያ (የአንስጥያ ልጅ)

ከላይ የቀረቡት አራቱ እናቶች፣ ልጆች እና የልጅ ልጆች አጅግ ውብ ከመሆናቸው የተነሳ ፊታቸውን ያየ እና ድምፃቸውን የሰማ ማንኛውም ህመም ያለበት ሰው ከያዘው በሽታ ይፈወሳል ተብሎ ይታመን ነበር። ሁሉም እንደ ኣማልክት ተቆጥረው በግብፃውያን፣በኑቢያውያን እና በሊቢያውያን ይመለኩ ነበር።

10. የኔትሜር (ታላቅ የግብፅ ፈርዖን የነበረው የፒያንግሮ እናት፣)





11. ሃትሃር (የታላቁ ሂሚክስ ባለቤት)

12. ዳግማዊ ቅንዳቅስ

13. እቴ ህንደኬ ሻን (ለኢየሱስ፣ ለማርያም እና ለዮሴፍ ከሄሮድስ በሸሹበት ወቅት በግብፅ ውስጥ ጥገኝነት የሰጣቸውና የሳይኛው ግብፅ ንጉስ የነበረው የንጉሥ አማናቱ ተትናይ አህት) ናቸው።

ዝርዝሩ ከዚህ ቢረዝምም ለጊዜው ይበቃናል። አረቦች እነዚህን የመሰሉ ንግሥቶች ጨርሶ አልነበሯቸውም። የኢትዮጵያ ንግሥቶች ነበሩ ሲገዟቸው የኖሩት። አረቦች በኢትዮጵያ ሴቶች መገዛታቸው ብቻ ሳይሆን እንደ ጣኦታት ያመልኳቸውም ነበር። የነዚያ አስደናቂ ንግሥታት ዝርያዎች የሆኑ ቆነጃጅት ኢትዮጵያውያት ዛሬ የማይረቡ አረቦች ገረዶች ሆነዋል። አይ ጊዜ! ይህ ለኢትዮጵያ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ክስተት ነው!

የንግሥት ሳባ የዘር ሐረግ ምን ይመስላል? ለመሆኑ ኢትያኤል ወይም ንግሥት ሳባ በገሀድ የነበረች ሰው ናት? ኢትዮጵያዊትስ ነች? አዎ! ፍጹም በሆነ ርግጠኝነት ንግሥት ሳባ በገሀዱ ዓለም የነበረች ገሃዳዊ ሰው ናት፤ ኢትዮጵያዊትም ነች። የሳባ ከተማ ንጉሥ የነበረው የንጉሥ አጋቦስ ተብሎ ይጠራ የነበረው የ ተዋስያ ሳቢ የልጅ ልጅ ናት። ሳባ ከተማ የተመሰረተቸው የንግሥናው ስም ሰንደቅ-ዐልማ ይባል በነበረው በእሴ ወይም እስያኤል ነው። እስያኤል የቀዳማዊ ኢትዮጵ እና የሳልሳዊ ኢትዮጵ ተወላጅ ሲሆን የሳባ ከተማ የመጀመሪያው ንጉሥ ነው። የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ ረጅም ዘመን ከመኖሩም በላይ ልጆቹ እና ዘመዶቹ የሆኑ በርካታዎችን ንጉሦች እያደረገ ሾሟል። ከነዚህ ውስጥ አሞር ሳቢሳባ ተብሎ የነገሠው ልጁ ኩርፋን፣ ዣንዛቦ ተብሎ የገዛው የኩርፋን ልጅ ስርፌ፣ የቆቦ ንጉስ ተብሎ የነገሰው የስርፌ ልጅ አኪላዣን፣ እና የአኪላዣን ልጅ ሳባ፣ የሳባ ልጅ ጵርስቅላ አንዘቦ፣ የጵርስቅላ አንዘቦ ልጅ አቅጃቦ፣ እና ተዋስያሳቢ ተብሎ የነገሰው የአቅጃቦ ልጅ አጋቦስ ይገኙበታል። አጋቦስ የሚባለው ተዋስያሳቢ ልዕልት አዝሚናን ወለደ። ልዕልት አዝሚና ኢትያኤልን ወለደች። ኢትያኤል አያትዋ አጋቦስ፣ ተዋስያሳቢ ተብሎ በነገሰባት ሳባ ከተማ ንግሥት ሳባ ተብላ ተጠራች። ስለዚህ ከዚህ የዘር ሐረግ ሳባ የኢትዮጵ ዝርያ የሆነች፣ አያትዋ የሳባ

ንጉሥ የነበረ ኢትዮጵያዊት ናት ብለን እንደመድማለን። ይህ ሀት የንግሥት ሳባን የማንነት ጥያቄ ላንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ የሚመልስ ይሆናል። ከዚህ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልገው አይደለም። ማንኛውም ተጨማሪ ማስረጃ ይህን የሚያጠናክር ነው የሚሆነው። የኢትዮጵያን ትክክለኛ ታሪክ የያዙ መጽሐፎችን ላወደሙ የኢትዮጵያ ፓትርያሪኮች ለነበሩ ግብፃውንና የነሱ አሻንጉሊቶች ለነበሩ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት እግዜር ይይላቸውና የሳባን ማንነት ለማስረገጥ ከላይ የጠቀስነውን *ታሪከ-ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ* ን እስከምናገኝ ድረስ ብዙ ደከምን።

የሳባ የዘር ሀረግ ቀደም ሲል ከተመዘገበው የኢትዮጵ ዝርያዎች ከሆኑ የኢትዮጵያ ነገሥታት እና ንግሥታት ዝርዝር ጋርም ይስማማል። ይኸውም ከኢትዮጵ እና ከአሞር ጀምሮ እስከ አያትዋ እስከ አጋቦና ያለው ሁሉ ነው። ዝርዝሩ አላይ ቁልጭ ብሎ ስለሚታይ እንደገና ይመልከቱት። በሳባ ከተማ እያንዳንዳቸው ለ10 ዐመታት የገዙትን እና የግዛት ዘመኑን ወደ 16 ዓመት አሳድጎ ተጨማሪ 6 ዓመት የገዛውን አያትዋን ያገኛሉ። የያንዳንዱ ንጉሥ የግዛት ዘመን 10 ዓመት እንዲሆን የደነገገው አጼ እስያኤል ነበር። የኤትያኤል አያት የግዛት ዘመኑን ወደ 16 ዓመት ያራዘመበት ምክንያት የልጅ ልጁ ኢትያኤል ወላጆቿን ገድሎብኛል በሚል ቂም አጼ አስያኤልን ስለገደለችውና በዙፋኑ ላይ ራሷን የኢትዮጵያ ንግሥተ-ነገሥታት አድርጋ በማስቀመጧ ጠያቂ ስላልነበረው ነው። ከኢትዮጵ የዘር ሐረግ በግልጽ እንደምናየው አሞር፥ ጽርስቅላ፥ አቅጃቦ፥ እና አጋቦና እያለ ይዘረጋል። አጋቦና ለኢትያኤል አያትዋ ሲሆን እናትዋ አዝሚና እና አባትዋ በቤተ-መንግሥቱ ውስጥ እሷ የተጸነሰችበትን ዝሙት ፈጽመዋል ተበሎ በአጼ አስያኤል ፍርድ ስለተገደሉ ኢትያኤልን በሳባ ከተማ ያሳደጋት ነው። አዝሚና በወጣትነትዋ ስለተቀጨች ንግሥት ስለመባልዋ የተመዘገበ ነገር የለም።

ኢትያኤያል የኢትዮጵያ እንጂ የአረብ ንግሥት አለመሆንዋ ምንም ጥርጥር የለውም። መሆንም አትችልም። መጀመሪያ ነገር ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ኢትያኤል እና የእግአዚ ወታደሮቿ ቢልቂስን እስካነገሱላቸው ድረስ አረቦች ንግሥት አልነበራቸውም። ሁለተኛ ኢትያኤል ራስዋ የአረቦች ብቻ ንግሥት መሆን አትችልም። ምክንያቱም የአረብ ንግሥት ብትሆን ኖሮ መሲህ ነው በሚል





ሥጦታ ይዛ የአይሁድ ንጉስ ወደ ሆነው ወደ ሰለሞን በነጻነት መሄድ አትችልም ነበር። የእስማኤል ዘሮች አረቦችና እስራኤሎች ከጥንት ጀምረው ጠላታሞች በመሆናቸውም ጭምር። ኢትያኤል ግን ኢትዮጵያዊት በመሆንዋ የሰላም ንጉስ ስለሆነው ስለመሲሁ መወለድ እና በሁዋላ ለብአለገል የተባሉት እና ጠቢባን የሆኑት ኢትዮጵያውያን ነገሥታትም የኢትዮጵያ ንፁህ ምርቶች የሆኑትን ብጫውን ወርቅ፣ እጣን እና ከርቤ ሥጦታ ይዘውለት ወደ እስራኤል እንደሚጓዙ ሲነገር እየሰማች ነበር ያደገችው። አረቦች እና እስራኤል የአብርሃም ሚስት እና የይሣቅ እናት የሆነችው ሣራ የእስማኤል እናት ከሆነችው ከአጋር ጋር ከተቀያየመችና አብርሃም አጋርንና እስማኤልን ከቤቱ እንዲያስወጣቸው ካደረገችበት ጊዜ ጀምሮ ፀበኞች ናቸው። በእስማኤል እና በይሥሐቅ መካከል ያለው ፀብ ያን ጊዜ ይቅርና ዛሬ እንኳ በመካከለኛው ምሥራቅ በዝርያዎቻቸው ዘንድ ከባድ ደም መፋሰስ እንዳስከተለ ነው። ስለዚህ አንዲት የአረቦች ንግሥት (አረቦች ንግሥት ካለቻቸው) ስጦታዎች ይዛ ወደ አይሁድ ንጉሥ የመሄድ እድልዋ ዜሮ ነው። የሳሌም ንጉሥ ከነበረው ከመልከጼዴቅ እና ከአብርሃም ዘመን አንስቶ፥ እንዲሁም ፒቦራ የተባለችውን ኢትዮጵያዊቷን ልዕልት አግብቶ አራት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ከወለደው ከሙሴ ጊዜ ጀምሮ ከእስራኤል ጋር የደም ዝምድና የነበራቸው ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው። ስለዚህም ኢትዮጵያውያን ብቻ ነበሩ የአይሁድን ንጉሥ ጥበብና እውቀት ሊቀስሙ እና በእንቆቅልሽም ሊገዳደሩት ወደ ኢየሩሳሌም መጓዝ የሚችሉት። ከዚህ በተጨማሪ ንግሥት ሳባ ሌላ ቦታ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖርዋ ተጨባጭ እና የተሟሉ ዝርዝር መረጃዎች አሉ። መቃብሯም ተጨባጭ ማስረጃ ነው። አክሱም ውስጥ ጉሎ ማክዳ የተባለ ቦታ አለ። በኢትዮጵያ ትውፊት መሰረት የንግሥት ሳባ አጽም ያረፈው እዚያ ነው።



**አክሱም ውስጥ ጉሎ ማክዳ የሚገኘው የንግስት ሳባ መካነ-መቃብር**

ሌላው የማያወላዳ ማስረጃ አመጣጥዋን የሚያሳየው የዘር ሐረግዋ ነው፡፡ ከኢትዮጵ ጀምሮ የወላጆቿን መገደል ለመበቀል አስከገደለችው አስከ እሴ ወይም አጼ እስያኤል ድረስ የሚዘረጋው የዘር ሐረግዋ፡፡ ከሷ በኋላ የመጣውን ዝርያዋን በተመለከተ ደግሞ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምረን እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ድረስ 225 ነገሥታትን እንቆጥራለን፡፡ ሁሉም እነዚህ ነገሥታት ራሳቸውን ከሰለሞን ዘር ጋር በማያያዝ "በእግዚአብሔር የተመረጠ ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ" ሲሉ የኖሩ ህልውናቸው ሊካድ የማይቻል ደምና ስጋ የተዋሃዳችውና የለበሱ ገሃድ ሰዎች ነበሩ፡፡ የያንዳንዱን ንጉሥ የግዛት ቦታና ዘመንም ለይተን እናውቃለን፡፡ በዘመናችን ከነበሩት ከቅርቡ ንጉሠ-ነገሥት ከአጼ ኃየለሥላሤ ተነስተንም ወደ ኋላ እስከ ቀዳማዊ ምኒልከ እና ንግሥት ሳባም መቁጠር እንችላለን፡፡ የነዚህን ነገሥታት ህልውና መካድና አሽቀንጥረን መጣል ያስኬዳል እንዴ?





በምንም መንገድ፡፡ የቀዳማዊ ምኒልክ እናት ኢትያኤል፣ንግሥት ሳባ መሆኗን በትክክል እናውቃለን፡፡ አባቱ ንጉሥ ሰለሞን አይደለም የምንል ከሆነ ማነው ታዲያ አባቱ? እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ፍንትው ብሎ የሚታወቅ አባት አለው፡፡ ምኒልከ ያለ አባት የተወለደ ይሆን? ሰለሞን አባቱ ካልሆነ ለአያቱ ለዳዊት ይበልጥ ክብር በመስጠት እና በሱም በመኩራራት ራሱን እንዴት "የዳዊት ልጅ" ብሎ ሊጠራ ቻለ?

ንግሥተ-ሳባን እና ልጇን አፈ-ታሪክ ናቸው ብለን ብንወስዳቸው እንኳ የአግአዚን እና የቋንቋቸውን የግዕዝን በኢትዮጵያ ውስጥ መገኘት ምን እናደርገዋለን? የፈላሻዎቹን እና የታቦተ-ጽዮንንስ ጉዳይ እንዴት እናደርገዋለን? የቃል ኪዳኑ ታቦት ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን ብንክድ እንኳ ኢትዮጵያ በያንዳንዱ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያንዋ ውስጥ በምሳሌው የተቀረጸ ጽላት ያላት በዓለም ብቸኛ አገር እንዴት ልትሆን ቻለች? በተጨማሪም 40,000 አግአዚዎች እና ብዛታቸው ያልታወቀ ፈላሻዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገቡ? ቋንቋቸው ግዕዝስ በፊት የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ቋንቋ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን መገልገያ ቋንቋ ሊሆን እንዴት ቻለ? ይቺ የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያንስ ልክ አይሁድ በሲናይ በረሃ ለክብረ-በዓላት ያደርጉት እንደነበረው ዲያቆኖቿ እና ቀሳውስቷ ልብሰ-ተክህኖ ለብሰው፣ ታቦት ተሸክመው፣ ልዩ ልዩ ቀለማት ያሏቸውን ዣንጥላዎች የሚያጠሉባት እና ዑደት የሚዞሩባት በዓለም ላይ ብቸኛዋ አገር እንዴት ሆነች? አይሁድ ያደርጉት እንደነበረው እጣንስ እንዴት ሊያጤሱ ቻሉ? በአክሱም እና በጣና ደሴት እንስሳትን ይሰዉ የነበረውስ ለምንድነው? ቀዳማዊ ምኒልክ አግአዚዎችን ንጉሦች እና ካህናት እያደረገ በመንግሥቱ የሥልጣን ቦታዎች ላይ ከፍ አድርጎ ባይሾማቸው ኖሮ ኣግኣዚዎች በአክሱም ንጉሥ እና ንግሥት እስከ ማንገሥ እና ማውረድ ብቻ ሳይሆን ያልፈለጓቸውን ነገሥታት እስከ መግደልም የደረሰ ኃይል እንዴት ሊኖራቸው ቻለ? አግአዚዎች በ4ኛው ክፍለ-ዘመን ከንጉሠ-ነገሥት አብርሃ ጋር የተደራደሩት እና እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናት የሚሠራባቸውን የአይሁድ እምነት አሠራሮችን ወደ ኢትዮጵያ አስርገው ያስገቡት በምን ሥልጣናቸው ነበር? ንግሥተ-ሳባ ወይም ኢትያኤል ኢትዮጵያዊት ባትሆን፣ ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ሥጦታዎች ይዛ ባትሄድ እና

ቀዳማዊ ምኒልክን ጻንሳለት ባትመሰስ ኖሮ ይህና፣ ይህ ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ እውን መሆን አይችልም ነበር። ንግሥተ-ሳባ ወደ እስራኤል ያደረገችውን ጉዞ አስመልክቶ ሌሎች በርካታ ዝርዝሮችን ማቅረብ ይቻል ነበር። ሆኖም በዚህ ጥናት ትኩረቴ የንግሥት ሳባ እና የንጉሥ ሰለሞን ታሪክ እውነተኛ ታሪክ መሆን አስመሆኑን ማረጋገጥ ስላልሆነ እዚህ ላይ አበቃሰሁ። ሳባ በእውን የነበረች ኢትዮጵዊት ንግሥት ነበረች በሚሰው ህሳብ አጠንጥኛለሁ። አንባቢዎቼ ስለሷ እና ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ማግኘት ከፈለጉ "የተደበቁና ያልተነገሩ የአይሁድ እና የኢትዮጵያውያን ታሪኮች" የተሰኘውን መጽሐፌን እንዲያነቡ እጋብዛለሁ።መፅሃፉ ግን በእንግሊዝኛ ነው።

አህመድ ግራኝ ከለለሞናዊው የኦሮሞ ሥርወ-መንግሥት ጋር ጦርነት ባደረገበት ጊዜ እና በዘመነ-መሳፍንት ወቅት አምስት የኦሮሞ ጊቤ መንግሥታት ማለትም፡- ሊሙ-እናሪያ፣ ጂማ፣ ጎማ፣ ጉማ እና ጌራ አንፃራዊ ሰላም፣ የውስጥ አገዛዝ ነፃነት እና የንግድ ብልፅግና አግኝተው ነበር። ሊሙ-እናርያ በጂኦግራፊያዊ አቀማመጡ የንግድ መስመር እምብርት ስለነበረ እና የወርቅ ክምችትም ስለነበረው ከሁሉም ጎልቶ የወጣ እንደ ነበረ እሙን ነው። በሸዋ ውስጥ ያሉ የሰሳሌ ኦሮሞዎች ከአህመድ ግራኝ ጦር ጋር ተባብረው ‹‹ሰለሞናዊውን-ኦሮሞ-ስርወ-መንግሥት›› በሚወጉበት ወቅት የሊሙ-እናርያ ንጉሦች ግን ከመንግሥት ጋር ጥሩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ነበራቸው። ይህ ዲፕሎማሲም እስከ ንጉሠ-ነገሥት ሰርፀ-ድንግል ዘመን (እ.ኤ.አ1563-1597) ድረስ እና ከዚያም ወዲህ ዘልቋል። የሊሙ-እናርያ ንጉሶች ለኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ሌባ ያዥ በመሆናቸው የሌባ ያዥ ግብር ይገብሩ እንደነበረ ተመዝግቧል። ለምሳሌ ከእናርያ የሚከፈለው የወርቅ ግብር በሰርፀ-ድንግል ዘመነ-መንግሥት ሰማይ ነክቶ አምስት ሺ ወቄት ወርቅ ደርሶ ነበር።

ሁለቱ ብቁ የእናርያ መሪዎች አባ ጎሞል (እ.አ.አ.1800-1825) እና ተተኪያቸው እና ልጃቸው አባ ባጊቦ (እ.አ.አ.1825-1861) የሚጠቀሱ ናቸው። ወደ መሳፍንቱ ዘመን ማብቂያ አካባቢ አባ ጎሞል ከጎጃም እና ከከፋ መሳፍንት ጋር ዲፕሎማሲያዊና ንግዳዊ ትስስሮሽ ፈጠሩ። ተተኪያቸው አባ ባጊቦ በቡና፣ በወርቅ፣ በዝሆን ጥርስ፣ በጥርኝ፣ እና አልፎም በባሪያ ንግድ እጅግ ከመበልፀጋቸው የተነሳ ከአጼ ቴዎድሮስ





አያት ከራስ ጎሹ የጦር-ሠራዊት ጥበቃ እስከመጠየቅ ደርሰው ነበር። ይህንን ዓላማ ለማሳካት የዳሞት ገዢ ለነበሩት ለራስ ጎሹ ሴት ባሪያዎችን ጨምሮ የተለያዩ ሥጦታዎችን ልከውላቸዋል። በፃፉት ደብዳቤም ግንኙነታቸውን ለማጠንከር የደጃዝማቹን ሴት ልጅ ለጋብቻ ጠይቀው ነበር። ደጃዝማቹ ሥጦታውን ተቀብለው 30 ነፍጥ እና ስለመሳሪያው አጠቃቀም ስልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎችን ጨምረው ልከውላቸዋል።

ምንም እንኳ እነዚህ መንግሥታትና መሪዎቻቸው ኦሮሞዎች ቢሆኑም ኦሮሞነታቸው እንዳቸው ባንዳቸው ላይ ወረራ እንዳይፈጽሙ አላቀባቸውም። ሁለቱም አባ ጎሞል እና አባ ባጊቦ ጉማን ገባራቸው ሊያደርጓት በርካታ ጊዜ ወረራ ፈጽመውባታል። አባ ባጊቦ ከደጃዝማች ጎሹ ጋር ወታደራዊ ስምምነት እና የንግድ ግንኙነት ማድረግ የፈለጉበት ሌላው ምክንያት የጉዱሩን ለም መሬት ለመቆጣጠር ነበር። ‹‹የጅማው ንጉሥ አባ ጂፋር (እኤአ 1830-1855) በጣም ጠንካራ ሆነው ሲወጡ በጊቤ ክልል እና በታዋቂው ሶዶ ገበያ መካከል ያለውን መሬት ተቆጣጠሩ›› ። ቆይቶ እኚሁ አባ ጂፋር ጃንጀሮ፣ ጎማ፣ ጉማ እና ጌራ የተባሉትን ግዛቶች ወርረው አንድ አደረጓቸው። የእባ ጂፋርና ቀደም ያሉትም የአባ ጎሞልና የአባ ባጊቦ ወረራዎች አጼ ምኒልክ እማራን፣ እፋርን፣ ትግሬን፣ ወላይታን እና የኦሮሞ ግዛቶችን በማዕከላዊ መንግስታቸው ስር ለማድረግ ካደረጉት ወረራ የሚለየው በአላማው ብቻ ነው። ኦሮሞዎቹ መሳፍንት አጎራባች መሬቶችን በመያዝ የግል ግዛታቸውን ለማስፋፍት ሲሆን የምኒልክ ግን ከዘመነ መሳፍንት በፊት የነበረችውን ትልቋን ኢትዮጵያ በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ስር ለማሰባሰብ ነበር። በዚህ ምክንያት፥ ምኒልክ የኦሮሞ ግዛቶችን ብቻ አይደለም ወደ ግዛታቸው የቀላቀሉት፤ የጎንደርን እና የጎጃምን አማራም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው በማናቸውም ዘዴ አስገብረዋል። ሉዓላዊ ገዢነታቸውን ያልተቀበሉትንና ግብር መገበር እቁመው ያመፁባቸውን እማራ ሆኑም አልሆኑም ማንም ንጉሠ-ነገሥት እንደሚያደርገው በጽኑ ቀጥተዋል። ጎንደር አልገብርም በማለቱ፣ ከዚህ ቀደም በአፄዎቹ ሱስንዮስ እና ቴዎድሮስ ድምጥማጡ እንደ ጠፋ አስተውሰናል። የእነዚህ ነገሥታት ቁጣ የጎንደርን ህጻናትና አሮጊቶችን እንኳን አልማረም።

ቴዎድሮስ ጀምረውት፥ አፄ ዮሃንስ ቀጥለውበት፥ አፄ ምኒልክ አስፋፍተውት አፄ ኃይለሥላሴ ፈረሳቸውን ጠቅል ብለው የጠቀለሉት ሀገር፥ በመጀመርያ ለደርግ፣ ቀጥሎ ለኢህአዴግ ተርፎለት እስከ ዛሬ ይገኛል። በአሁኑ ሰዐት የዚህ ሁሉ ጥረትና ድካም ፍሬ ተመጋቢ ኢህአዴግ ነው። ነገ ደግሞ ተረኛው ገዢ ነው። ከእለታት አንድ ቀን ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠቃሚ ይሆን ይሆናል።

ዘር ግምት ውስጥ ሳይገባ ለሥልጣን እና ለግዛት መፋለም በልሂቃን ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ባሕሪ ነው። ልሂቃን ኃይላቸውን እስከሚያጠናክሩ እና ይገባናል የሚሉትን ግዛት እስከሚጠቀልሉ ድረስ ሁል ጊዜ እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ። የትግሬ የጦር አበጋዞች እንኳ ኃይላቸውን ለማጠናከር እና ግዛታቸውን ለማስፋት እርስ በርሳቸው ይዋጉ ነበር። ባለፉት ጊዜያት በመረብ ወንዝ ማዶና ማዶ ያሉት የትግራይ እና የትግሬ ገዢ መደቦች ለሥልጣን እና ለግዛት ሲሉ ተዋግተዋል። ለምሳሌ፣ ከአጋሜ የአጋሜው የደጃዝማች ሰባጋዲስ አባት የሹም አጋሜ ወልዱ ገዢ ቤተሰብ፣ ከተንቤን የአጼ ዮሐንስ 4ተኛው አባት ሹም ተንቤን ምርጫ ፣ ከእንደርታ የራስ ወልደሥላሴ ቤተሰብ እና የከንቲባ ተስፋ እና ዘርኣይ ቤተሰብ፣ ደጃዝማች ወልደሚካኤል እና ደጃዝማች ኃይሉ ከህማሴን ሁል ጊዜ በሥልጣንና በመሬት ጥያቄ አምርረው የሚዋጉ ደመኛሞች ነበሩ።

አጼ ቴዎድሮስ፣ በዋናነት በኦሮሞ ራሶች ተወስዶ የነበረውን ሰለሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት መልሶ መመስረት ከመለኮት የታዘዙት ተግባርና ግዴታቸው አድርገው ተመለከቱት። ስለዚህ፣ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆን በተጠናወታቸው ስተቻለም ንጉሠ-ነገሥት መባል በሚቋምጡ መሳፍንት ተከፋፍላና ብዙ ቦታ ተበጣጥላ የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ፣ ዘመነ-መሳፍንትን በማስቆምና ዳር ድንበርዋን እንደ ቀድሞው እስከ ቀይ ባህር እና እስከ ሕንድ ውቅያኖስ በማስፋት ኢትዮጵያን ወደ ቀድሞ ክብርዋና ገናናነትዋ የመመለስ ራዕይ ይዘው ተነሱ።

ይህንን ታላቅ ራዕያቸውን እውን ለማድረግ ከነዚያ ትናንሽ ዓላማዎች እና ጠባብ ግዛቶች ከነበሯቸው በርካታ መሳፍንት ጋር ጦርነት ማድረግ ነበረባቸው። አጼ ቴዎድሮስ አይቀሬ ጦርነት ከሚዋጉዋቸው የመጨረሻዎቹ መሳፍንት አንዱ ራስ ዓሊ ትንሹ ነበሩ። ከራስ ዓሊ





ትንሹ ጎን ደግሞ ኃይለኛዋ እቴጌ መነንን ነበሩ። እሳቸውንም መፋለም ነበረባቸው። እናትና ልጅ ሁለቱም የየጁው ሴሩ ጓንጉል እና የትልቁ ራስ ዓሊ ተወላጆች እንደ ነበሩ ይታወሳል። ልጃቸው ራስ ዓሊ ትንሹ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በነበሩበት ወቅት ቆንጆዋና ጮሌዋ መነን ንግሥት የመሆን ጽኑ ምኞት ስለነበራቸው ነበር የመጨረሻውን አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት ሳልሳዊ ዮሐንስን ያገቡአቸው።

ስሙ ካሳ ኃይሉ የነበረው ቴዎድሮስ ገና እንደተነሳ ራስ ዓሊ እና እቴጌ መነን ለሥርወ-መንግሥታቸው ስጋት መሆኑንን ወዲያው ተገነዘቡ። በዚያን ወቅት ለአልጋው የሚያሰጋ ኃይለኛ ሰው ሲነሳ በጋብቻ አስሮ በቀዬው መግታት የተለመደ ስለነበር የራስ ዓሊን ልጅ ልዕልት ተዋበችን ለካሳ ኃይሉ በጋብቻ ሰጡ። ካሳ ኃይሉ ተዋበችን ከልብ ስላፈቀራት ሽፍትነቱ ለጊዜው በጋብቻው ረግቦ ነበር። ሆኖም መርገቡ ብዙ አልቆየም። እናትና ልጅ፣ ሁለቱም ተዋጉትና ተሸነፉ።

ከዚያም የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥታት ሥልጣናቸውን መጀመሪያ በትግሬው ራስ፣ ቀጥሎ በኦሮሞ መሳፍንት ከተቀሙ ከ68 ዓመት በኋላ ካሳ ኃይሉ እውነተኛ ፍፁማዊ ሥልጣን ይዞና እውነተኛ ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ የካቲት 5 ቀን 1847 አጼ ቴዎድሮስ ተብሎ ነገሠ። ኦሮሞዋ ባለቤቱ እቴጌ ተዋበችም እውነተኛዋ ንግሥተ-ነገሥታት ሆና የካቲት 12 ቀን 1847 ዓ.ም. ዘውድ ተቀዳጀች።

ካሳ ኃይሉ ከአጼ ልብነ-ድንግል ጋር ዝምድና አለኝ ቢልም በእናቱ በወይዘሮ አትጠገብ አብተው በኩል ነው እንጂ በአባቱ በኩል አይደለም በሚል የጎንደር ሕዝብ ስንግሥና በዓሉ ጥቂት ቀደም ብሎ ተቃውሞ አነሳበት። በህጉ መሰረት በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ቀደም ካለው ንጉሠ-ነገሥት ጋር አለ የሚባለው ዝምድና መቆጠር ያለበት በሴትዋ ወላጅ (በእናት) በኩል ሳይሆን በወንዱ ወላጅ (በአባት) በኩል ነው። ‹‹እየሱስ ክርስቶስ እንኳ ዓለምን ለማዳን የተወለደው ከሴት ነው›› በማለት ቴዎድሮስ እንደ ንጉሳቸው እንዲቀበሉት የጎንደርን ህዝብ አሳመነ። ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማዳን የተነሳ በመሆኑ በሉነቱ ሊቀበሉት ይገባል። ሆኖም በቴዎድሮስ ደም ስር ውስጥ ጠብታ የንጉሣውያን ደም ባትኖር ኖሮ የቱንም ያህል በጦር ኃይለኛ ቢሆንም በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ያነሳውን ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደርግበትና ይብስ

ችግር ውስጥ ይከተው ነበር። በዚህ በሕዝብ ውድቅ የመደረግ ፍራቻ ስለተያዙ ነበር ክትልቁ ራስ ዓሊ እስክ ትንሹ ራስ ዓሊ ድረስ የነበሩት የየጁ ኦሮሞዎች በለለሞናዊው ዙፋን ሳይ በገዛ ፈቃዳቸው ፊጥ ለማለት ያልደፈሩት። ስለዚህም፥ አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት እንዳሻቸው እየሾለቱና ፍፁማዊ የውክልና ሥልጣን እየያዙ ኢዮጵያን ሲገዙ ኖረዋል።

የቴዎድሮስ አማት ትንሹ ራስ ዓሊ ከቴዎድሮስ ጋር ጦርነት ገጥመው ሲሸነፉ ሸሽተው ደምበጫ (ዳሞት) ገቡና የደጃዝማች ብሩ ጎሹን ክለላ ጠየቁ። ሆኖም በአባታቸው ሞት ስለጠረጠሯቸው ተጣሉና ወደ ደራ ሲያቀኑ ኦሮሞው ግራዝማች ዋቄ ዲቦ ለቴዎድሮስ አሳልፈው ሊሰጧቸው አሰሯቸው። ቴዎድሮስ ግን ራሩላቸውና ወደ አባቶቻቸው አገር ወደ የጁ እንዲሄዱ ይለቃቸው ዘንድ ደጃዝማች ዋቆ ዲቦን አዘዙ። አንዳንድ ሰዎች ግን የዳግማዊ አጼ ምኒልክ አባት ንጉሥ ኃይለ-መለኮት ናቸው ግራዝማች ዋቆ ዲቦን ወግተው ያስለቀቋቸው ይላሉ። የዚህ መፅሐፍ ፀሃፊ ግን በመጀመሪያው ሀሳብ ነው የሚስማማው። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ራስ ዓሊን ለመያዝ ቢፈልጉ ኖሮ እስክ ዕለተ-ሞታቸው ያሳድዱአቸው ነበር እንጂ ወደ የጁ ሲሄዱና በእዚያም ጭራሽ ያንዲት ትንሽ አገር ገዢ ሲሆኑ ዝም ብለው አያዩአቸውም ነበር። የሚያሳዝነው ራስ ዓሊ ትንሹ የእንግሊዙን ጄኔራል ናፒየርን ጦር በመርዳት በመቅደላ ምሽግ ሳይ የቆመውን ቴዎድሮስን መበቀላቸው ነው። ራስ ዓሊ የዳግማዊ ምኒልክን ዘመነ-መንግሥት እስክሚያዩ ድረስ በሕይወት ኖረው የዕድሜ ባለጸጋ ሆነዋል። ምንም እንኳ ራስ ዓሊ ከልጃቸው ከተዋበች ቢለያዩም በሚችግራቸው ሁሉ በምሥጢር ትረዳቸው ነበር። ተዋበች ሳባትዋ የምታደርገውን ልግስና ቴዎድሮስ ቢያውቁም ጣልቃ አልገቡም። ራስ ዓሊ የተዋበችን ሞት መራራ መርዶ ሲሰሙ በጣም አዝነው በተባ አማርኛቸው ቅኔ ተቀኙላት። በዚህም ምንም እንኳ ኦሮሞ ቢሆኑም አማርኛ ቋንቋን ለመንግሥታዊ ሥራ ማከናወኛ ብቻ ሳይሆን ጥልቅ ውስጣዊ ስሜታቸውን ለመግለጽም ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ በድጋሚ አስመስክሩ። ጥልቅ ውስጣዊ ስሜትን በግጥም እና በቅኔ መግለጽ በኢትዮጵያውያን መሳፍንት እና ነገሥታት ዘንድ የተለመደ ወግ ነበር። ተክለጻድቅ መኩሪያ ዐፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት





በተሰኘው መጽሐፋቸው ገጽ 186 ላይ ያሰፈሩት የራስ ዓሊ ግጥም / ቅኔ / ቀጥሎ ቀርቧል፤

*ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች*

*ራበኝም ስላት አህሉን ታስኝጭናለች*

*በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች*

*ሌባዬ ተይዛ ባል,ጋ ትሄዳለች።*

*የት አባትዋን አውቃ ታሳዝነኛለች፥*

*የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሳ፥*

*በኔማ ጣት (በኔ ማጣት) ገብቶ አሰጨነቀኝሳ።*

ቴዎድሮስ ለራስ ዓሊ እናት ለእቴጌ መነንም ምህረት በማድረግ ርኅራኄ አሳይተዋል። በሰባት ደጃዝማቾች እየተመራ የመጣውን ጦራቸውን እስክዚያን ጊዜ ድረስ በዚያች አገር ሳይ ታይቶ በማይታወቅ የጦር ስልት ብትንትኑን አውጥቶት ከማረካቸው በኋላ ወደ ጎንደር ተመልሰው እንዲሄዱ እና ክባላቸው ክአጼ ሳልሳዊ ዮሐንስ ጋር እንዲቀላቀሉ ማድረጋቸውትልቅ የርኅራኄ ተግባር ነበር። ምላሰኛዋ ሴትዮ ‹‹ይህ ፍየል ጠባቂ ቆለኛ›› ብለው የሰደቡአቸውንም ይቅር ብለዋቸዋል። ልጃቸውን ካገቡ በኋላ እንኳ በብዙ መልኩ ሲያዋርዱአቸው አልተበቀሏቸውም። ይህ መሀሪነታቸውና ይቅር ባይነታቸውም የጎንደርን ሕዝብ አድናቆት አትርፎላቸዋል።

ቆየት ብሎ ቴዎድሮስ ወደ ወሎ ሲያቀኑ ወርቂት እና መስተዋት ከተባሉ ሁለት ኦሮሞ ባላባት ወይዛዝርት ተቃውሞ ገጠማቸው። ወይዘሮ ወርቂት ከቴዎድሮስ ጋር ተዋግታ ድል ሆነችና ወደ አንድ ተራራ ሸሸች። እዚያ ሆና ለመስተዋት መልዕክት ላከች። መልእክቱም በራስዋ ዋና ከተማ በጊምቢያ-ወረሂመኑ አጼ ቴዎድሮስን ድግስ ደግሳ እንድትቀበላቸውና አዘናግታ እንድትገድላቸው የሚያሳስብ ነበር። ይህን ዓላማ ለማሳካት የወርቂት ሠራዊት ዓባላት እና ልጆቿ አግደው ዓሊ እና አምዴ ዓሊ በቴዎድሮስ ሠራዊት ውስጥ ሰርገው እንዲገቡ

ተደረገ። ሆኖም ሴራው ከሽፈና መስተዋት እና የወርቂት ልጅ አምዷ ዓሊ ሸሽተው ሲያመልጡ አግደው ዓሊ እና ሌሎች መኳንንቶች ተይዘው መቅደላ ታስሩ። የአቀባበል ግብዣ አስመስለው ሲገድሉአቸው በማሴራቸው የተናደዱት ቴዎድሮስ የማረኩአቸውን ወታደሮችና ህዝባዊ ጦር አንዳንድ እጃቸውን አስቆርጠው በወርቂት እና በመስተዋት ቦታ ወይዘሮ ተመኙን ሾመው ወደ ሸዋ አቀኑ።

አጼ ቴዎድሮስ እንደነገሡ ያረቀቁትን የሥራ መመሪያ ለኢትዮጵያ ህዝብ አነበቡ። በመመሪያውም የባርነት ሥርዓት እንዲቀር ደነገጉ። የመንግሥትን ወታደሮች በደሞዝ ለማሳደርና በጭሰኛው ላይ ሸክም የሚሆኑበትን የተሠሪነት አሠራር ለማስቀረት ቃል ገቡ። በየቤተ-ክርስቲያኑ የሚያገለግሉትን ካሕናት ቁጥር ከ10 በታች ዝቅ ለማድረግና የቤተ-ክሕነትን አስተዳደር ለማሻሻል እንደሚሞክሩ አስታወቁ። ሌሎቹ ካህናት በእርሻ ሥራ ላይ ተሰማርተው በላባቸው እንዲተዳደሩ አሳሰቡ፡ ይህ የመመሪያ አዋጃቸው ከካህናቱ ጋር ቅራኔ ውስጥ አስገባቸው። ቴዎድሮስን ለመጉዳት ሲሉም የሚወዱአቸውን ባለቤታቸውን እቴጌ ተዋበችን በቤተ-ክርስቲያን ተገኝተው ሥጋ-ወደሙ ሲቀበሉ መርዝ ቀላቅለው ሰጧቸውና ገደሉባቸው። በዚህ የተበሳጩት ቴዎድሮስ በቀኝም በግራም ካሉ መሳፍንት ጋር ጦርነት ውስጥ እየገቡ የሚቃወሙአቸውን ሁሉ ወደ መግደል የእብደትና የቀቢፀ-ተስፋ ድርጊት ውስጥ ገቡ።

የየጁውን ራስ ዓሊ ትንሹን፣ የወሎዋን ወርቂት ይማምን፣ የላስታውን ዋግ ሥዩም ጎበዜ ገብረ-መድህንን (ቴዎድሮስ እንደ ወደቁ ንጉሠ-ነገሥት ተክለ-ጊዮርጊስ ተብሎ ነግሷል፤)፣ የትግሬውን በዝብዝ ካሣ ምርጫን (አጼ ተክለ-ጊዮርጊስን ከያዘና ዐይናቸውን ጎርጉሮ አውጥቶ ከገደለ በኋላ አጼ ዮሐንስ 4ኛ ተብሎ ነግሷል)፣ ጨምሮ ሁሉም ጠላቶቹ ተባበሩና የእንግሊዝን ጦር እንደየ አቅማቸው ይረዱ ጀመር። አጼ ቴዎድሮስ ግን በናፒር ተማርከው ከሚዋረዱና አገራቸውንም ከሚያዋርዱ ይልቅ የራሳቸውንና የአገራቸውን ክብር እንደጠበቁ መሞትን መርጠው ሽጉጣቸውን ጠጥተው ወደቁ። ህዝቡም የሚከተለውን ቅኔ እየተቀኘ ህዘኑን ገለፀላቸው፤--

*ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው፤*





*ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው፤*

*ለወሬ አይመቹም ተንኮለኛ ናቸው፤*

*ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው።*

በሌላ አንፃር ግን ቴዎድሮስ በኀይል ስለ ገዙዋቸው በቴዎድሮስ ሞት የፈነጠዙም ብዙ ነበሩ። አንድዋ አልቃሽ በሚከተሉት ስንኞች ይህን ሁኔታ ገለጠች-

*ባለድባብ ንጉሥ ባለ ጥና አቡን*

*አየዞሩ ፈትዋት ኢትዮጵያን።*

*መላ የጎዣም ሰው፥ መላ የበጌምድር፥*


*መላው የትግሬ ሰው፥መላው የሸዋ ሰው ተይዞ በምጥ፥*

*የእንግሊዝ ሃኪሞች መጥተው ቢይዙት፥*

*ተገላገለ አሉ ይህ ሁሉ ፍጥረት።*

አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ እንደጻፉት አጼ ቴዎድሮስ በዘር አማራ አልነበሩም። ቋራ {ቁዋሬ} ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለአማራ አልወገኑም። ታማኝ አገልጋይዎቻቸው እነደ ጃዝማች ገልሞ እና ደጃዝማች ጠህዬ ቅማንት ነበሩ። ከአማራዎች ይልቅ እነሱን ያምኑ ነበር። አማርኛ አቀላጥፈው ይናገሩ ነበር። አማራ ሆኑ አልሆኑ አጼ ቴዎድሮስ ፈጽሞ የአማራን ሥር-መንግሥት እወክላለሁ አላሉም ወይም በፍፁም የአማራ ሥርወ-መንግሥት የሚል አልመሰረተም። በሠራዊቱ ውስጥ በርካታ አማሮች እንደነበሩ ግን እሙን ነው። የንጉሥ ሰለሞን እና የቀዳማዊ ምኒልክ ደም አለኝ ያለው በእናቱ በወይዘሮ አትጠገብ አብተው በኩል ሲሆን በርግጥም የአጼ ቴዎድሮስ እናት የለም ንጉሠ-ነገሥት የነበሩትና ስለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት እንደገና ሲመሰረት ዙፋን ላይ የተቀመጡት የአጼ ዮሐንስ ሳልሳዊ ዝርያ ነበሩ። የሆነው ሆኖ የዘር ሐረጋቸውን ጠበቅ አድርገን ስንመዝ

የሰሰሞን ደም በደም ሥራቸው ውስጥ እናገኛለን፡፡ የአጼ ልብነ-ድንግል ዝርያ ናቸው፡፡



ምንም እንኳ በአባታቸው በኩል ዘራቸው ቋራ ቢሆንም የአጼ ቴዎድሮስ እናት ያፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ከሆነ (ይሆናል ብዬም አስባለሁ) እና ቴዎድሮስ በአማርኛ አፋቸውን ከፈቱ በጎሣ ትርጉም መሰረት ጎሣቸው አማራ ይሆናል፡፡ በዘራቸው አማራ እንዳልሆኑ ግን አለቃ አፅመጊዮርጊስ ግልጥ አድርገው አስቀምጠውታል፡፡ አጼ ልብነ-ድንግል በእናታቸው ከቱሉ በዴሳ ልጅ ከኦሮሞይትዋ ከጽዮን ሞገሣ ነው የሚወለዱት፡፡ ከፍ ሲል አጼ ቴዎድሮስ ከእሳቸው አብራክ ይፈልቃሉ፡፡ የአጼ ቴዎድሮስን ማህተም ስንመረምር የተለመደውን የይሁዳ አንበሳን ምሥል ይዟል፡፡ ለንግሥት ቪክቶሪያ እና ለሌሎችም





በጻፉአቸው ደብዳቤዎች ላይም የአባቶቻቸውን ንጉሣዊ ግዛት (ሰሎሞናዊውን ሥርወ-መንግሥት) እግዚአብሔር ከኦሮሞዎች እጅ አውጥቶ እንደመለሰላቸው ጠቅሰዋል፡፡ (በአጼ ቴዎድሮስ ደም ስር ውስጥ የኦሮሞ ደም መኖሩን ያስታወሰ አንባቢ መቸም ፈገግ ማለቱ አይቀርም) ከሁሉም በላይ ደግሞ በደብዳቤዎቹ አናት ላይ ‹‹የእግዚአብሔር ባሪያ፣ የዳዊት እና የሰሰሞን ልጅ›› የሚል ማስታወቂያ ይነበብ ነበር፡፡ አሟሟታቸው አሳዛኝ ቢሆንም አጼ ቴዎድሮስ እውነተኛ የንጉሠ-ነገሥትነት ሥልጣን ይዘው ኢትዮጵያን እንደገና አንድ አድርገው ለማዋሃድ ያደረጉት ብርቱ ጥረት ከንቱ አልቀረም፡፡ ከእልፈተ-ሕይወታቸው በኋላ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በእግራቸው የተተኩት አጼ ተክለ-ጊዮርጊስ፣ከዛም አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ፣ አጼ ኃይለ-ሥላሴ የልፋታቸው ውጤት ተቋዳሾች ሆነዋል፡፡ በዘመነ-መሳፍንት ከነበረችዋ ኢትዮጵያ ይበልጥ የሰፋች አገር መውረስ ችለዋል፡፡ አላይ ጠቆም እንዳደረግኩት፥ ወታደራዊው ደርግ የገዛት እና ሕወሃት ኢህአዴግም ዛሬ እየገዛት ያለችው ኢትዮጵያ ዳር ድንበርዋ የተፈጠረ በአጼ ቴዎድሮስ፥ በአፄ ዮሃንስ፥ በአፄ ምኒልክ እና በአፄ ኀይለሥላሴ ጥረት ነው፡፡ ኢሕአዴግም ቢለቅና ማንኛውም ዓይነት መንግሥት ቢመሰረትም መጪውም መንግሥት የሚረከበው ያሁኗን ኢትዮጵያን ነው፡፡

የተከፋፈለች ኢጣሊያንን ለማዋሀድ እና የተበታተነች ጀርመንን አንድ ለማድረግ እንደ ቅደም ተከተላቸው ጋሪባልዲ እና ቢስማርክ ለየአገሮቻቸው ብዙ ደክመዋል፡፡ የጣልያንና የጀርመን ሕዝቦች ያን ጊዜ አስተዋዮቹ መሪዎቻቸው በሠሩላቸው የውህደት እና የአንድነት ሥራ ዛሬ በዓለም መድረክ ኃያላን ሕዝቦች ለመሆን በቅተዋል፡፡ ያን ጊዜ ጋሪባልዲ እና ቢስማርክ ለውህደት ባካሄዷቸው ጦርነቶች ዛሬ የጣልያንና የጀርመን ሕዝቦች ዕድለኞችና ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ ብልሆቹ የወቅቱ የአውሮጳ መሪዎችም አውሮጳን ያለምንም ደም መፋሰስ አንድ እያደረጓት ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም ላለፉት 60 ዓመታት በፍጥነት እያደገ የመጣው የፖለቲካ ብስለት አውሮጳን ወደ ውህደት ለማምጣት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል፡፡ አሁን አውሮጳ 300 ሚሊዮን ሕዝብ ይዛ አሜሪካንንና ቻይናን የምትፎካከር አንድ ጠንካራ አገር እየሆነች ነው፡፡ አብርሃም ሊንከን በተገንጣዮቹ በደቡቦቹ ላይ አስከፊና አውዳሚ ጦርነት በማካሄድ የተዋሀደች አሜሪካንን ፈጥሯል፡፡ በደቡብ

ተገንጣዮች ላይ የተቀዳጀው ድል ዛሬ የዓለም ኃያል አገር የሆነች አሜሪካንን አስገኝቷል፡፡ ከባድ ዋጋ ተከፍሎ በተገኘው አንድነት ሳቢያ የተፈጠረውን ዴሞክራሲና ብልጽግና ከደቡብም ከሰሜንም ያሉ ሁሉም አሜሪካኖች በመቋደስ ላይ ናቸው፡፡ እንኳን እነሱ በሃገራችን ውስጥ በደረሰብን መከራ እና ሰቆቃ እኛም ወደ አሜሪካ ሸሽተን ጥጋት አግኝተን የአሜሪካን አንድነት ባስገኘው ነፃነት እና ብልፅግና ተሳታፊ ለመሆን በቅተናል፡፡ አንድነትንና መልካም አስተዳደርን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ የተለዩ አይሆንም፡፡ ኢትዮጵያ ጠንካራ ልትሆን እና ልትበለጽግ የምትችለው በእኩልነት ላይ በተመሰረተ እውነተኛ አንድነት፣ በጋራ መከባበር እና በሕግ የበላይነት መስፈን ብቻ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥታዊት ሪፑብሊክ አገር ሆና ለግለሰብ እና ለብዙሃን መብቶች፣ ለሁሉም ዋስትና ሲሰጥ፣ ብሔሮች በትልቋ ኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው የውስጥ ነጻነታቸው ተከብሮ እውነተኛ የራስ-ገዝ የውስጥ አስተዳደር መብት ሲኖራቸው ነው፡፡

እሮሞ እና አማራ በማናቸውም ምክንያት እርስ በርሳቸው ቂም ቢያያዙም ያለፈውን መቆፈር ለዛሬው አጣዳፊ ችግር መፍትሔ አይሆንም፡፡ ወይም በማንኛውም መንገድ ለነገው አይበጅም፡፡ መፍትሔው ይቅር መባባል እና እርቅ ማውረድ ብቻ ነው፡፡ እርቆ አሳቢው እና ይቅር ባዩ ኔልሰን ማንዴላ ምሳሌያችን ሊሆን ይገባል፡፡ ዘረኞቹ ነጮች እሱን በአካል ለ27 ዓመታት በእስር ቤት አጉረው ምን ያህል እንዳሰቃዩት እና በህዝቡ ላይም ምን ያህል ጉዳት እና ሰቆቃ እንዳደረሱ መታወስ አለበት፡፡ ባለፈው ጊዜ ውስጥ ሆኖ ላጥፊዎች ተገቢ የሚባል ቅጣት ከማስጠት ይልቅ ማንዴላ ከፈላጭ ቆራጮች ነጮች ጋር ለመታረቅ እና ይቅር ለመባባል ወሰነ፡፡ ይህን ያደረገው በቀጣይ የሚደርሰውን የደም መፋሰስ እና የህገሩን ውድመት ለማስቀረት ሲል ነው፡፡ በውጤቱም ሥልጣን በሰላማዊ መንገድ ወደሱ ሕዝብ ተላለፈና ያላግባብ ይደርስ የነበረው የህይወት እና የንብረት ውድመት ተረፈ፡፡ ከጥቁሩ የደቡብ አፍሪቃ ሕዝብ ጋር በዘር፣ በባሕል፣ በኤኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ እና በንግድ እንኳ ሳይቀር ለመነካካት ከሚፀየፉ ከለየላቸው ዘረኞች ነጮች ጋር እንኳ መታረቅ እና ይቅር መባባል ከተቻለ ኢትዮጵያውያን ተቀላቅለው፣ ተጋብተው፣ ተዋልደው፣ ተዛምደው፣ አንድ ዓይነት ደም፣ መልክ፣ አመለካከት እና ሥነ-ልቦና፣ ኖሮአቸው፣ ተመሳሳይ ወግ፣ ባሕል፣ ታሪክ እና አገር





ተጋርተው ለ4000 ዓመታት እንደኖሩት ሁሉ አሁንም እርስ በርሳቸው ይቅር የማይባባሉበትና ሌላ አዲስ ሕይወት የማይቀጥሉበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ እርቆ አሳቢነት፣ ቅን ልቦናና በጎ ፈቃደኛነት ካሉ ይህንን የተከበረ ዓላማ በርግጠኝነት ማሳካት ይቻላል፡፡

ገብረ-መድህን ይባል የነበረው፣ የዘውድ ስሙን ተክለ-ጊዮርጊስ ያለው፣ የላስታውና የዛጉዌው ጎበዜ በ1861 ከአጼ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ላሊበላ ተብሎ ነገሠና በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ተቀመጠ፡፡ ካሳ ምርጫ ባይማርከውና በ1864 ዮሐንስ 4ተኛ ብሎ ራሱን በአክሱም ባያነግሥ ኖሮ (ላሊበላ) የዛጉዬን ሥርወ-መንግሥት እንደገና ሳይመሰርት አይቀርም ነበር፡፡

አጼ ዮሐንስም እንዲሁ የሰለሞን ሥርወ-መንግሥት ተወካይ ነኝ አሉ፡፡ በዚያ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ አራተኛው ዮሐንስ መሆናቸው ነው፡፡ ከእርሳቸው በፊት በዚያ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ሦስት ዮሐንሶች ነግሠዋል፡፡ የትግሬ ሥርወ-መንግሥት ልመስርት ግን አላሉም፡፡ እንደዚያ ብሎ ነገር ከዚያ በፊት በትግሬ መኳንንቶች ታሪክ ቀርቶ በአማራውና በኦሮሞው እንኳ አልነበረምና፡፡ ቢሆንም ቅሉ ኦሮሞዎች ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ በጋብቻ አማካይነት የሰለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት መሆን ችለዋል፡፡ አጼ ቴዎድሮስ እና አጼ ዮሐንስ ከሰለሞናዊው /እሥራኤል/ አግአዚ መኳንንት ጋር በአጼ ፋሲል በኩል የደም ዝምድና ነበራቸው፡፡ በሪሁን ከበደ፤ "የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ታሪክ፤" በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 147 ላይ እንደ ፃፉት ራስ ሚካኤል ስሑልም ከጎንደሩ አጼ ፋሲል ጋር ይዛመዳሉ፡፡


እንደ አቶ በሪሁን ከበደ የአጼ ዮሐንስ አግአዚ-ሰለሞናዊ ደም ከአጼ ፋሲል እስከ ሹም ተምቤን ምርጫ ወደ ታች ፈስሷል፡፡ አጼ ፋሲል የራስ አንስጣትዮስን እናት ንግሥት እህተ-ማርያምን ወለደ፡፡ ራስ እንስጣትዮስ ቢትወድድ ጊዮርጊስን ወለደ፡፡ ቢትወደድ ጊዮርጊስ ወይዘሮ ወለተ-ዮሐንስን ወለደ፡፡ ወይዘሮ ወለተ-ዮሐንስ ወይዘሮ መና-እስራኤልን ወለደች፡፡ ወይዘሮ መና-እስራኤል ሹም ተንቤን ምርጫን ወለደች፡፡ ሹም ተንቤን ምርጫ ካሣ ምርጫን ወለደ፡፡ ካሣ ምርጫ በንግሥና ስሙ አጼ ዮሓንስ 4ተኛ የተባለው ነው፡፡ አጼ ዮሐንስ 4ተኛ ለአግአዚ-ሰለሞናዊ ሐረጉ የሚጨነቅ አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት እንደሌሎቹ አግአዚ-ሰለሞናዊ ነገሥታት በማህተሙ ላይ

*"ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ" የሚል ጽሁፍ አሳስቀረፀም። ሆኖም ራሱን የጽዮን ንጉስ ብሎ ይጠራ ነበር፤ በማሕተሙ መካካልም ዘውድ የደፋ አንበሳ ነበረው።*

የአጼ ዮሐንስን ማሕተም ይመለከቷል፡ ማህተሙ የአረብኛ ጽሑፍ፡ ነበረው። ጽሑፉ "ንጉሠ ነገሥታት ዮሐንስ ንጉሠ ፅዮን ዘ ኢትዮጵያ፥ ዘ አምነገደ እስማኢል" የሚል ነበር። "ዘ እምነገደ-እስማኢል" የሚለውን ጽሁፍ ሳይ ዐይኖቼን አሳመንኩም ነበር። የገዛ ዐይኖቼን ተጠራጠርኳቸው። ሌሎች ሰዎች እንዲያነቡልኝ እስከመጠየቅም ደረስኩ። ሁሉም "ነገደ እስማኤል" እያሉ አነበቡልኝ። እስካሁን አልተዋጠልኝም። ዐይኖቸ ቢሳሳቱ እመርጣለሁ። አጼ ዮሐንስ የአረብ ዝርያ ያላቸው ይመስል በማህተማቸው ላይ ለምን "ነገደ እስማኤል" የሚል ጽሁፍ አስቀረጹ? አጼ ዮሐንስ ሙስሊም እንኳ አለመሆናቸውን እናውቃለን። እንዲያውም በርካታ ሙስሊሞችን በጉልበት ጭምር ወደ ክርስትና እምነት የመለሱ አክራሪ ክርስቲያን ነበሩ። ፍጹም የተጉ ክርስቲያን ነበሩ። ከእስራኤል ሰለሞናዊ የዘር ሐረግ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ስለማያውቁትና እስማኤልም የአብርሃም ልጅ ስለሆነ፤ አብርሃምም የእስራኤላውያን ሁሉ አባት ስለሆነ ከእስማኤል ጋር የነበረውን ዝምድና መቀበላቸው ይሆን? ከአብርሃም ዘር ማፈግፈጋቸውና ከአብርሃም እስራኤላውያን ልጆች ጋር ያላቸውን ዝምድና በተዘዋዋሪ ማወጃቸው ይሆን? ማሕተሙን አሳስተን ካላነበብነው በስተቀር ግራ የሚያጋባ ነው። እስካሁን የነበሩ የታሪክ ጸሐፊዎች ይህን ክስተት ለምን ሳያነሱ እንዳለፉትም ይገርመኛል። ምናልባት በየግል ምክንያታቸው ዝምታን መርጠው ይሆናል።







አጼ ዮሐንስ - የራስ ሚካኤል ስሑል ዝርያ በመሆናቸው ይሆናል አቶ በሪሁን ከበደ የጠቀሱት። አጼ ዮሐንስ ከሰለሞናዊው የደም መስመር ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ባኖራቸውም እንኳ እርሳቸው ግን በማህተማቸው ላይ ‹‹የይሁዳ አንበሳ›› የሚል ምልክት አስቀርፀው ዝምድናው ያላቸው አስመሰለዋል። በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ይሠራበት እንደነበረው ‹‹በእግዚአብሔር የተሾመ፤ የጽዮን ንጉሥ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት›› የሚል ግልጽ አርማም ነበራቸው። የመንግሥታቸው የሥራ ቋንቋም ትግርኛ ሳይሆን አማርኛ ነበር። እላይ የሰፈረውን ከማህተማቸው ስር የአለው ቁራጭ ደብዳቤያቸው እንደሚመሰክረው። ቀደምት ዝርያዎቻቸው ሰለሞናዊያን /እሥራኤላውያን/ ኣግኣዝያን ያደርጉት እንደነበረው ደብዳቤ ሲጽፉ በግዕዝ ይጀምሩና በአማርኛ ይቀጥሉ ነበር።

እላይ ከተጠቀሰው ጋር በተያያዘ አግአዚዎች ትግሬ አለመሆናቸውን ማስታወስ ተገቢ ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከተው እግአዚዎች ከእሥራኤልና ከጋዛ የመጡ አይሁዶች እና የዮቅጣን ጎሣ ዓባላት ናቸው። ትግራይ የሚለውን ስያሜ ያስገኙት ቲጋሩዎች ምንጮቻቸው ‹‹ቲክሪት›› የተባለች ከተማ እና ጥንት ሜሶፖታሚያ ይባል የነበረው የዛሬው ኢራቅ ውስጥ ያለው ‹‹የጤግሮስ/ቲግሪስ/›› ወንዝ ሸለቆ

ናቸው። ወደ ኢትዮጵያ ያቀኑት ‹‹ታላቅ›› ተብዬው አሌክሳንደር ኢራቅንና ሶሪያን በወረረበት ወቅት በኣግኣዚው ንጉሠ-ነገሥት በአጼ ዋዜባ ዘመን በ331ዓ.ዓ ነው። የአጼ ዋዜባ ዋና ከተማ አክሱም ነበረች። አክሱም የተመሰረተችው በ880 ዓ.ዓ ገደማ በንጉሠ-ነገሥት አክሱማይት ነበር። ይኸውም 550 ዓመት ቀደም ብሎ ማለት ነው። አጼ አክሱማይት ከተማዋን በስሙ መሰየሙ ማስረጃ ይሆናል። ቲክሪት ከባግዳድ ሰሜናዊ ደቡብ በ140 ኪ.ሜ ርቀት በጢግሮስ ወንዝ ላይ ተሰርታ አሁን ድረስ ያለች ከተማ ናት።

ቆየት ባለው ዘመን የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት በጦርነት፣ በርሀብ፣ እና የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዋል። በ330 ዓ.ዓ ገደማ አጼ ዋዜባ እና አሌክሳንደር ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ስምምነት ከፈፀሙ በኋላ አጼ ዋዜባ ለአሌክሳንደር 21,000 ምርጥ ተዋጊዎቹን ሰጥቶታል። ዘመዱን ንግሥት ህንደኬ ቅንዳቅስ ኒካውላ የተባለችውን ሚስት እንድትሆነው ድሮለታል። ህንደኬ አሌክሳንደርን ከማግባቷ በፊት ነጋዴ ተመስሎ ኢትዮጵን ሲሰልል ይዛው ነበር። (106) እነዚያን እስፈሪ የኢትዮጵያ ወታደሮች ተጠቅሞ አሌክሳንደር ሶሪያንና ባቢሎንን፣ ማለትም የዛሬዋን ኢራቅን ለመያዝ ችሎ ነበር።

አሌክሳንደር ውለታውን ለመመለስ ሲል በመጀመሪያ ለአጼ ዋዜባ አንድ ሺ ሜቄዶኒያንን ሰጠ። አጼ ዋዜባም የሚሰፍሩበት ጥሩ መሬት ሰጣቸው። መቄዶኒያኑም እዲስ የሰፈሩበትን ቦታ መቄት፣ ድላንታ እና መቂዶ ሲሉ መነሻ እገራቸውን በሚያስታውስ መልክ ሰየሙት። እነዚህ ቦታዎች ዛሬም (በዚሁ መጠሪያቸው) ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ። ከመቄዶናውያን በተጨማሪ የመቄዶኒያው አሌክሳንደር በጀግኖቹ የኢትዮጵያ ወታደሮች ብርታት ሶሪያንና ኢራቅን ካንበረከከ በኋላ 25,000 ሶሪያውያንን እና ኢራቃውያንን ለኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት በስጦታ ሰጠ። ከሶሪያ የመጡት አዲስ የሰፈሩበትን ቦታ ሶሪ፣ ስራዬ፣ ሺሬ እና ሼሪ ብለው ሰየሙ።

በ330 ዓ.ዓ ገደማ ከዛሬዋ ኢራቅ ከቲክሪት እና ከጤግሮስ፥ የቲግርስ ወንዝ አካባቢ፥ የመጡትም ወታደራዊና ፖለቲካዊ ኃይል ሲያጎለብቱ ምንጫቸውን በሚያስታውስ መልክ የኢትዮጵያውን መኖሪያቸውን ትግረ፥ ትግሩ፥ ትግሪ፥ ትግራ፥ ትግሬ፥ ትግር፥ ትግሮ ብለው ጠሩ። አጋዝያንም ስማቸው ትግሬ እንዲባል ተወሰነባቸው።





በቦታው ላይ እነዚህ ከመምጣታቸው ከ550 ዓመት በፊት ጀምሮ የነበሩና የአክሱማይትን ሥልጣኔ የመሰረቱ አገር በቀል ነዋሪዎች ነበሩበት።ሂማሪት፥ ሃርጊጎ፥ ራይዳን፥ ደቅ፥ አስገድ፥ ሚክሮብያ፤ በጅያ፥ ችያ፥ ናይቦ፥ ስእኔ፥ ሃሳን፥ ሃበሳት፥ አንጋቤ፥ ስጀየን፥ ቲያሞ፥ ቤጋ፥ ቦጎል፥ በደው፥ ከሰው፥ ፈለው፥ አርሆ፥ ከሮስ፥ ደንዲ፥ ሱካ፥ ኢልግ፥ ከሳዊ፥ አሳሁርት፥ አብስ፥ አግአገዝ፥ ያ፟ክ፥ ከሮስ፥ አነጋቤ እና ናይቦና ናቸው። (እነዛ ከሶርያና ከኢራቅ የመጡት ህዝቦች፥ ከእነዚህ ነባር የኢትይጵያውያን ዘሮችም ጋር በጋብቻና በባህል ተቀላቅለው በ 2300 ዐመታት ውስጥ የዛሬው ኢትዮጵያውያን ትግሬዎች ለመሆን በቅተዋል። አግአዝያን ግን የመጡት ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር ከነሱ 600 ዐመታት ቀድመው፥ ማለትም በ2950 ዓ.ዓ ገደማ ስለነበር እነዚህን ነባር ሕዝቦች አግአዚዎች ተቀላቀሏቸው እና ተዋህደው ሃይማኖታቸውን አስፋፍተው ንጉሣውያን ቤተሰቦች እየተቆጣጠሩ ተንሰራፍተው ይኖሩ ነበር። አካባቢው ትግራይ ተብሎ መጠራት ሲጀምር አግእዚዎቹም ምርጫ ስላልነበራቸው በዚያው ተካተቱ። በዚህም በጊዜ ብዛት አግአዚዎቹን እንደትግሬ የመቁጠር ውኻንብር ተጀመረ። አግአዚዎቹ መነሻቸው ከእስራኤል እንጂ ከሶሪያና ከኢራቅ እንዳልሆነ አውቀናል። ከጊዜ በኋላ ትግሬ ተብለው የተጠሩት ነገዶች ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው ከ600 ዓመት በፊት ጀምሮ አግአዚዎቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበሩ። ከሁሉም በላይ ደግሞ አግአዚዎቹ ግዕዝ ነው ቋንቋቸው። ከትግርኛ ይሰያል። እንደ እውነቱ ከሆነ ትግርኛ ከግዕዝ ይልቅ ለአረብኛ ይቀርባል። ሁለቱ ቋንቋዎች፣ ግዕዝ እና ትግርኛ አንድ ዓይነት ቢሆኑ ኖሮ የትግሬ ተማሪዎች ግዕዝ ለመማር እስከ ጎጃምና ጎንደር ድረስ አይሄዱም ነበር። የሆነው ሆኖ ከትግርኛ የሚለየው ትግረ ቋንቋ ከግዕዝ ጋር በቅርብ እንደሚዛመድ መታወቅ አለበት።

ለመድገም ያህል፥ ከሶሪያ እና ከኢራቅ የመጡት ነገዶች ከላይ ከተጠቀሱት ከነባሮቹ ጎሣዎች ጋር እየተጋቡ ተዋልደው ተዋሃዱና እንደሌሎቹ መጤዎች ሁሉ ከዘመን ብዛት (በ 2300 ዐመታት ውስጥ) የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ሆኑ። ስለዚህም የመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች በቀድሞው እነሱነታቸው ዛሬ የሉም። ቢኖሩም አያችሱም።

ከአጼ ዮሐንስ ሞት በኋላ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ በዘሮቻቸው በቀዳማዊ ምኒልክ እና በይኩኖ-አምላክ የተመሰረተውን ሥርወ-

መንግሥት እጃቸው ከተቱ:: ዳግማዊ አጼ ምኒልክም ከአጼ ልብነ-ድንግል ጋር ከአህመድ ግራኝ ሸሽቶ መንዝ ተደብቆ በነበረው ትንሽ ልጃቸው በያቆብ በኩል ይዛመዳሉ:: (‹‹ሞአ አንበሳ ዘ-እምነገደ ይሁዳ ድል እድራጊው የይሁዳ ነገድ አንበሳ››) ተብለው ነገሡ:: ዳግማዊ ምኒልክ ብቻ ሳይሆኑ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ-ሥላሴ ፍፃሜ ድረስ ሁሉም ንጉሠ-ነገሥቶች ለአይሁድ ነገድ እውቅና ለጥተዋል፤ ከአይሁድ ነገድ ነን እያሉም አውጀዋል:: ከአይሁድ ነገድ፣ ከእግአዚና ከሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ጋር ምንም የደም ዝምድና ያልነበረው የገናናዎቹ የኢትዮጵና የደሸት ልጅ አማራው ለኢትዮጵያ ስልጣኔ በተለያዩ የእውቀት ዘርፍ እና የሥራ ጥበብብ ከማበርከቱ በተጨማሪ በነበረው ታላቅ የጦር ብቃት እና ችሎታ የሀገሩን የኢትዮጵያን ዳርድንበርና መንግሥት በታማኝነት ና በቅንነት በመጠበቅ ና እባክህ ለመንገሥ እርዳን ሲሉት ያመነበትን እና የሚወደውን በማንገሥ፣ እንዲሁም ተባበረን ሲሉት ጥያቄው ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ሲመስለው ከዙፋን መውረድ ይገባዋል የአለውን ሲያወርድ ኖረ:: አማራው ሚናውን ጠንቅቆ የተረዳ፣ ፍጹም ታማኝነት የተካነ ስለ ሆነና የስልጣን ጥማት ስላልነበረው እንጂ ቢፈልግ ኖሮ የማይበገር የጦር ኃይል ስለነበረው ሌሎችን በማንገሥ ፈንታ ራሱን እንዳይነግሥ ምንም የሚያግደው ነገር እልነበረም:: በዚህ የተአማኝነት ጠባዩና ለስልጣን ባለመስገብገቡ የማራ ልጅ አማራ ሊወደስ እና ሊደነቅ ይገባዋል:: እድሉ መጥፎ ሆኖበት ግን ለኢትዮጵያ ለዋለው ውለታ ተገቢውን ካሳ ካለመከፈሉ ም በላይ በመሸለም እና በመመስገን ፈንታ እሱ ባልዋለበት ና ባላጠፋው ነገር • ቋንቋው የመንግሥት አፍ በመሆኑ ብቻ እንደ ገዢ መደብ ታይቶ በየአቅጣጫው መጠቃቱ ነው::

ስለ አጼ ምኒልክ ቤተሰብ ጥቂት ለማለት ያህል፣ የዳግማዊ ምኒልክ እናት እጅጋየሁ ለማ አዲያሞ ከላስታ ነበሩ፤እገው ሳይሆኑ አይቀሩም:: አያታቸው ደጃዝማች አዲያሞ የላስታ ባላባት ሲሆኑ አባታቸው ለማ ደግሞ ፊታውራሪ ነበሩ:: የምኒልክ ባለቤት እቴጌ ጣይቱ ብጡል የኦሮሞ ደም አላቸው:: የወንድማቸው ልጅ ኦሮሞው ጉግሳ ወሌ አባትዋ ንጉሠ-ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሲሞቱ ንግሥተ-ነገሥታት የሆነችውን ዘውዲቱ ምኒልክን አግብቶ ነበር:: ጣይቱ • በዘመነ-መሳፍንት ጎንደር ሆኖ ኢትዮጵያን ከገዛው የኦሮሞ ቤተ-ሰብ





ከሆነው ከየጁው ሌሩ ጓንጉል ይዛመዳሉ:: አጼ ምኒልክም በኦሮሞ ሹማምንት ነበር የተከበቡት:: ለምሳሌ ገበየሁ ጎራ፣ ባልቻ አባ ነፍሶ፣ ሃብተ-ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ አሉላ ብጡል፣ ወሌ ብጡል እና ምንም እንኳ ሰለሞናዊውን/የኦሮሞ/ ሥርወ-መንግሥት እንደገና ለመመስረትና ለማጠናከር በተደረገው ጦርነት በርካታ የኦሮሞ ግዛቶችን በመውጋታቸው በአንዳንድ የዘመኑ ተራማጆች ዘንድ የተጠሉ ቢሆኑም ራስ ጎበና ዳጬም የሚጠቀሱ ናቸው::

የንግሥት ጣይቱ ወንድሞች አሉላና ወሌ ከምኒሲክ ጋር በመቅደላ የአጼ ቴዎድሮስ እስረኞች ነበሩ:: ከዚያ አምልጠው ወደ ሸዋ መጡና ቀደም ሲል ከቴዎድሮስ አምልጦ መጥቶ ንጉሥ የሆነውን ምኒልክን ተቀላቀሉ:: ሁለቱ ኦሮሞ ወንድማማቾች ከምኒልክ ጋር በመቅደላ እስር ቤት ለዓመታት አብረው ስለቆዩ የጠበቀ ወዳጅነት ነበራቸው:: ለዚህ ነበር ከቴዎድሮስ አምልጠው ወደ ሸዋ መጥተው በደስታ የተቀበሉአቸውን ምኒልክን የተቀላቀሉት:: ጣይቱ ወንድሞቿን ልትጠይቅ ስትመጣ ከምኒሊክ ጋር ተዋወቀች::

ከቴዎድሮስ እና ከዮሐንስ በኋላ የቀድሞውን የኢትዮጵያን አንድነት እንደገና የመመለሱና እንዲት ሉዓላዊት አገር የመፍጠሩ ሃላፊነት በምኒልክ ትከሻ ላይ ወደቀ:: ለፋፊ ግዛት ከያዙት ውስጥ አብዛኞቹ ምኒልክ የዮሐንስ ወራሽ መሆኑን ተቀብለው በሰላም ገቡላቸው:: እነሱም የጎንደር፣ የጎጃም፣ የወሎ፣ የትግሬ፣ የኤሉባቦር፣ የሲዳማ እና የወለጋ መሪዎች ነበሩ:: የወለጋ ባላባቶች ኩምሳ ሞረዳ እና ጆቴ ጦርነት ውስጥ ቢገቡ እንደሚሸነፉ ስላወቁና የውስጥ አስተዳደር ነፃነታቸው እንደሚከበርላቸው በምኒልክ ቃል ስለተገባላቸው አስተውለው ወሰኑና ለምኒልክ ገቡ:: በመሆኑም ለነሱም የውስጥ አስተዳደር መብት ተጠበቀላቸው፤ ላገሪቱም የግዛት አንድነቷ ሰመረላት::

የተወሰኑትን የጊቤ ግዛቶች ወርሮ ያጠፋቸው የኦሮሞው ንጉሥ አባ ጂፋርም እንዲሁ በሰላም ለምኒልክ ገባና የግዛቱን ደህንነትና ብልፅግና አስከበረ:: ምኒልክም በክብር እና በእንክብካቤ ያዙት:: ጠፍቶ የነበረውን ያገሪቱን አንድነት እንደገና ለመመለስ ምኒልክ የተጠቀሙበት የራሳቸው ሰላማዊ ብልሃት ነበራቸው:: መጀመሪያ ለባላባቱ ምክር አዘል መልዕክት ይልኩበታል፤ ‹‹አሁን ንጉሠ-ነገሥትህ

እኔ ነኝ፣ እውቅና ስጠኝና የኔን የበላይ ገዢነት ተቀበል፤ በዚህም የደም መፋሰስን እናስወግድ፤ ግብሬን አስገባልኝ!›› ይሉታል። ባላባቱ በዚህ ሀሳብ ከተስማማ ምኒልክ ማእረጉን አሳድገው ይሾሙትና በያዘው ግዛት ላይ ሌላ ግዛት ይጨምሩለታል። ወይም የያዘውን ያፀድቁለታል። ባላባቱ በደረሰው መልዕክት ካልተስማማ ግን ደም መፋሰስንና የጦርነት ውድመትን ባይጋብዝ የተሻለ መሆኑን በድጋሚ ያስገነዝቡታል። አሁንም አሻፈረኝ ካለ ምኒልክ ጦርነት ገጥመው ያሸንፉታል፤ ከዚያም በሚገርም ሁኔታ ተሸናፊውን ምህረት አድርግውለት መልሰው በሥልጣኑ ላይ ያስቀምጡትና የበላይነታቸውን በተጨባጭ ያሳዩታል። የወላይታው ንጉሥ ካኦ ጦና ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይህ ሰው ምኒልክ ደም መፋሰስንና የንብረት ውድመትን እናስቀር እያሉ በተደጋጋሚ ቢያስገነዝቡትም፥ ቢማጠኑትም አልሰማ ብሎ ወደ ጦርነት ውስጥ ገባና ቆስሎ ተማረከ። ምኒልክ ግን በቀድሞ የወላይታ ንጉሥነት ሥልጣኑ ላይ መልሰው አስቀመጡት። የምኒልክ ይቅር ባይነት፣ ትዕግሥት እና መሓሪነት ብዙውን ጊዜ አፀፋውን አስገኝቶላቸዋል።

የተወሰኑት ባላባቶች ለምሳሌ ይማም መሐመድ ዓሊ (በኋላ የወሎው ንጉሥ ሚካኤል የተባለው)፣ ይማም አባ ዋጠው (የወሎዋ የንግሥት መስተዋት ልጅ)፣ መርእድ አዝማች ኃይለ-ሚካኤል እና የሸዋው ደጃዝማች መሸሻ ሰይፉ፣ የትግራዩ ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ እንዲሁም የበጌምድሩና የሰሜኑ ራስ ዘውዴ በምኒልክ ላይ ሁለት፣ ሦስት ጊዜ አመፁባቸው። ምንም እንኳ አንዳንዶቹ የሞት ፍርድ ቢገባቸውም ምኒልክ ግን ደጋግመው ማሩአቸው። የሚያስገርመው ነገር ሁለቱም የወሎ ይማሞች፣ መሐመድ ዓሊ፣ እና እባ ዋጠው በተደጋጋሚ ሲያምፁባቸው ምኒልክ ግን ደጋግመው ምህረት ከማድረጋቸውም በላይ ክርስትና እያስነሱ (ይማም አባ ዋጠው፣ ኃይለ-ማርያም የሚል የክርስትና ስም ተሰጥቶታል፤) የክርስትና አባት እየሆኑእቸው በሹመት ያሳድጉአቸው ነበር። ክርስትና ከተነሳ እና ራስ ሚካኤል ከተባለ በኋላ ምኒልክ ልጃን ሸዋረጋን ለይማም መሐመድ ዓሊ መዳራቸውም እርግጥ ነው። የምኒልክ ተተኪ ልጅ ኢያሱ የተወለደው በዚህ ጋብቻ ነበር። ምኒልክ በዚህ መልክ ያገሩን አንድነት አንፃራዊ በሆነ ሰላም እና መረጋጋት ማስጠበቅ ችሎ ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ እነዚህ የጦር አበጋዞች እና የ ሀገር መሪዎች በ1896 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ወቅት





ወራሪዋን ጣልያንን ድባቅ በመምታት ረገድ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። በዚህ ወቅት እንደ እናት ተወደው ‹‹እምዬ›› እስከ መባል ከደረሱት ምኒልክ ጋር ትብብር የቸሩት አንዱም በአፄ ምኒልክ የቻይነት ፀባይ እና መልካም አስተዳደር ሰኬት ነው። ትናንሽ ግዛቶች በማእከላዊው መንግሥት ስር መጠቃለላቸውን የተቃወሙትን ግን ምኒልክና ተባባሪዎቻቸው ክፉኛ ቀጥተዋቸዋል። የጡት መቁረጡን ማስረጃ - ቢስ ክስ እንኳን ብንተወው፥ ለምሳሌ የሜጫና የአርሲ ኦሮሞዎች የምኒልክን መስፋፋት ሲቃወሙ አምነው እስከሚገቡ ድረስ ያለርኅራኄ ተመትተዋል። እነሱም ግን እጃቸውን እጣጥፈው አልተቀመጡም። ጠንክረው በጀግንነት ተዋግተው የምኒልክ ሰራዊት ላይ ከፍተኛ እልቂት ፈፅመዋል። ከዚያ በኋላም አምነው በሰላም ስላልገቡላቸው ምኒልክ የራሳቸውን የጦር አበጋዞች ገዢ እያደረጉ በእነሱ ግዛት ላይ ሾመውባቸዋል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው በሰላም አምነው ለገቡት ግን የየራሳቸው መሪዎች እንዲያስተዳድሯቸውና እና የውስጥ አስተዳደር ነፃነታቸው እንዲጠበቅላቸው ነው የተደረገው። ያም ለነሱ መልካም ነበር።

አፄ ምኒልክ ንጉስ ጋኪ ሸሮቾን ከፋ ለዳግማዊ ምኒልክ እንዲገብር እና ግዛቱ እንዲከበርለት በተደጋጋሚ ቢጠይቁትም አልገብርም ብሎ ኃይለኛ ጦርነት ተነሳና የምኒልክን ጦር 9 ወር ገትሮ በመያዝ ከባድ ጉዳት አደረሰበት። በመጨረሻ ንጉሥ ጋኪ ሸሮቾ ተማረከና በሰንሰለት ታሰረ። ግዛቱም ለምኒልክ ጭቃሹሞች ተሰጠ። (አለቃ ገብረ-ሥላሴ፤ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ*፤ ገጽ 277)

ቀደም ሲል እንዳልኩት ፥ አጼ ምኒሊክ የወላይታ ንጉሥ የነበረውን ጦናን እንዲገብርላቸውና ደም መፋሰስን እንዲያስቀር ለመኑት። ጦና ፈቃደኛ አልሆነም። ለጥቂት ቀናት በጀግንነት ተዋግቶ ክፉኛ ቆስለና ተማረከ። ምኒልክ ጦናን ከመጨረስ ይልቅ ማሩትና ገባሪያቸው አድርገው ወደ ቀድሞ ስልጣኑና ግዛቱ መለሱት። (አለቃ ገብረስላሴ፤እላይ በተጠቀሰው. ገጽ 220) ጦና ባይዋጋም ኖሮ የምኒልክን ንጉሠ-ነገሥትነት እስከተቀበለ ድረስ ግዛቱን ማስተዳደር ይቀጥል ነበር። ምኒልክ ኢትዮጵያን እንደገና ባንድ ሉዓላዊ ንጉሠ-ነገሥት ሥር ሲያዋህዱ ጥበባዊ አመራራቸው እንደዚያ ነበር፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከምኒልክ የጦር አበጋዞች መካከል በሰላምም ይሁን በኃይል ኢትዮጵያ እንድትሰፋ እና አንድነቷ እንዲጠበቅ ምኒልክን የረዱት ከኦሮሞ ወታደሮቻቸው ጋር የኦሮሞ ባላባቶች መሆናቸው መታወስ ይኖርበታል። ለምሳሌ ንጉሥ አባ ጂፋር፣ የወሎው ንጉስ ሚካኤል፣ ራስ አሉላ ብጡል፣ ራስ ወሌ ብጡል፣ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (አባ ነፍሶ)፣ ፊታውራሪ ገበየሁ ጎራ እና ፊታውራሪ ሀብተ-ጊዮርጊስ ዲነግዴ ይጠቀሳሉ። ይህ እንግዲህ ራስ ጎብና ዳጨን ክዝርዝሩ ውስጥ ሳናስገባ እንኳ ነው። እነዚህ ሁሉ የጦር አበጋዞች ለኢትዮጵያ አንድነት ቆርጠው የተነሱ ነበሩ። ምክንያቱም እነ ጋሪ ባልዲ በጣልያን፥ እነ ቢስማርክ በጀርመን እና እነአብርሃም ሊንክን በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ታላቅ መስዋእትነትን ክፍለው የየሀገራቸውን አንድነት እንዳስጠበቁት ሁሉ እነዚህም ታላላቅ ኢትዮጵያውያን ክንጉሣቸው ጋር ተባብረው የሀገራቸውን አንድነት መጠበቅ ለኢትዮጵያ የሚጠቅማት መሆኑን በመገንዘባቸው በዘመናቸው ሳገራቸው ሊያደርጉላት የሚችሉት የላቀ ነገር ያ ነው ብለው ስላመኑበት ነው። ያሰነሱ ቁርጥ ውሳኔና ትብብር አጼ ምኒልክ በዘመነ መሳፍንት ተበጣጥሳ የነበረችውን ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ወደጥንት ቦታዋ ለመመለስ የነበራቸው ራዕይ ባልተሳካም ነበር።

አንዳንድ ሸማግሌዎች እንደሚሉት ዳግማዊ ምኒልክ በጠና በታመሙበት ወቅት አባቱን የወሎውን ራስ ሚካኤልን ንጉሠ-ጽዮን ብሎ (ጽዮንን ለማስታወስና የሰለሞናዊውን ሥርዎ-መንግሥት ለመጥቀስ ነው) ያነገሠው የምኒልክ የልጅ፣ ልጅ፣ ኢያሱ ለህዝብ ይፋ አልሆነም እንጂ በ1906 ዓ.ም በአዲስ አበባ በምስጢር ኢያሱ 4ተኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት ተብሎ ነግሶ ነበር። ንግሥናው ለህዝብ ይፋ ያልሆነበት ምክንያት በክርስቲያን ሥርዓተ-ንግሡ ላይ ኢያሱ ሙስሊሞች ፀሎት ሲያደርሱና ድቤ እየመቱ ነቢያቸውን መሐመድን ሲያወድሱ እንደሚያደርጉት ሁሉ ራሱን እየወዘወዘ ሙስሊም መስሎ ሰለነበር ነው። ይህ ታሪክ እውነት ይሁንም አይሁን ንጉሠ-ነገሥታዊ ሥልጣን ባይኖረው ኖሮ አባቱን ንጉሥ ብሎ ባልሾመም ነበር። ምክንያቱም ከንጉሠ-ነገሥትነት ያነሰ ሥልጣን ያለው ሰው ንጉሥ ብሎ መሾም አይችልም። ቢሾምም አይፀናም።

ኢያሱ የምኒልክን ልጅ ዘውዲቱንና ተፈሪ መኮንንን ወደ ሥልጣን ባመጣው መፈንቅለ-መንግሥት ከተገለበጠ በኋላ የዳግማዊ





አጼ ምኒልክ አያት የሸዋው ንጉሥ የንጉሥ ሣህለ-ሥላሴ የልጅ ልጅ-ልጅ የሆነችው ዘውዲቱ በ1909 ዓ.ም በምኒልክ ዙፋን ላይ ተቀመጠች። ተፈሪ መኮንን በነበረው የማስገደድ ኃይል ባንድ ጊዜ ልዑልና ንጉሥ ሆኖ አደገ። ንግሥት ዘውዲቱ ለተፈሪ መኮንን መንገዱን ጠርጋለት እስከ ዕለተ-ሞቷ እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ በሰለሞናዊው ዙፋን ላይ ቆየች እና ልክ እሷ ስታርፍ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ‹‹ንጉሠ-ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ-ሥላሴ፣ በእግዚአብሔር የተመረጠ አሸናፊው የይሁዳ አንበሳ›› ተብሎ ነገሠና 44 ዓመት ከገዛ በኋላ በ1967 ዓ.ም በህዝባዊ አብዮት ከሥልጣን ተወገደ የመጨረሻው የሰለሞን /ኣግኣዚ/ኦሮሞ/ ሥርወ-መንግሥት ንጉሠ-ነገሥት ሆነ። ኃይለ-ሥላሴ ባመዛኙ ኦሮሞ ነው። እናቱ የሺእመቤት ዓሊ ጋምጬ በአባትዋ በኩል የወረሂመኑ ኦሮሞ ናት። በአዲስ ግኝት መሰረት ይብረሁልሽ በተባለቸው ስልጤ-ጉራጌ እናትዋ ‹‹ቂቶ›› ትባል የነበረችው አያትዋ ወ/ሮ ወለተ-ጊዮርጊስ የወሎው-ኦሮሞ ነቢይ የሼሕ ሁሴን ጅብሪል ልጅ ናት።( )

ይህ ማለት ሼኽ ሁሴን ጅብሪል የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ቅድመ-አያት ናቸው ማለት ነው። ቅድመ አያቶቹ ሙስሊሞች የመሆናቸው ይህ እውነታ እስከ ዕለተ-ሞቱ ድረስ ትልቅ ምሥጢር ሆኖ እንዲያዝ ተደርጓል። የቀዳማዊ እና የዳግማዊ ምኒልክን ፈለግ ተከትሎ ራሱን ‹‹በእግዚአብሔር የተመረጠ፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ ድል አድራጊ የይሁዳ አንበሳ›› ብሎ የሰየመ በመሆኑ እስላምነቱ የሰለሞናዊ-ይሁዲያዊ - ክርስቲያን ዙፋኑን ይጎዳል ብሎ ስለሰጋ ነው። ወንድ ቅድመ-አያቱ ባባታቸው በኩል ጉዲሳ የሚል የኦሮሞ ስም ነው ያላቸው። በኋላ እንደተረጋገጠው ጉዲሳ አሳዳጊያቸው ሲሆኑ ትክክለኛ ቅድመ-አያታቸው ግን ከትግራይ ተንቤን ወደ ሸዋ ዶባ የመጡ ወልደ-መለኮት የሚባሉ ትግሬ ነበሩ። ዶባ መጥተው የአንድ ባላባት ልጅ አገቡና ደጃዝማች ወልደ-ሚካኤልን ወለዱ። ደጃዝማች ወልደ-ሚካል ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ እያት ከንጉሥ ሣህለ-ሥላሴ ልጅ ከልዕልት ተናኜ ወርቅ ራስ መኮንንን ወለዱ (የአጼ ኃይለ-ሥላሴ ባለቤት እቴጌ መነን አስፋውም እንዲሁ ከልጅ ኢያሱ በቅርብ የምትዛመድ የወሎ ኦሮሞ ደም ያለባት ናት ተብሎ ይታሰባል። የአህቱ የወይዘሮ ስሂን ሚካኤል ልጅ ናት።

እስካሁን ከቀረበው ሀተታ ተነስተን የሚከተለውን መደምደም እንችላለን፤ አማራው ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-መንግሥትም ሆነ እንደ ግለሰብ ንጉሠ-ነገሥት/ንግሥተ-ነገሥት/ በመሆን ወይም የአማራ ስርወ-መንግሥት በማቋዋዉዋም ፈጽሞ አልገዛም። ይህም ሲባል በራሱ ክፍለ-ሀገራት የራሱ ነገሥታት አልነበሩትም ማለት አይደለም። በተለያዩ ዘመናትና ግዛቶች ለራሱ ለአማራ፣ የአማራ ነገሥታት ነበሩት። የቅርብ የቅርቡን እንኳዋን ብንተወው፥ የዛሬ 2000 ዐመት በአንድ ጎጃም ላይ በጣና አካባቢ ብቻ 4 የአማራ ንጉሦች ነበሩ።:-- በቅድመ-አባቱ በደሸት ከተማ የጎንጂ እና ጉንዳጎንዲት ንጉሥ የነበረው አጎጃ ጀባን፥ የጣና ደጋና የአካባቢው የነበሩ ሶስት ነገሥታት ወንድማማቾች፥ አቦል፥ ቶና እና በረካ የሚባሉ ነበሩ። ቡና ጠጪዎች አቦል፥ ጦና እና በረካ እያሉ የሚጠጡት ምናልባት እነዚህን ታላላቅ ነገሥታት ለማስታወስ ይሆናል። አጎጃ ጃባንን እና እነዚህን ሶስት የአማራ ንጉሦች ታላላቅ የሚያደርጋቸው ህዝባችውን በፍትህ እና ባስተዋይነት ማስተዳደራቸው ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት ግዛት ተነስተው የመሲሁን መወለድ የምታበስረውን ኮከብ ተከትለው ገፀበረከት ይዘው ቤተልሄም ድረስ ሄደው ለዐለሙ መድህን ለእየሱስ ክርስቶስ ከሰገዱለት 12 ኢትዮጵያውያን ወንድማማች ጠቢባን ነገሥታት መሃል በመሆናቸው ነው። ከዚህ በተቃራኒ ያለው ጭቅጭቅ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚዘወር የፈጠራ ታሪክ ነው። ያም ሆነ ይህ አማራ የጦር ኀይልም የፖለቲካ ስልጣንም በፍፁም አልነበረውም፣ በሰለሞናዊ-ኦሮሞ ሥርወ-መንግሥት ውስጥ አስተዳዳሪና ዳኛ ሆኖም አልሠራም ማለት አይደለም። በፊት እዳስረገጥኩት፥ በርግጥ አማሮች ንጉሦችን ደግፎ የማውጣት እና ዘርጥጦ የማውረድ የጦር ኃይል ችሎታ ነበራቸው። ከአመኑበት፥ ንጉሥ ለማንገስ እና ለመሻር አጋዥ ኃይሎች ነበሩ። በኦሮሞ ንጉሣውያን ቤተሰቦች ለሚመራው የኢትዮጵያ መንግሥትና ለፍትሕ ሥርዓቱም በነበራቸው የወታደራዊና የትምሕርት ችሎታ ብዙ አበርክተዋል። በየግዛታቸው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ለንጉሠነገሥቱ ተጠሪ የሆኑ የራሳቸው የአማራ ንጉሦች ቢኖሩአቸውም ፥ ባብዛኛው በራሳቸው ምርጫ ፀሀፍት ፥ ሊቃውንት፥ ባለቅኔዎች፥ ገበሬዎች፣ ባለእጆች፤ ነጋዴዎች፣ አዝማሪዎች፣ ካህናት ፥፣ ዳኞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ምሁራን እና መምህራን ነበሩ። ይህ እውነታ





አማሮችን የገዢው መደብ አባላት ወይም ልሂቃን እንደነበሩ አያስቆጥራቸውም።

ከአስራ አራት ዓመት በፊት ወደ ጎጃም ስሄድ አባይን እና ደጀንን አልፈን ግርግዳቸው በጭቃ፣ ጣራቸው በሰንበሌጥ የተሰሩ ቤቶች ያሏት አንዲት ሥልጣኔ ያልጎበኛት የምትመስል መንደር ደረስንና ‹‹ደብረ-ማርቆስ ለመድረስ ምን ያህል ይቀረናል?›› ስል ሾፌሬን ጠየቅሁት። አየት አደረገኝና ‹‹ማርቆስ ይቺ ናት›› አለኝ።

‹‹ደብረ-ማርቆስን ማለቴ ነው›› አልኩት።

"እኮ! ይቺ ናት ደብረ-ማርቆስ" ሲል መለሰልኝ። አማራው እንደ ሥርወ-መንግሥት ኢትዮጵያን ሲገዛ ኖሯል ብዬ እንደአብዛኛው ሕዝብ አስብ ስለነበር ዘመናዊ ሕንፃዎች እና በርካታ መኪናዎች የሚርመሰመሱባቸው አስፋልት መንገዶች ለማየት ጠብቄ ነበር። ‹‹ተሞኘሁ!›› ስል አጉመተመትኩ። ‹‹ምን ጠብቀው እንደነበር አውቃለሁ››፤ ሾፌሩ አስተያየቱን ሰነዘረ፤ ‹‹እኔም መጀመሪያ ደብረ-ማርቆስ ስመጣ እንዲሁ ነበር የተሰማኝ›› አለ።

‹‹ኗሪዎቹ ያገሪቱ ገበሮች ናቸው። አማሮች ናቸው። እንዴት ይህን ያህል ጎስቋሎች ሆኑ!›› ተገረምኩ። ‹‹ትርኪ-ምርኪ ናት!›› መንዝን፣ ተጉለትን፣ መርሐ-ቤቴን፣ ቡልጋን፣ ጋይንትን፣ ላስታን፣ ጎንደርንና አማራ ሳይንትን ቢያዩ ምን ሊሉ ነው! የባሱ ናቸው። ሰው ሊኖርባቸው የማይችል፣ በድህነት የተመቱ ናቸው። እኔ በነዚህ ቦታዎች አልኖርም። አብዛኛው ሰው ባዶ እግሩን ነው የሚሄደው። አንዲት ልብስ ካለችው እሷኑ እላዩ ላይ ብጥሥጥስ እስክትል ይለበሳታል። ጥቂት የአማራ ልሂቃን ሥልጣን ላይ አሉ ማለት ሰፊው የአማራ ሕዝብ አልፎለታል ማለት አይደለም። በፍፁም! ሰፊው የአማራ ሕዝብ የስቃይ ኑሮ ነው የሚገፋው›› አለ። ትክክል ነበር።

ያ ሁኔታ ስለ አማራው ሕዝብ ለነበረኝ አስተሳሰብ መለወጥ አንድ ምክንያት ሆነ። በርግጥ ኢትዮጵያን የሚገዙ ከሆኑ ለምን ይህን ያህል ክልክ ያለፈ ጎስቋሎች ሆኑ? ስል ጠየቅሁ ራሴን። ይህ ጥያቄ መልሱን ራሴ እንድፈልግ አነሳሳኝ። በዚህ ጽሁፍ እንዳያችሁት አሁን መልሱን አግኝቸዋለሁ ብዬ አምናለሁ።

በ1967 ዓ.ም የአጼው ሥርዓት ከተወገደ በኋላ እንኳ ርእሰ-ብሔር ሆኖ የመራ ሙሉ በሙሉ አማራ የሆነ አንድም ግለሰብ የለም። ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ትግሬ፤ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ኦሮሞ፣ የቀድሞው ፕሬዝዳንቶች መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባንድ በኩል ኮንሶ ማለትም ኦሮሞ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ ኦሮሞ፣ በፊት ፕሬዝዳንት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው መለስ ዜናዊ በወላጆቹ ትውልድ ኤርትራዊ ነበር እንጂ ከነዚህ አንዳቸውም አማራ አልነበሩም። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአድዋ የተወለደ ሙሉ በሙሉ ኤርቴራዊ የሆነ ሰው ነው። አዲስ የተሾሙት የይስሙላ ፕሬዝዳንቶችም ቢሆኑ ግርማ ወልደ-ጊዮርጊስ ቅይጥ ብሔረ-ሰብ ሲሆን፣ የአሁኑ ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ኦሮሞ ነው። ስለዚህ ‹‹አማራ ገዛን፤ ጨቆነን›› የሚለው ጩኸት መሰረተ-ቢስ ውንጀላ እና ህዝቡን ለማነሳሳት እና ራሳቸውን ለማጠናከር የፈለጉ ፖለቲከኞች የፈጠሩት ‹‹ማታገያ ጠላት›› ነው። የእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች እንዲህ ዓይነቱን ፈጠራ "bogeyman" ይሉታል፤ የአማርኛ አቻው የልጆች ማስፈራሪያ ‹‹ጭራቅ›› እንደ ማለት ነው። በልጅነቴ ትንሽ ሞልቀቅ ብዬ እናቴን ሳስቸግራት አንድ ጋሼ አበበ የሚባል ሰውዬ ‹‹ ጎረዳማንን ነው የምጠራው!›› ሲለኝ አብረክረክ ነበር። ።ጎረደማን የሚለውን ቃል ገና ሲጠራብኝ ሞት የተጠራብኝ ያህል ስለምፈራ ወዲያውኑ አዋቂዎቹ የሚፈልጉትን ፀባይ አሳይ ነበር። ቀድሞ ነገር አማራን ማስፈራሪያ ማድረግ እንደገና ወደ ሥልጣን የሚያወጣ መስሏቸው ከሆነ አስቂኝ ነው። ያም ሆነ ይህ አማራ ሥልጣን ቢኖረው እንኳ እንዲገለል ከተደረገ ከ40 ዓመት በላይ ሆኖታል። የሚያሳዝነው አማሮች የውጭ ዜጎች የሆኑ ያህል በገዛ አገራቸውና በገዛ ርስታቸው ከግራም ከቀኝም በፖለቲካ ጥላቻ ከመኖሪያቸው እያፈናቀሉ ሲያሰቃዩዋቸው ራሳቸውን ጥንት የኢትዮጵያን ዳርድንበር በውትድርና ያልጠበቁ ያህል አሁን ለራሳችው መከላከል እንኳ ያልቻሉ መሆናቸው ነው።

አማሮች የራሳቸው ሥርወ-መንግሥት ሳይኖራቸውና እንደ ሌሎቹ ርዕሰ-ብሔር ሳይሆኑ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሚናቸው በዋናነት መንግሥትን መጠበቅና ያገሪቱን የግዛት አንድነት እና ሉዓላዊነት ማስከበር፥ ከዚህ ሲያልፍም በየግዛታቸው በንጉሥነት፥ በአርሻ፣ በንግድ፣ በአስተዳደር፣ በቤተ-ክህነት እና በባህላዊ ትምህርት ቤቶች በመምህርነት ማገልገል ሆኖ ሳለ ‹‹ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-





መንግሥት በጭካኔ ገዝተዋል›› እያልን ያን ያህል እንዴት ልንዋሽ ቻልን?

ለዚህ መደናገር አራት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ቋንቋቸው ነው። በተረትና ምሳሌዎች፣ በዘይቤዎች፣ በቅኔ፣ በስምና ወርቅ አባባል በኅብር አነጋገር የበለፀገው አማርኛ ቋንቋ። ይህ ቋንቋ ታዋቂ የሆነው የውትድርና እና የንግድ ተግባራቸውን ለማሟላት መላ ኢትዮጵያን ዳር እስከዳር ያካለሉ በነበሩ በአማራ ወታደሮችና በነጋዴዎች ነው። በተጨማሪ በሁለቱም በዛጉዬ እና በሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥቶች ነገሥታት ከዚያም አልፎ በ አፄ ዮሐንስ እና በወቅቱ የትግሬ መንግሥት ጭምር የሥራ ቋንቋ ሆኖ ስለሚ ሠራበት ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ አማርኛ ከአሥራ ሁለተኛው፣ አሥራ ሦስተኛውና አሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመናት ጀምሮ ነው በሦስት አበይት ንጉሠ-ነገሥቶች በላሊበላ፣ በይኩኖ-አምላክ እና በዳግማዊ ኢያሱ በይፋ የሥራ ቋንቋ ተደርጎና ፀድቆ እየተሠራበት ያለው። ላሊበላ የላስታ-አገው ተወላጅ ሲሆን ይኩኖ-አምላክ እና ዳግማዊ ኢያሱ ደግሞ ሁለቱም የኦሮሞ ዝርያዎች ናቸው። አማርኛ ብሔራዊና መንግሥታዊ ቋንቋ መሆኑ ፋይዳው ቁልጭ ብሎ ስለታያቸው ነው ያንን ያደረጉት። በተለይ ዳግማዊ ኢያሱ ግዕዝ በቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ እንዲወሰንና አማርኛ ግን በመላ ግዛቱ ለሁሉም መንግሥታዊ ሥራዎች መገልገያ እንዲሆን በሕግ ደንግጓል። እነዚህ ንጉሠ-ነገሥታት አንዳቸውም አማራ እንዳልሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ ‹‹የአማራ ነገሥታት አማርኛን አማርኛ ተናጋሪ ባልሆኑ ሕዝቦች ላይ ጫኑባቸው›› ብሎ መደምደም ጨርሶ አያስኬድም። ስዚያውም አማራውን ወክሎ አንድም የአማራ ንጉሠ-ነገሥት በሥልጣን ላይ ባልወጣበት ሁኔታ።

የተለያዩ ብሔረሰቦች አባላት በኢትዮጵያ ውሰጥ አስተዳዳሪዎች እየሆኑ ለመሥራት አማርኛ ተማሩ። ብዙዎቹ ሥራቸውንና ማኅበራዊ ደረጃቸውን አስጠብቀው ለመኖር ከአማራ ጋር መቀላቀልና ራሳቸውን አማራ ማድረግ መረጡ። አማራ እንደ ገዢ መደብ የተቆጠረበት ሁለተኛው ምክንያት አማራነትና ክርስቲያንነት አንድ ቃል የሆኑ እስከሚመስል ድረስ እማሮች የተዋሕዶ እምነትን ከአግአዚ/ኦሮሞና

ዛጉዬ ነገሥታት ጋር መጋራታቸው ነው፡፡ ሦስተኛው ምክንያት አማሮች ኢትዮጵያን እንደ ሥርወ-መንግሥት መላዋን ኢትዮጵያን አስመግዛታቸው በወጉ አስመታወቁ ነው፡፡ አራተኛውና የመጨረሻው ምክንያት ከላይ ጠቆም እንደተደረገው ሆን ተብሎ የሚሠራጭ ውኸምብር እና የፖለቲካ ሰዎች አማራን እንደ የጋራ ጠላት አስቆጥረው ሠፊውን ሕዝብ በመቀስቀስና በማስተባበር የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት ያደርጉት የነበረው እንቅስቃሴ ነው፡፡ አማሮች በዚህ የተነሳ ስስቆቃ መዳረጋቸው፣ በተለያዩ ጊዜያት እንደ ገዢ መደብ እየታዩ ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸውና መለቃየታቸው ያፀፅታል፡፡ ብዙሃኑ አማራ ግን ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የገዢ መደብ ሳይሆኑ እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ዜጎች በውትድርና እና በተለያዩ ሙያዎች ተሰማርተው ደፋ ቀና ሲሉ የኖሩ ናቸው፡፡

የአማራን ትክክለኛ ማንነት በተመለከተ አንዳንድ የአውሮፓ ምሁራን ተብዬዎች እንደሚሉት አማሮች ሴማውያን አይደሉም፡፡ ኦሮሞና አማራ ካንድ ምንጭ ነው የተቀዱት፡፡ ቀደም ሲል እንደተረጋገጠው ኦሮሞና አማራ በዘርም አንድ ናቸው፡፡ ኦሮሞዎች ኩሻውያን ከሆኑ አማሮች እንዴት ነው ሴማውያን የሚሆኑት? አንድ ሰው ቋንቋቸውን ሴማዊ አድርጎ ስለመደበው አማሮችም ሴማውያን ተደርገው የሚመደቡ ከሆነ ግልብ ምደባ ነው፡፡ ቋንቋ ዘርን አይወስንም፤ ጎሳን ነው እንጂ፡፡ ቀድሞ-ነገር አማርኛን ‹‹ሴማዊ ቋንቋ›› ነው ብሎ መመደቡ አጠያያቂ ነው፡፡ ለምሳሌ እንደ ግዕዝ ባሉ ሴማዊ ቋንቋዎች ውስጥ የማይገኙ ድምጾች በአማርኛ

እና በኦሮምኛ ውስጥ አሉ፡፡ እነሱም ‹‹ h € ' I µ Ê Û ›› ናቸው፡፡ እነዚህን በመሰሉ የአማርኛና የኦሮምኛ መሰረታውያን ድምፀ-ልሳናት ላይ የተደረገው ጥናት እንደሚያብራራው አማርኛ ከግዕዝ ይልቅ ለኦሮምኛ ነው የሚቀርበው፡፡ እነዚህ ድምፀ-ልሳናት የአማርኛ እና የኦሮምኛ ናቸው እንጂ የግዕዝ አይደሉም፡፡ እነዚህ የፊደላት ድምፆች የኩሽ ቋንቋዎች መስኪያና መሰረታውያን ጠባያት ናቸው፡፡ ወደፊት በአማርኛ እና በኦሮምኛ ቋንቋዎች ላይ የሚደረግ ጥልቅ የንፅፅር ጥናት አዲስ ውጤት ይሰጠን ይሆናል፡፡

የሙዚቃው ቃና /melody/ ወይም ባለ አራት ቅኝቱ የአማርኛና የኦሮምኛ ሙዚቃ እንኳ ከአረቡ ወይም በእብራይስጥ ምንም





ግንኙነት የለውም፡፡ የአማርኛና የኦሮምኛ አልፎም የኑቢያ (ከሥር ከመሠረቱ ጥቁሮች የሆኑ ኩሻውያን ሱዳኖች) ሙዚቃዎች ግን ተመሳሳይ ቅኝት ነው ያላቸው፡፡ የአረብና የእብራይጥ ሙዚቃዎች ግን አማሮችንና ኦሮሞዎችን ጨምሮ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ጆሮ እና ልቦና አይመስጡም፤ አይጥሙም፡፡ የኦሮሞና የአማራ ሙዚቃዎች ግን ተመሳሳይ ቅኝት እና ምት አላቸው፡፡ ይህም ሁለቱ ህዝቦች አንድ ዓይነት የነገድ እና የባሕል ዳራ ያላቸው ስመሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡

አማሮች ኩሻውያን ሆነው ሳለ ለምን ሴማዊና ሐበሻ ተብለው ተፈረጁ? ምክንያቱ ምንጫቸው እሥራኤል ከሆነ እግአዚያን ጋር ስለተምታቱ ነው፡፡ የንጉሥ ሰለሞን እና የንግሥት ሳባ ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ ከሦስት ሺ አመታት በፊት አባቱን ለመጠየቅ ወደ እሥራኤል ሄዶ የአይሁድን ሃይማኖትና ባሕል እየተማረ ጥቂት አመታት ከቆየ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ 40,000 ጠንካራ አይሁዳውያን እና በጋዛ የሚኖሩ ኢያቡሳውያን ወንዶችን ይዞ መምጣቱ መታወስ ይኖርበታል፡፡ ቀዳማዊ ምኒልክ እነዚያን 40,000 እሥራኤላውያን ‹‹አግአዚ/ነፃ አውጪ/›› ብሎ ስይሞ ሥልጣን ስለሰጣቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለ3,000 ዓመታት የተጋቧቸውን ኢትዮጵያውያንን ማንነት ማስለወጥ አልቻሉም እንጂ በኢትዮጵያ ሃይማኖት፣ ቋንቋ ፖለቲካ እና ባሕላዊ ገጽታዎች ላይ ተፅእኖ ማሳረፍ ችለዋል፡፡ እነዚያ 40,000 እሥራእላውያን ወንዶች በኢትዮጵያ ስፍረው ከአገር በቀል ነዋሪዎቹ ኩሻውያን እንስቶች ጋር ተጋቡ፡፡ ኢትዮጵያ በዋናነት ኩሻዊት አገር ነበረች፤ የኩሽ ምድር ትባልም ነበር፡፡ በዚህም ከእሥራኤል የመጡት 40 ሺ ወንዶች በሶስት ሺ ዓመታት የኢትዮጵያ ቆይታቸው ‹‹ሴማዊ ደማቸውን›› አጥተው ‹‹ኩሻዊ ደም›› ያዙ፡፡

በኢትዮጵያ የሚኖሩ አግኣዚዎች የአይሁድ እምነታቸውን ጠብቀው ከመያዛቸው በቀር በአካል ከተቀሩት ኢትዮጵያውያን ምንም የማይለዩ የሆኑት ለዚህ ነው፡፡ በርግጥ ቀዳማዊ ምኒልክ ቋንቋቸውን ግዕዝን የሥርወ-መንግሥቱ የይፋ ቋንቋ ስላደረገው አባብሶባቸዋል፡፡ ከ2,000 ዓመት በፊት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ ጋር ተያይዞም ግእዝ በአድገቱ ቀጥሏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ተተረጎመበት፤ የእግዚአብሔር ቃል ይሰበክበት ጀመር፤ ቅዱስ ያሬድ መዝሙራቱን ቀመረበት፤ በሌላ አባባል ግዕዝ የቤተክርስቲያን ቋንቋ ሆነ፡፡ ባሕላዊ እምነታቸውን ጠብቀው ከኖሩት ከኦሮሞዎች ጋር ሲነፃፀሩ በርካታ አማሮች ወደ

ክርስቲያን ተዋሕዶ ሃይማኖት ተሰወጡ። ብዙ ቁጥር ያላቸው ግእዝን እየተማሩ ቀሳውስት ሆኑ። በዚህ ሳቢያ በሁሉ ነገራቸው በዘራቸው ሳይቀር ሴማውያን መሰሉ። ሀቁ ግን እንደ ሥጋ ዘመዶቻቸው እንደ ኦሮሞዎቹ ኩሻውያን መሆናቸው ነው። ልክ ገዢዎቹ አግአዚዎች አማርኛን የመንግሥታቸው የሥራ ቋንቋ አድርገው ስለሠሩበትና የተወሰኑ አማሮች ወታደሮች ሆነው መንግሥቶቻቸውን፣ ሃይማኖታቸውንና ያገራቸውን ዳር ድንበርና አንድነት ለመጠበቅና ለማስከበር በመላ አገሪቱ ደፋ-ቀና በማለታቸው የገዢው መደብ አባላት ተደርገው ሲታዩ እንደኖሩት በማንነታቸውም እንደ ሴማዊ ተቆጠሩ።

‹‹ሀበሻ›› የሚሰው ስም ወይም አምደ-ቃል አማሮችን አይወክልም። ይህንን ነጥብ ለማስረገጥ መነሻውን መዳሰስ ያስፈልገናል። ቃሉ መስሎ እንደሚታየው እዎንታዊ ፍቺ ያለው አይደለም። ይልቅስ የወረደ ትርጉም ነው ያለው። መጀመሪያ የተጠቀሙበት ፈላሻ አይሁዶች ሲሆኑ አጠቃቀማቸውም አግአዚያን አይሁዶችን ለመሰደብ ነበር። ሁኔታው ባጭሩ ሲቀርብ የሚከተለውን ይመስላል፤ በ598 ዓ.ዓ ባቢሎናውያን እሥራኤልን በወረሯት ወቅት በርካታ እሥራኤላውያን ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አግአዚዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ 400 ዓመት ሆኗቸው ነበር። አግአዚዎች ከኢትዮጵያውያን ጋር እየተጋቡ በባሕል ተመሳስለውና ራሳቸውን ኢትዮጵያውያን አስመስለው መኖራቸውን አዲሶቹ መጪዎች አይተው ‹‹ካልተገረዙ ጋር ተቀላቅለው አይሁድነታቸውን አርክሰዋል›› በሚል ነቀፏቸው። በዚህ ምክንያት ‹‹ሀበሻ›› የሚል ስም አወጡላቸው። ትርጉሙም ‹‹ድቅል፣ ንፁህ ያልሆነ ወይም የተካለሰ ›› ማለት ሲሆን በተራዘመ ፍቺው ደግሞ ‹‹የተበከለ፣ የቆሸሸ›› ማለት ነው። አግአዚዎቹ ደግሞ በአፀፋው አዲስ መጤዎቹን ‹‹ፈላሻ›› አሏቸው። ‹‹ስደተኛ›› ማለት ነው። በተራዘመ ፍቺው ደግሞ ‹‹አገር-አልባ›› ማለት ይሆናል። ይህ ነው ሁኔታው። ይህ አንግዲህ በሁለቱ የአይሁድ ቡድኖች መካከል የተፈፀም አተካራ ሲሆን ከአማራ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። አማሮች አበሾች አይደሉም። ራሱን እንደ ሀበሻ የሚቆጥር ማንኛውም አማራ ካለ ታሪኩን የማያውቅ ብቻ ሳይሆን ራሱን የሚዋርድም ነው። ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚሰው ስም ኦሮሞን + አማራን እና ሁሉን ኢትጵያውያንን የሚያቅፍ እና የታላቁን ፃድቅ አባታችንን የ‹‹ኢትዮጵ››ን መጠሪያ የያዘ በመሆኑና ፍቺውም ‹‹ለእግዚአብሔር





**የሚበረከት የቢጫ ወርቅ ሥጦታ›› ማለት ስለሆነ እኛ ሁላችንም ‹‹ኢትዮጵያውያን›› ተብለን ነው መጠራት ያለብን። ከ‹‹ኢትዮጵያ››** በላይ የሚያኮራ ታላቅ ስም ከቶ የለምና!።

ፈላሻዎቹ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹን የአይሁድ ሰፋሪዎችን አግአዚዎቹን ሴማዊነታቸውን ትተው ኩሻውያን ወይም ኢትዮጵያውያን በመሆን ሀበሻ ሆነዋል ሲሉ ትክክል ነበሩ። ቀደም ብዬ እንዳልኩት ከማይታወቅ ጊዜ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ታሪክ የምናምንበት ከሆነ በኖህ ዘመን ከደረሰው የጥፋት ውኃ በኂላ ኩሽ በኢትዮጵያ ከሰፈረበት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን የኩሽ ህዝብ ነበር የምንባለው። አግአዚንና ፈላሻዎችን ጨምሮ የተሰያዩ ሴማውያን ሕዝቦች በአነሰተኛ ቁጥር ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ከኢትዮጵያውያን ጋር እየተቀላቀሉ በኩሻዊነት ውስጥ እየሰመጡ ቀርተዋል። በሌላ አባባል አዲስ መጪዎቹ ሴማውያን በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ውስጥ ጠፍተዋል ወይም ተውጠዋል። በባሕሩ ውስጥ ጠብታ ውሃ ሆነዋል ማለት ነው። ስለዚህ በባሕሩ ውስጥ ሟሙ እንጂ ባሕሩን አልበከሉትም።

አማሮች ከመነሻቸው ከጎጃም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ኩሻውያን ናቸው። ካንዳንድ ሴማውያን ጋር መዳቀል ቢኖርም ኩሻዊነታቸውን ቅንጣት አልለወጠውም። ከጥንት ከመነሻቸው እንደነበሩት አሁንም ያው ኩሽ ናቸው። ሴማዊነቱ ሙሉ በሙሉ ያልተረጋገጠውን ቋንቋ እንደ መስፈርት ወስዶ **‹‹አማርኛ ሴማዊ ስለሆነ አማሮች ሴማውያን ናቸው››** ብሎ መደምደም ስህተት ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ ቋንቋ ሁል ጊዜ የሰውን ዘር እንደማያረጋግጥ እስተውሰናል። ለምሳሌ በርካታ አፍሪቃውያንና አፍሪቃ-አሜሪካውያን እንግሊዝኛ፣ ስፓንኛ እና ፈረንሳይኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ። ቢሆንም ዘራቸው አንግሎ-ሳክሶን፣ ሂስፓኒክ እና ፈረንሳይ ነው ብለን አንደመድምም። ቋንቋቸው ሴማዊ ቢሆን እንኳ ለአማሮችም ልክ እንዲሁ ቋንቋቸው ሴማዊ ስለሆነ እነሱም ሴማውያን ናቸው አንልም።

ያለ አማሮች ወታደራዊ ድጋፍ፣ አግአዚ/ሰለሞናዊ እና በኂላም አግአዚ/ኦሮሞ ስርወ -መንግሥታት ገና ከመነሻቸው በተንኮታኮቱ ነበር። ያ ብቻ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ነፃነት ሳይቀር አደጋ ላይ ይወድቅ ነበር። ለዚህ ተግባራቸው ኢትዮጵያውያን በሙሉ የአማሮች

ውስታ አስባቸው፡፡ አማሮች የኢትዮጵያ ነፃነት ጠባቂዎች ሆነው ባከናወኑት የመስዋዕትነት ተግባር ባንፃራዊ መልኩ ይበልጥ ጠንከር ያለ የኢትዮጵያዊነት ስሜት አዳበረዋል፡፡ ስዚህ ነው አማሮች ዘረኝነትን ከሚያራምዱ ነገዶች በተቃራኒው ከምንም ነገር በፊት ከአማራነትም በላይ ኢትዮጵያዊነት እጅግ ጎልቶ የሚበልጥባቸው፡፡

አንዳንድ ሰዎች አንኮበሬ የሚባሉትን ከጠቅላላው አማራ ጋር ያምታታሉ፡፡ ሸዋ ውስጥ ከሚገኘው ከአንኮበር በመነሳት አንኮበሬዎች የሚባሉት የሸዋ ልዑላን እና ነገሥታት ፈጽሞ ራሳቸውን እንደ አማራ አይቆጥሩም ወይም የአማራ ሥርወ-መንግሥት እንወክላለን ብለው አያውቁም፡፡ ራሳቸውን የሚቆጥሩት የአግአዚ-እስራኤል-ሰለሞናዊ ሥርወ-መንግሥት ዝርያ አድርገው ነው፡፡ አንኮበሬዎች አማሮች ቢሆኑ እንኳ አሁን በሥልጣን ዐታቸው ላይ የሉም፡፡ ከ42 ዓመት በፊት አፄ ኃይለሥላሴ ከስልጣን ሲወርዱ ከፖለቲካው ተወግደዋል፡፡ ስለዚህ እነሱ በተጨባጭ ማስረጃ አጥፍተዋል ከተባለ የነሱ መጥፎ ሥራ ነው የሚባለውን መቆፈር ለዛሬው ችግራችን ምንም መፍትሄ አይሆንም፡፡

አንዳንዶቻችን ስለ ገዳ ሥርዓት ማዳነቅ እና መከራከር እንወዳለን፡፡ ባንድ ወገን እውነታችንን ነው፡፡ ህዝብን በሚወክሉ በህገር ሽማግሎች በጎ ፍቃድና ከትውልድ ትውልድ በተላለፈ ደንብ የሚመረጡት ጎልማሶች እያንዳንቸው ግዛታችውን ለስምንት ዐመታት አስተዳድረው ጊዜያቸው ሲያበቃ ያለ ደም መፋሰስ መሰናበት እውነተኛ ዲሞክራሲ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከአሜሪካ ዲሞክራሲ ጋር መሳ ለመሳ ይራመዳል፡፡ "ከስልጣኔ ሞት ብቻ ይገላግለኝ" ለሚሉት የአፍሪካ መሪዎችም ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡ ይህን ስርአት የፈለሰፉት አባቶቻችን ክብር ይገባቸዋል፡፡ ዛሬ ላይ ሆነን ግን የገዳ ሥርዓት ጊዜ አላለፈበትምን? በምርጫ መስተዳደር ደስ የሚለውና የሚያኮራ አንዱ የገዳ ስአርት ገጥፅታ ሲሆን ሌላው ገፅታው ግን ያነጋግራል፡፡ ሙሉው የገዳ ስርአት ዛሬም በ21ኛው ክፍለ-ዘመን በኢትዮጵያ ሊሠራ ይችላልን? ባሁኑ ወቅት የገዳ ሥርዓትን ለወግ እና ለማስታወሻ ሳይሆን፥ በተሟላ መልኩ ወይም ገፅታው የሚሠሩበት ኦሮሞዎች ስንቶች ናቸው? እነሉስ እነማን ናቸው? የትስ ናቸው? የገዳ ሥርዓትን ከእነ ሙሉ ገፅታው መተግበር ጊዜ ለማሳለፍ ሽርሽር መውጣት አይደለም፡፡ ድንቅ ከሆነው እና በአርኣያነት ከሚታየው





ዴሞክራሲያዊነቱ ባሻገር ዘረፋን፣ ጦርነትን፣ ወረራንና ግዛት ማስፋትትን ያበረታታል፤ ምርኮኞችን መስለብን እንደ ጀግንነት ይቆጥራል፡፡ አዲሱ ሉባ ካለፈው የተሻለ ሆኖ ለመገኘት እነዚህን ድርጊቶች መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያና የዐለም ሁኔታ እውነታ ግን ይህን አይፈቅድም፡፡ ስለዚህ እኛ ተምረናል የምንለው ሰዎች ከገዳ ስርዐት መጥፎውን ትተን መልካሙን፥ ማለትም የዲሞክራሲ ባህሪውን እና ጥበትን አስመውደዱን ብቻ አድንቀን እነሱን እንቀስማልን፡፡

የድሮውን ለማውሳት ያህል ግን ፥ ኦሮሞዎች በኬንያ፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲ፣ በማሊ፣ በኒጀር እና በናይጄሪያ ዛሬ የሚገኙት ለምንድነው? የገዳው አዳዲስ ወጣት ሉባዎች አዳዲስ ግዛቶችን ለመያዝ ባደረጉት እንቅስቃሴ ነው፡፡ የገዳ ተፈጥሮው ወይም አንድ መሰረታዊ ባህርዩ በስፋት ሆነው ሳይጣበቡ መኖር ነው፡፡ ‹‹ኦሮምያ›› በተባለች አንዲት ጠባብ ክልል መወሰን የገዳ ባህርይ አይደለም፡፡ የኦሮሞ ቀልብ እና መንፈስ በጠባብ ቦታ መታጨቅና መታሰር አይወድም፡፡ ስገዳ ሥርዓት የሚሟገቱ ከሆነ ከጠባብነት በተቃራኒው ያለውን የሰፊነት ጠባዩን መቀበል ይኖርብዎታል፡፡ ኬኩን ሊያስቀምጡትም ሊበሉትም አይችሉም፡፡ ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ከጠባብ ክልል እና ከሰፊው አገር ምረጥ ቢሉት ሰፊውን ነው የሚመርጠው፡፡ ምክንያቱም ለዘመናት በገዳ ሥርዓት የተቃኘው ተፈጥሮው እንደዚያ ነዋ!

ከፍ ሲል የትልቁ የኢትዮጵ ፥ ዝቅ ሲል የነቢዩና የፈላስፋው የደሸት ልጆች የ ሆኑት እውነቶኞቹ ኦሮሞዎች አገራቸው ድፍን ኢትዮጵያ የኔ ናት ብለው ያስባሉ ። ኦሮምያ ብቻ በምትባል ጠባብ ስፍራ መወሰን አይሹም፡፡ መጣበብ እና መጨነቅ ባህሪያቸው ስላልሆነ፡፡ ኦሮምያ ተብሎ የተሳለ አንድ ካርታ ዐይቼ ነበር፡፡ ይህን ካርታ በተመለከተም የምለው አለኝ፤ ካርታው ጎጃምንና ጎንደርን አላካተተም፡፡ ለምን? ኦሮሞ ከ3,500 ዓመት በፊት ከአማራ ጋር የተፈጠረው እኮ ጎጃም ነው፡፡ ኦሮሞዎች ጎጃምን ተንከባክበዋል፤ አሳድገዋል፡፡ የሩቁን ዘመን ትተን የዛሬ 400 ዓመት በንጉሠ-ነገሥት ሱስንዮስ ዘመን የሆነውን እንኳ ብናነሳ በጎጃም እንቅስቃሴ ውስጥ ኦሮሞዎች በጣም ትልቅ ሚና ነበራቸው፡፡ ከጣና በስተደቡብ ያሉ ሌሎች ቦታዎችን ሳናነሳ የዛሬዎቹ ኢልማና እና ዴንሳ ዓበይት

የኦሮሞ ሰፈራ ቦታዎች ነበሩ። ቡሬ አጠገብ ወንበርማ፣ ደንግጂዳ፣ መተከል ዙሪያ እና እንዲሁም ወንበራ የሰፈራ ቦታዎቻቸው ነበሩ። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ራሱን የሚያሞኝ ካልሆነ በስተቀር በደም ሥሩ ውስጥ ትንሽ የኦሮሞ ደም የሌለበት እውነተኛ ጎጃሜ የለም። እንዳውም የኦሮሞ ደም የሌለበት ጎጃሜ ደበናንሳ ነው የሚባለው። ይህ የሚመሰከረው፥ የጎጃም አማሮች በኦሮምነታቸውም እንደሚኮሩ ነው። ጥንትም የአማራውም የኦሮሞውም አባት የዛው የጎጃም ንጉሥ የነበረው ፈላስፋውና ነቢዩ ደሸት ወይም ደሴት ነበርና። እንዲሁም ኦሮሞዎች በጎንደር ውስጥ ኖረው ከሱስንዮስ እና ከልጁ ከፋሲለደስ ጋር ጎንደርንም ገንብተዋል። ‹‹የጋላ አገር›› እየተባለ የሚጠራ የተለየ መኖሪያ ቦታም ነበራቸው። በዘመነ-መሳፍንት መግቢያ በኢዮኣስ ዘመን የጎንደር ቤተ-መንግሥት በኦሮሞዎች የተሞላ ነበር። በዘመነ-መሳፍንትማ ሁለቱም፣ ጎጃምም ጎንደርም የእነርሱ ነበሩ። ታዲያ በአዲሱ የኦሮምያ ካርታ ላይ ጎጃምንና ጎንደርን የማናክለው ለምንድነው?

የኦሮምያ ካርታ ትግራይን፣ አፋርን፣ ኦጋዴን-ሶማሌን እና ደቡብ ክልልን ጭምር የማያካትተውስ ለምንድነው? ትግራይ የራስ ቱሉ በዳሳ ልጆች ዶሪ በሚል ልዩ ስም የሚታወቁት ንጉሦች እና የየጁ ቤተሰብ የኦሮሞው የሴሩ ጓንጉል ቤተሰቦችና ነበረች እኮ። የኦሮሞ ልዑላን ለምሳሌ ሁለቱን ለማንሳት ያህል ራስ ዶሪ እና ባህርነጋሽ ይስሐቅ የትግራይ እና ኤርትራ ገዢዎች ነበሩ። ከሁሉም በላይ በአሁኑ ወቅትም የተወሰነው አካባቢ እዛው በቀል ነዋሪዎች በሆኑት በራያ መደባይ ኦሮሞዎች እንደተያዘ ነው። በደቡብና በኦጋዴን-ሶማሊ ክልሎች በርካታ ኦሮሞዎች እንደሚኖሩ ሁሉ በአፋር ምድርም ከረዩ የተባሉ ኦሮሞዎች ይኖራሉ። በርግጥ ኦሮሞና ሶማሊ የአፍሪቃ ቀንድን ሲጋሩ ዘመናት ተቆጥረዋል። አካባቢው ለሁለቱም በእኩልነት የጋራቸው ነው። ታዲያ በእነዚህ ክልሎች ውስጥ ኦሮሞዎች የሰፈሩባቸው አንዳንድ ቦታዎች በኦሮምያ ካርታ ውስጥ ለምን አልገቡም? ኦሮሞው በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ አካባቢ ውስጥ ድርሻ አለው። አማራውና ሌሎቹ ኢትዮጵያውያንም ቢሆኑ ድርሻ አላቸው። ኦሮሞ የኖረባቸውና ታሪካዊ ትስስሮሽ የፈጠረባቸው ክልሎች በኦሮምያ ካርታ ውስጥ መጠቃለል አለባቸው ብዬ አስባለሁ። ሬጋ፣ ለከን ብዬ ሳስብ ደግሞ በነዚህ ክልሎች ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው





ብሔረሰቦች ለምሳሌ አማራ፣ ትግሬ፣ አፋር፣ ሶማሊ፣ የደቡብ ሕዝቦችና ሌሎች ኢትዮጵያውያንም ስለሚኖሩ ሁሉንም እጠቃሎ ‹‹ኦሮምያ›› ብሎ መጥራት ተገቢ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሐዊ እና ትክክል እንዳልሆነ እገነዘባለሁ። እንዲህ ዓይነቱ ጭፍን አስተያየት ኦሮሞ ላልሆኑት ኢትዮጵያውያን ትክክል አይደለም። ጠቅላላው የኢትዮጵያ ግዛት ‹‹ኦሮምያ›› ተብሎ ቢጠራ ኦሮሞ ያልሆኑት ብሔር ብሔረ-ሰቦች ከካርታው ላይ ይፋቁና ማንነታቸው አደጋ ላይ ይወድቃል። ቀድሞ-ነገር እንዲህ ያለውን የበላይነትና ከምድረ-ገጽ የማጥፋት ተግባር ፈጽሞ አይቀበሉትም። በአፍሪቃ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ቀውስና ብጥብጥ ነው የሚነሳው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱን አደገኛ ሃሳብ አላቀነቅንም። እንግዲህ እንደዚያ ቢደረግ ኦሮሞ ያልሆኑት ግላዊና ልዩ የሆነውን ማንነታቸውን ማጣታቸው ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው የመኩራት ስሜታቸውም ይሞታል። ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ ምንም ነገር ቢደረግላቸው ራሳቸውን ኢትዮጵያውያን ብለው አይጠሩም። ስለዚህ መፍትሔው ሁሉንም ክልል ‹‹ኢትዮጵያ›› ብሎ መጥራት ነው። ምክንያቱም ቃሉ ሁሉንም ያካትታል። ከዚህ በላይ ደግሞ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የትግሬ፣ የአፋር፣ የሶማሊ፣ ጋምቤላዎች፣ የሲዳማዎች፣ የወላይታዎች፣ የሃዲያዎች፣ የደቡብ ህዝቦች እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን አባት የሆነውን የኢትዮጵን ስም ይዟል።

ቀደምት አባቶቻችን የተወሰነ ክልል ከልለው ‹‹ኦሮምያ›› ብለው ያልሰየሙበት ምክንያት መላዋ ኢትዮጵያ የነሱ ስለሆነችና እንድትሆንም ስለፈለጉ ነው። ይህ አንዱ ምክንያት ነው። ሌላው ምክንያት ከእኛ ተምረናል ከምንለው ኦሮሞዎች ይልቅ የጥንት እባቶቻችን መነሻ አባታቸው ኢትዮጵያ የተሰየመችበት ኢትዮጵ መሆኑን ይበልጥ ወደ ውስጥ ዘልቀውና ጠልቀው ስለሚያውቁ ነው። በዚህ ምክንያት የገዛ አባታቸው የመሰረታትን አገር ለማፍረስ አልደፈሩም። ስለዚህ የመስፋፋት፣ የመሻሻልና የመበልጸግ ትግላቸው ጥንተ-አባታቸው ኢትዮጵያ ብሎ በሰየማት አገር በመላ ነው እንጂ ቆርሰው እና አጥብበው ‹‹ኦሮምያ›› በሚሏት፣ ባንፃሩ ትንሽ መሬት ላይ ራሳቸውን ነጥለውና ገድበው አይደለም። ትንሽዋ መሬት፥ ቁጥሩ ከሁሉም ይበልጣል ለሚባለው የኦሮሞ ህዝብ አይበቃውም። ለንግድ፥ ለኢንዱትሪ መስፋፋት፥ ለኤኮኖሚ መዳበር፥ ለእርሻ፥ ለተለያዩ

ሥራዎች ሁሉ ይጠበዋል:: የህዝቡ ቁጥር እያደገ ሲሄድም መጨናንቅ ይገጥመዋል::

በእዲሉ የኦሮምያ ፖለቲካ ካርታ መሰረት ጎጃምና ጎንደር ብቻ ናቸው ለአማራ የተወሰኑት:: እማሮች በመላ አገሪቱ ስለሚኖሩ ሰፋ ያለ ምርጫ ቢሰጣቸው በነዚህ በሁለቱ አካባቢዎች ብቻ ራሳቸውን የሚገድቡ አይመስለኝም:: መላዋ ኢትዮጵያ የኛ ናት ብለው ነው እማሮች የሚያስቡት:: ምክንያቱም ባለፉት 3000 ዓመታት ውስጥ በውትድርና ሙያቸው መንግሥታትን ሲጠብቁ እና የአገሪቱን ዳር ድንበርና የግዛት አንድነት ሲያስከብሩ ጠንካራ የኢትዮጵያዊነትና ብሔራዊ ስሜት ገንብተዋል:: ለኢትዮጵያ ሀገርነት መኖር ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የፈፀሙት ታላቅ ጀብድ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፥ ስለእውነት ብለን እውነት ብንናገር፥ በኢትዮጵያ ነፃነት ላይ አማሮች የመሪነት ሚና ባይጫወቱ ኖሮ ቅኝ ገዢዋ ጣልያን ኢትዮጵያን በቀላሉ ድል እድርጋ ለመያዝ በቻለች ነበር:: የዚህም ምስክሩ ጣልያን ናት:: የእማራን ወሳኝ ሚና በመረዳትዋ ጣልያን ክሁሉም በፊት እማራንና ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ነበር ለማጥፋት የተነሳችው:: አማሮች ከተበታተኑ ኢትዮጵያም እንደምትበታተን ጣልያኖች በሚገባ ያውቁ ነበር:: ኢትዮጵያን እዳክመው ለመቆጣጠር የሚሹ ከባህር ማዶ የመጡም ሆኑ የውስጥ ኃይሎች ሁሉ ይህንኑ እድርገዋል:: የአማራ ጠላት የበዛውም ለዚሁ ነው:: ይህ ማለት ግን የኦሮሞ አርበኞች እና ሌሎችም ነፃነት ወዳድ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን ስመጠበቅ ያደረጉትን የጀግንነት ተጋድሎ ማሳነስ እይደለም::


‹‹አገሬ ጎንደር፣ ጎጃም ወይም ሸዋ ነው›› የሚል እማራ እጋጥሞኝ እያውቅም:: እንዲህ ከማለት ይልቅ ‹‹ጎንደሬ ነኝ፣ ጎጃሜ ነኝ ወይም የሸዋ ኢትዮጵያዊ ነኝ›› ይላል:: ብዙዎቻችን ስለዜግነታችን ስንጠየቅ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን እንደዚህ እንደምንል አምናለሁ:: ሰፋ ባለ እነጋገር ሁሉም የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝቦች ማንነታቸውን የሚያያይዙት ከኢትዮጵያዊነት ጋር መሆኑ በ1896 እና በ1936 የተሞከሩትን የኢምፔሪያሊቶችንና የፋሺስቶችን ወረራዎች ለመቀልበስ ባሳዩት ጠንካራ እንድነት አረጋግጠዋል:: በቅርቡ ትውስታችን ሟቹ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያውያን የብሄራዊ ስሜት የላቸውም እያለ ደጋግሞ ቢናገርም በባድመ የተነሳ ትግራይ በኤርትራ ስትወረር የኢትዮጵያ ሕዝቦች እጆቻቸውን እጣጥፈው ‹‹ጦርነቱ በትግራይና በኤርትራ





መካከል ነው፤ እኛ ምን አገባን!›› አላሉም:: ይልቁንም የኢትዮጵያ ወጣቶች ጥሪ ሲደረግላቸው ክምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ሁሉም ከዳር እስከዳር ተነቃንቃው ትግራይን ለማዳን ዘመቱ:: ምክንያቱም ጠንካራ የሆነ የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት እላቸዋ! በዚህም ያቶ መለስ ዜናዊን ዲስኩር ውድቅ አደረጉት::

የኦሮምያ ካርታ ትንሽ ውስብስብነት ይታይበታል፤ ለአብነት ከአዲስ አበባ ወደ ወሎ ስንጓዝ የእማራና የኦሮሞ ቦታዎች በጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው ተቆላልፈው እናገኛቸዋለን:: ከአዲስ አበባ ወጣ እንዳልን ሸኖን እናገኛለን የኦሮሞ መሬት ናት:: እሷን አለፍ እንዳልን የአማራ መሬት የሆኑት ደብረ-ብርሃን እና ሸዋ ሮቢት ይገኛሉ:: ክዚያ የኦሮሞ መኖሪያ የሆኑት ጂሌ እና ከሚሴ ከተማ ይለጥቁና ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸው ክምቦልቻ እና ደሴ ከተሞች ይክተላሉ:: ዘልቀን ከተጓዝን ደግሞ በአማራዎች ወደ ተያዘው የጁ እንደርሳለን:: የጁን ስናልፍ የኦሮሞዎች መኖሪያ የሆነውን ራያ እና እዘቦ እናገኛለን:: አዩ ምን ያህል የተጠላለፈ እንደሆነ? ይህ እንግዲህ በአንድ እቅጣጫ ብቻ ያለ እውነታ ነው:: በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሁኔታው ይመሳሰላል:: እርግጥ ነው በነዚህ አካባቢዎች የሰፈሩ አማሮች እንደዚህ መጨናነቃቸውን የሚፈቅዱት እና ማንነታቸውን ሲያጡም ደስ የሚላቸው አይሆኑም:: ክዚህ የምንማረው አንድ ትምህርት እነዚህ ሁለት ሕዝቦች፣ ኦሮሞና አማራ፣ አንድ መሬት እየተጋሩ እና አንድ ዓይነት ባሕል እየተወራረሱ የሚለያቸው የድንበር መስመር ሳያሰምሩ፣ ሆነ ብሎ እንዳይገናኙ የሚያደርጉዋቸውን የወሰን ምልክቶች ሳያስቀምጡ ለረጅም ዘመን አብረው ኖረዋል:: ለእነዚህ ሕዝቦች ሁነኛው መፍትሔ ከማኅበራዊነታቸው ባሻገር ግለሰባዊ ማንነታቸውንም ማስጠበቅ ነው:: ክማንነት ጥያቄም በላይ እጅግ አሳሳቢ የሆነው ችግር አካባቢውን እንዳለ ከተቀረው ኢትዮጵያ ገንጥሎ አዲስ አገር ለመፍጠር፣ እነዚህን ህዝቦች ለመነጣጠል እና ለመለያየት ክኦሮሞም፣ ክአማራም ሆነ ከተቀረው የኢትዮጵይ ህዝብ ሙሉ ፍላጎት ውጭ በእንድ የፖለቲካ ልሂቃን ድርጅት እየተቀነቀነ ያለው እቅድ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ እቅድ ወደ ግጭት እና ወደ ኢኮኖሚ ድቀት ይመራል እንጂ ለሁሉም ወገኖች ዘላቂ ሰላም እና ብልጽግና እያመጣም::




የኦሮምያ የፖለቲካ ካርታ

ልሂቃን የጎሳቸውን ክልል ለመገንጠልና ለመግዛት ሲቋምጡ ሕዝበ-ውሳኔን እንደ ሽፋን ይጠቀማሉ። የመገንጠል አጀንዳቸውን ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ የሚያስመስሉበት ሥልታቸው ህዝበ-ውሳኔ ነው። በውጤቱም ሰፊው ሕዝብ ጠብ የሚልለት አንዳች ነገር የለም። ህዝበ-ውሳኔ ተብየው ነገር በጠረጴዛ ላይ መቀመጥ የለበትም። ምክንያቱም ለመገንጠል ያቆበቆቡ ልሂቃን በዘዴ በጃቸው ያስገቡትና በህዝቡ ስም ሥልጣን ላይ ፊጥ ይሉበታል። ሰፊው ህዝብ ሁል ጊዜ የታቀደለትን እንዳደረገ እና የልሂቃን መጠቀሚያ እንደሆነ ነው። ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን ምኞት የተቃጠሉ እንዲህ ዓይነት ልሂቃን «ነፃነት ወይስ ባርነት» የሚሉ አማራጮችኝን ብቻ ያስቀምጡና ህዝቡ መገንጠልን እንዲመርጥላቸው በዘዴ






ያስገድዱታል። በኤርትራ ጉዳይ ላይ እንደተደረገው ማለት ነው። «ባርነት ወይስ ነፃነት» የሚል ምርጫ ሲሰጥ «ባርነት» ብሎ ማን ይመርጣል? ሕዝበ-ውሳኔ ማካሄድ የግድ አስፈላጊ ክሆነ ባለ ድርሻ አካላትን በሙሉ መጋበዝ፣ የሚመለከታቸውን የነገድ እና የጎሣ አባላት በሙሉ ማቀፍ፣ የአናሳ ሕዝቦችንም መብት በመጠበቅ በክልሉ የተወለዱትን እና ቢያንስ ለ10 ዓመት የኖሩትን ሁሉ ማስገባትና ባጠቃላይም የኢትዮጵያን ህዝብ ሁሉ ማሳተፍ ያስፈልጋል። ምክንያቱም መገንጠሉ የሚነካው ተገንጣዩን ቅርንጫፍ ብቻ ሳይሆን የሚገነጠልበትንም ግንድ ጭምር ነው። ልሂቃኑ ሀቀኞች ክሆኑ «የብሔር ብሔረ-ሰቦች ነፃነት እስከ መገንጠል መብት!» የሚለውን ጊዜ ያለፈበትን ማርክሲስት-ሌኒኒስት-እስታሊኒስት መርህ ትተው *«የብሔር ብሔረ-ሰቦች መብት ለውስጥ አስተዳደር ነፃነት ራስ ገዝነትን ጨምሮ»* ማለት ይኖርባቸዋል።

ሕዝበ-ውሳኔ ተካሄደም አልተካሄደ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚነሳ የብሔር ጥያቄ (የጎሳ ጥያቄ ነው፥ ትክክለኛው አባባል!) የሚበጀው መፍትሔ የዜግነት መብቶችን፣ ለብዓዊ መብቶችን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እና ሌሎችንም የሃይማኖት፣ የኤኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የጽሁፍ፣ የሚዲያ ወ.ዘ.ተ. ነፃነቶችን በማስጠበቅ የሁሉንም ኢትዮጵያውያን መብቶች በሕግ የምታረጋግጥ አንዲት ኢትዮጵያዊት አገር መገንባት፤ ሕገ-መንግሥታዊት ሪፑብሊክ አገር መፍጠር ነው።

ሪፑብሊክ የብዙሃኑንም የግለሰቡንም፣ የሁለቱንም መብቶችና ፍላጎቶች በሕግ የሚያስከብር ሥርዓተ-መንግሥት ነው። አሁን ባገራችን ያለው ሁኔታ ሲታይ የብዙሃኑ መብት እየተጠበቀ አይደለም። ብዙሃኑም ቢሆን በክልሉ ያሉትን አናሳዎች ይጨቁናሉ። በቅርቡ የተፈፀመ አንድ እውነታ ብናነሳ በቤንች ማጂ እና በቤንሻንጉል-ጉሙዝ በአማሮች ላይ የተፈፀመው በደል የሚጠቀስ ነው። እነዚህ አማሮች በማይረባ ሰበብ ቤት ንብረታቸውን አጥተው፣ መሬታቸውን ተነጥቀው፣ ገንዘባቸውን ተቀምተው፣ ሰብአዊ ክብራቸውን ተገፈው ሜዳ ላይ ተጥለዋል:ጅብ የበላቸውም እንደ አሉ ተነግሮአል:። ኢትዮጵያውያን እንዳልሆኑ ሁሉ በገዛ አገራቸው ይህ ሁሉ ግፍ ተፈፅሞባቸዋል። ኢትዮጵያውያን ባይሆኑም እንኳ የሰው ልጆች ስለሆኑ እንደዚያ መደረግ የለባቸውም።




የኦሮምያ የፖለቲካ ካርታ

ስለ ዲሞክራሲያዊና በተቃራኒው ስላለው ስለ ሪፐብሊካዊ የመንግሥት ቅርፆች ጥቂት ለማለት ያክል ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥሩነቱ ለምርጫ ሂደትና ለድምጽ ቆጠራ ብቻ ነው። ያም ቢሆን በአፍሪቃ ውስጥ ማታለያና ማጭበርበሪያ ሥርዓተ-ሂደት ሆኗል። ሪፐብሊክ ግን በህዝብ የሚመረጡና ለመረጣቸው ሕዝብ ተጠያቂዎች የሚሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን የሚይዝ ሥርዓት ነው። በሥልጣን የሚባልጉ ባለሥልጣናትን ከሥልጣናቸው ለማውረድ፣ የሕግ ጥሰትንና የሰብአዊ መብት ረገጣን እንዲሁም የኢኮኖሚ መድልዎንና ጭቆናን ለማጋለጥ እና ለማስቆም ሕዝቡና ሚዲያው መብት አላቸው። ዲሞክራሲያዊ ቅርፀ-መንግሥት ግን በብዙሃን አገዛዝ ስም የግለሰቦችን የዜግነት መብቶች ለሚረግጡና ሥልጣንና ሀብት ለሚያከማቹ አምባገነኖች እና ለአምባገነንነት በር ይከፍታል። በህግ የተደነገገ እና ለህግ ተገዢ የሆነው ሪፐብሊክ ግን የየግለሰብን መብት በህግ ለሰሚያስጠብቅ የሁሉንም ዜጋ መብት ያስከብራል ማለት ነው። ከሪፐብሊክ በተቃራኒ ያለው ይህ የዲሞክራሲ ጽንሰ-ሃሳብ ወደ ፊት በጥልቀት መጠናት ያለበት ነው።

ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የታሪክ ጊዜያት በተለይዩ ቦታዎች ላይ መስፈራቸውን በተመለከተ ሸዋ እና ወሎ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። የዛሬን ጀማ ወይም ዠማ ወንዝ እና አካባቢውን እንደ ምሳሌ አድርገን ፤ ግራርጌ፣ ሲኮ፣ ካቢ እና ገነቲን ጨምረን እንይ። በእነዚህ አካባቢዎች ከ3000 አመት በፊት አማራና ጀማ ሰፍረውባቸው ነበር። አማራ እና ጀማ - የኦሮሞውች አባት የደሸት የልጅ ልጆች ናቸው።- ወንድማማቾች ናቸው። ዛሬ ሸዋ የሚባለው ከ3000 ዓመት በፊት አማሮች ሲኖሩበት ግራርጌ ነበር የሚባለው። ከዚያ በኋላ በቅደም ተከተል ኡይዝ ፣ገበታን፣ቤጋን፣ እየተባለ ተጠራና በቀዳማዊ ሚኒልክ ጊዜ ሸዋ ተባለ። ኡይዝ ተብሎ ሲጠራ መደባይ/ኦሮሞ/ ይኖሩበት ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት እስከ ንግሥት ሳባ ልጅ እስከ ቀዳማዊ ምኒሊክ ጊዜ ድረስ ኦቺ ይባል ነበር። ቀዳማዊ ምኒልክ "ሸዋ" በሚል ስም ቀየረው ። በሱባ ቋንቋ "ሸዋ" ማለት "የጦርሰራዊት›› ማለት ነው። የምኒልክ ልጅ ቶማይ ጦሩን /ሸዋ የሚባለውን/ በአማራ መሬት ላይ አስፈረና አገሩም "ሸዋ" ተብሎ ይጠራ ጀመር። ይኩኖ አምላክ ከኦሮሞ ከአማራ እና ከሌሎችም ነገዶች በተውጣጣ ፈቃደኛ ሰራዊት ድጋፍ የሰለሞናዊውን ሥርወ-





መንግሥት እንደገና ሲመልስ እና ሲነግሥ ያንን የረዳውን ፈቃደኛ ጦር ቋሚ ጦሩ አደረገውና በሸዋ ውስጥ አሰፈረው። ከዚህ ጦር ውስጥ አብዛኛው አማራ ነበር። አህመድ ግራኝ ሸዋን ሲይዝ የኦሮሞ ጦሩን በአማራ መሬት ላይ አሰፈረ። በዚህም ግራርጌ ይባል የነበረው ሰሌ ወይም ሰላሌ ተባለ። ምክንያቱም ሰላሌ ተብሎ የሚጠራ የግራኝ ጦር እዚያ ስለሰፈረ ነው። አሁን ወሎ የሚባለው የአማራ አገር ጥንት "ሰኮ" ነበር የሚባለው። በ16ኛው ክፍለ-ዘመን አህመድ ግራኝ ከአጼ ልብነ-ድንግል እና ከተከታዮቻቸው ጋር በሚዋጋበት ወቅት የተወሰኑ ኦሮሞዎች እዚያ ሰፈሩ እና በአባታቸው ስም "ወሎ" ብለው አካባቢውን ጠሩት። ሁለቱም አማራም ኦሮሞም ያንድ ሰው፣ ማለትም የኢትዮጵ ዝርያ የሆነው የደሸት ልጆችና ልጅ ልጆች ስለሆኑ፥ እንዲሁም ሁለቱም ዘመዳሞች በዛ ቦታ ላይ ሲኖሩ እነዚህ ቦታዎች አሁን ለማን ይሰጡ? ወደ ማንኛቸውስ ይከለሉ? ሁለቱም (ኦሮሞም አማራም) የኔ ነው ስለሚሉ እውነታቸውን ነው፥ የሁለቱም ነው። የሁለቱም ንብረት ከሆነ ደግሞ በሰላም አብሮ ለመኖር እና ለጋራ ፍቅር ሲባል ያለ ራስ ወዳድነት ስሜት ሁለቱም ቢካፈሉት ለዘላቂ ሰላም እና ብልፅግና ይበጃል። ለሸዋ ኦሮሞዎችና አማሮች ደግሞ ይህን ማንም አይነግራቸውም። እነሱ ተቻችለውና ተዛምደው አብረው ለ 3000 ሺህ ዐመታት በሸዋ ኖረዋል። የተለያዩ ኢትጵያውያንም በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የኢትዮጵያ መሬቶች እየሰፈሩ ኖረዋል። 100 ዓመት ወደኋላ ሄዶ የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ማንሳት ፍሬ-ቢስ ነው። አንዱ ጎሳ ሌላውን ሳይጫንና ያንበሳ ድርሻ ይገባኛል ሳይል የኢትዮጵያን ምድር ሁሉም የኢትዮጵ ልጆች በፍትሃዊነት እና በእኩልነት ሲኖሩባት ይገባል። ባሁኑ ዘመን ስግብግብነት እና ራስ ወዳድነት ዋጋ ያስከፍላሉ። በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ፍትሃዊ መቁዋደስ ነው ለሁሉም ሰላምን እና ብልጽግናን ሲያለፍን የሚችለው። ልጆችዋ ከስሜታዊነት ይልቅ ምክንያታዊ ቢሆኑ፣ እርስ በርሳቸው ቢፋቀሩ እና ቢተሳሰቡ ኢትዮጵያ ከሰው በሃጢያት መውደቅ በፊት፣ ማለትም አዳም በገነት ከመሳሳቱ በፊት እንደነበረችው ምድረ-ገነት ትሆናለች። አዳዲስ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ገነትም የነበረችው ኢትዮጵያ ውስጥ ነበርና።

# ማጠቃለያ እና መደምደሚያ

ከላይ ከቀረቡት ሦስት አበይት ርዕሶች ኢትዮጵ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ጥንተ-አባት መሆኑን ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ብዙ እንዳበረከቱ፣ ኦሮሞ እና እማራ ካንድ አያትና አባት የተገኙ ወንድማማቾች፣ ባንድ አገር በኢትዮጵያ፣ ባንድ አካባቢ በጎጃም የበቀሉ አንድ ዘር መሆናቸውን ተምረናል። ዋና ከተማው አክሱም የነበረውን የሰሎሞንን ሥርወ- መንግሥት ስንመረምር ከምታፈቅረው ባልዋ ተወስዳ ለንጉሠ-ነገሥት ጃንሰገድ የተዳረችውን ማርብሳ የተባለችውን አማራ ሴት አግኝተናል። ልጅዋ አአልሜዳ ንጉሠ-ነገሥት ሰይፈ-አርዕድ ተብሏል። ሌላዋ አሃዬ የተባለች ከፊል አማራ የሆነች ሴት አልአሜዳን እግብታ ንግሥት አብርሂት እንደተባለችና አብርሃ እና እጽብሃ የተባሉ መንትያ ልጆችን እንደወለደች አይተናል። የተጠቀሱት ሁሉቱም ሴቶች ልጆቻቸው ህጻናት በነበሩበት ወቅት ሰሰሞናዊውን ዙፋን መጠበቃቸውንና ንግሥት አሃዬ ከመንታዎቹ ልጆቿ ጋር ሆና ክርስትናን ማስፋፋቷን ተመልክተናል። እጼ ናግሺሬ፡ አዴር ወልዱ የተባለ ወንድም የነበራትን ሶሪያዊት ሴት እንዳገቡ እና በትልቁ አሌክሳንደር ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱት ሶርያውያን እና ባቢሎናውያን እግአዚዎቹን ድል አድርገው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሥልጣን ለወገኖቻቸው እንዳስገኙም ዳሰሰናል። በዚህ ወቅት የኦሮሞ ዝርያ የሆኑ ንጉሦች እና ንግሥቶች ባያጋጥሙንም ዋና ከተማቸውን ሸዋ ውስጥ ተጉለት ያደረጉ በርካታ የኦሮሞ ዝርያዎች የሆኑ ንጉሠ-ነገሥቶችን እና ንግሥተ-ነገሥታትን በሰሰሞናዊው ዙፋን ላይ ተቀምጠው አግኝተናል። ተጉለት መናገሻ የሆነችው ኦሮሞ ከሆነችው ክሃዊ ጊፍቲ መንዲያ በሚወለዱት በአጼ ይኩኖ አምላክ ነው። ዋና ከተማቸውን ተጉለት፣ ሸዋ እና ላስታ አድርገው በሰሰሞናዊው እና በዛጉዬው ሥርወ-መንግሥታት ዙፋኖች ላይ ከተቀመጡት ውስጥ አንድም አማራ የሆነ ንጉሠ-ነገሥት ወይም እማራ የሆነች ንግሥተ-ነገሥታት አላገኘንም። አማሮች እና እማርኛ ግን በሁለቱም ሥርወ





መንግሥታት የተፈቀዱ ነበሩ። ምክንያቱም ይኩኖ እምላክንም ላሊበላንም ሥልጣን እንዲይዙ አማሮች ስለረዱዋቸው። ይሁን እንጂ በአማራው ስም በኢትዮጵያ ምድር ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ የገዛ አንድም ሰው አላገኘንም። ይልቁንስ አጼ ሱስንዮስ እና አጼ ኢዮአስ እንዲሁም ኦሮሞዋ የአጼ ኢዮእስ እናት ንግሥት ወለተቤርሳቤህ በ15ኛውና በ18ኛው ክፍለ-ዘመናት የኦሮሞ መሳፍንትና መኳንንትን በአማራው ላይ ነፍጠኞች አድርገው በጎንደር እና በጎጃም ይሾሙ እንደነበር አይተናል። በዘመነ-መሳፍንት ወቅት ጎንደር ከትመው የነበሩ የየጁ የኦሮሞ መሳፍንት በሰሰሞናዊው ዙፋን ላይ አሻንጉሊት ንጉሠ-ነገሥት ለስሙ እያስቀመጡና እነሱ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ እየሆኑ እውነተኛውን ሥልጣን በመጨበጥ ሰሜንና ምእራብ ኢትዮጵያን ለ70 አመታት እንደገዙ ተገንዝበናል። ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ሀቅ የኦሮሞ ዝርያዎች ከአማራም ሆነ ከሌሎች ጎሣዎች በላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ሆነው ላለፉት 700 ዓመታት ኢትዮጵያን ሲገዙ፣ ሲመሩ እና ሊያስተዳድሩ የኖሩ መሆናቸውን ነው። አንዳንድ የኦሮሞ ልሂቃን ግን ይህን ታሪካዊ ሀቅ በወጉ የተገነዘቡት ስለማይመስል ግንዛቤያቸውን ማደስ እና ከእውነታው ጋር ማጣጣም ይጠበቅባቸዋል።

በጎሳና በነገድ፥ በዘርና በቋንቋ፥ በብሄርና በጎሳ፥ በሃገርና በዜጋ መሃል የአሉትን ልዩነቶች ሁሉ ተመልክተናል።

በዚህ ጽሁፍ ይዘት ውስጥ የተሰያዩ ነገሥታት እና ኢማም አህመድ ግራኝ አማራና ኦሮሞ ወታደሮቻቸውን ዛሬ ሸዋ እና ወሎ ብለን በምንጠራቸው ቦታዎች በማስፈራቸው በሸዋ ውስጥ "ግራርጌ" በማዕከላዊ የአማራ ክልል ደግሞ "ሊኮ" ተብለው ባማርኛ ይጠሩ የነበሩ ቦታዎች በስተኋላ በመጡ ኦሮሞ ሰፋሪዎች ስያሜአቸው "ሰላሌ" እና "ወሎ" ወደሚሉት መለወጡን ተገንዝበናል። እንዲሁም የሰሰሞናዊው እና የዛጉዬ ስርወ-መንግሥታት አጼዎች ዙፋኑን እና ፍጹማዊውን ሥልጣን ለራሳቸው ብቻ አድርገው በየክልሎቹ የሚሾሟቸው እና ሉኣላዊ ገዢነታቸውን ተቀብለው የሚገብሩላቸው ንጉሦች ግዛቶቻቸውን በነፃነት እንዲያስተዳድሩ መብት የሚሰጥ ፌዴራላዊ ዓይነት ሥርዓት እንደነበራቸው ተረድተናል። ከነዚህ እውነታዎች ጋር የሁለቱም ሥርወ-መንግሥታት ንጉሠ/ንግሥተ/-ነገሥታት የሚወክሉት፣ የሚጠብቁትና የሚንከባከቡት ራሳቸውን እና ቤተ-

ሰቦቻቸውን ብቻ እንጂ የኦሮሞን እና የአማራን ሰፊ ሕዝብ ፍላጎት እንዳልነበረ እውቀናል።

እንዲሁም በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዙፋን ላይ እየተቀመጡ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ኢትዮጵያን የመሩ እና ያስተዳደሩ ኦሮሞዎች ነበሩ እንጂ አማሮች እንዳልነበሩ ተገንዝበናል። ከዚህ በተጨማሪ ኦሮሞና አማራ በጣም የተቀራረበ ባሕላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ-ልሳናዊ እና ሥነ-ሕይወታዊ ትስስሮሽ እንዳላቸው ተምረናል። ይህ ጥናት በኦሮሞና በአማራ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ቢያተኩርም የተቀሩት ኢትዮጵያውያንም ኢትዮጵያን የመሰረታትና መጠሪያዋንም የሰጣት የኢትዮጵ ልጆች መሆናቸውንና ላለፉት 4,000 ዓመታት በጋብቻ፣ በማህበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት፣ በባህላዊ መስተጋብር እና በመሳሰሉት እንደቅደም ተከተሉ ከኦሮሞና ከአማራ ጋር እየተሳሰሩ መዛመዳቸውን የኢትዮጵያን ታሪክ ሰንቃኝ አይተናል።

የላቲኑን ወይም የኢትዮጵያውያን ፊደል ስለመጠቀም ጉዳይ አንስተን በላቲን ፊደል ለንባብ አስቸጋሪ እና ላፃፍ የተንዛዛ የሆነው በኢትዮጵያው ፊደል ግን ሳነባበብ ቀና እንደአጠራሩ የሚጻፍ፣ እንደተጻፈው የሚነበብ፣ እና ላፃፍ ቀልጣፋ (ፊደል፣ገንዘብና ጊዜ ቆጣቢ) እንደሆነና የኢትዮጵያ ፊደላት ለሚውሉበት ዓላማ እጅግ ተስማሚዎች መሆናቸውን በዚህም ኦሮሞዎች እና ሌሎችም ኢትዮጵውያን ከላቲኑ ፊደል ይልቅ በኢትዮጵያ ፊደል ቢጽፉ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተረድተናል።

ስለ ኢትያኤል ታዋቂ በሆነችበት መጠሪያዋ ‹‹ንግሥተ-ሳባ›› ስለምትባለዋ ማንነት እና በርግጠኝነት መኖር አንብበናል። በንባባችንም ኢትያኤል(ንግሥት ሳባ) የኢትዮጵ ዝርያ እንደሆነች፣ አያትዋ አጋቦና በአጼ አሰያኤል የተመሰረተችው የሳባ ከተማ ንጉሥ እንደነበረ፣ ሳባ የተሰኘው የኢትያኤል መጠሪያም ከዚች ከተማ የመጣ መሆኑን ጨብጠናል። ከኤትያኤል ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያዊ ምንጭ ያላት ቢልቂስ በኢትያኤል ፈቃድ የአረቢያ ንግሥት ሆና በእግአዚዎች እንዛ እንደ ነገሰች አንብበናል።

ኢትዮጵያ ረጅምና ዝነኛ ታሪክ ያላት አስገራሚ አገር ናት። ህዝቧም ቅይይጥ መልክ ያለው የተለየ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያውያን መልክ





የተለያዩ ቀለማት እንዳሉት ውብ አበባ የሚወደድና የማይጠገብ ነው። የተለያዩ ቋንቋዎቿ ባህሏ፣ ሙዚቃዋ፣ ዳንኪራዎችዋ ፣ የምግብ አሰራሯ፣ አልባሳቷ፣ የፀጉር አሠራር ዘዴዎቿ እንዲሁም የንድፍ ጥበብዋ እና እደ-ጥበብዋ ይህ ሁሉ በያንዳንዱ ነገድዋ ውስጥ ሲታይ ኢትዮጵያን ከልክ በላይ በፀጋ የታደለች አገር ያደርጋታል። ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ብዙ ቋንቋዎች እና በርካታ ባህሎች ላላቸው ማኅበረሰቦች ጥሩ ሞዴል የምትሆን አገር ናት። በርካታ ነገዶች ያሏት አገር መሆኗ አያያዙን ካወቀችበት በሰውር ያለ ጸጋ ነው። መሪዎቿ ብልሆች፣ አርቆ አሳቢዎች እና ራዕይ ያላቸው ከሆኑ ነገደ-ብዙነቷን ለመከፋፈልና ለውድቀት ሳይሆን ለአንድነት፣ ለጥንካሬ እና ለብልጽግና መሰረት አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ዳሞ፣ ሐዲያ፣ ጎጃም፣ ኮንሺ፣ ሴኑካ፣ ጨላሎ፣ መጋል እና ጋውል የተባሉ ሰምንት ንጉሦች መደባይ፣ መንዲ እና ጂማ ከተባሉ ወንድማማቾች ከሆኑ የደሼት/ደሴት/ ልጆች እንደተወለዱ እና በየዘርፋቸው የኢትዮጵያን ነገዶች እንዳስገኙ፤ ሁሉም ደግሞ የኢትዮጵ ዝርያዎች እንደሆኑ እውቀናል። እነዚህ ንጉሶችና ነገዶች የኖሩት ከ3,200 ዓመት በፊት ነው። ከእነዚህ ነገዶች አብዛኞቹ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸውና ሁላችንም የኢትዮጵና የደሼት ዝርያዎች ለመሆናችን ህያው ማስረጃዎች መሆናቸው የሚያስደንቅ ነው። እነሱም መደባይ፣ ማጂ፣ ጋፋት፣ ጂሬ፣ ዋጂራት፣ ቦነጋ፣ ጎጃም፣ መንዲ፣ ወንጌ፣ ቦረና፣ ቱሰማ፣ አባታሊት፣በርቱማ፣ ጋሊ፣ ጂሎ፣ ኢሳ፣ ሃሼን፣ ሲዳማ፣ ማያ፣ ሆሮ-ወላቦ፣ ቦረን፣ ኢቱ እና ወረማያ ናቸው። ለ3200 ዓመታት ያለማቋረጥ ሲፈሉ የኖሩት ወንዞቻቸውም አሁንም ይፈሳሉ። ግዮን፣ ዋቢ፣ ነገሌ፣ ገናሌ፣ አዋሽ፣ ጊቤ፣ እና ጁባ ናቸው። እነዚህ ስ3200 ዓመታት በኢትዮጵያ ምድር ላይ የኖሩ ኢትዮጵያውያን ነገዶች ተራብተውና ቅርንጫፎቻቸውን አራብተው ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ የምንኖር መላ ኢትዮጵያውያንን አስገኝተዋል። በዛን ጊዜ ከ350 ዓመት በኋላ የዛሬ 2850 ዓመት ከነገሰው ከንጉሠ-ነገሥት አከሉማይት ዘመን ጀምሮ እንኳ የነበሩ ነገዶች በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ እንዳየነው ዝርዝራቸው ብዙ ስለሆነ እንደገና እዚህ ለመድገም አልሻም።

እድሜ ለቴክኖሎጂ! ሰፊዋ ዓለም ዛሬ ጠባብ መንደር ሆናለች። የመለያየት፣ የመበጣበጥ እና የመጠላላት መንፈስ ጊዜው አልፎበታል።

ለኢትዮጵያ ችግር ሁነኛው መፍትሄ የህግ የበላይነትን በሚያሰፍን ሪፐብሊካዊ ሥርዓተ-መንግሥት ስር በእውነተኛ እኩልነት ላይ የሚመሰረት አንድነት ነው። መበታተንና መገነጣጠል ለማንኛውም ወገን ምንም አልፈየደም። እንደኛ የተለያዩ ነገዶች፣ ሃይማኖቶች፣ ቋንቋዎች እና ባሕሎች ያሏት አገር ማድረግ ያለባት ሁሉንም በእኩልነት ማየት፣ ለሁሉም እኩል ድጋፍ ማድረግ፣ ሁሉንም እኩል ማወደስ፣ እኩል ማሳደግ እና እኩል ማክበር ነው። ኢትዮጵያም ይህንኑ ነው ማድረግ ያለባት። ርግጥ ነው የጋራ አገራችንን እየገነባን የየግል ኑሯችንን ስንኖር ለሁላችንም የመተሳሰሪያ እና አርስበርሳችን የምንግባባበት፣ መንግሥትም ሥራውን የሚያካሂድበት አንድ ብሔራዊ የሥራ ቋንቋ ያስፈልገናል። አዲስ የጋራ ቋንቋ በመፍጠር ሀ ብለን ከምንጀምር ላሰፉት አንድ ሺ. ዓመታት ብሔራዊ መግባቢያ ሆኖ ሲሰራበት የቆየው አማርኛ ሰላለን በእሱ መጠቀማችንን ብንቀጥል ብልህነት ነው። ኦሮምኛ ደግሞ ሁለተኛው ብሔራዊ መግባቢያችን መሆን ይችላል። አማርኛ ቁዋንቁዋ መቀጠል ያለበት፥ በቃላት የበለጸገ፣ ሰፊና ጥልቅ ሃሳቦችን በጥቂት ቃላት የሚያስተላልፍ፣በዐለም ላይ ወደር የሌለ ቅኔ የሚገለፅበት፥ ተረትና ምሳሌዎች፣ሥነ-ቃሎች፣ አባባሎችና ፈሊጣዊ አነጋጋሮች የታጨቁበት ከመሆኑም በላይ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚረዳው ቋንቋ ስለሆነ ነው። እስካሁን እንደ አማርኛ ያለውን መንግሥታዊ ቋንቋ ማወቅ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት አውቀው የተገለገሉበት ነገዶች በጣም ጥቂት የሆኑ "ጮሌዎች" ብቻ ናቸው። እነዚህ ጮሌዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ ልሳነ-ብሄራት የሆነውን አማርኛንም አጥርተው ያውቃሉ። በዚህም ከሌሎቹ በትምህርት መሰጫነቱ እና በጋራ መግባቢያነቱ ከማይጠቀሙበት ዜጎች ይበልጥ የተሻለ የትምህርት፣ የሥራ እና የኤኮኖሚ ዕድል ሊያገኙበት ኖረዋል፤ በማግኘትም ላይ ናቸው። አማርኛን መማር ይጠሉ የነበሩ ዜጎች አማርኛን ከአማራ ጋር ያምታቱ የነበሩ ናቸው። ብዙ ዕድል አምልጧቸዋል። አማርኛን በማውገዝ ይታይ የነበረው ፍንደቃ እና የራስን ቋንቋ ብቻ የማራመድ አባዜ አሁን ጋብ ያለ ይመስላል። ጥቂት መምህራን በየ ክልላቸው በሚነገሩ ቋንቋዎች ሥርዓተ-ትምህርት ነድፈው የህጻናት ትምህርት ቤቶችን ከፍተው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በርካታ ወላጆች ግን አማርኛ በሥርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ ካልተካተተ በሚል ልጆቻቸውን ወደነዚህ ትምህርት ቤቶች ለመላክ ፈቃደኞች አልሆኑም።





ምክንያቱም፥ መንግሥት በድፍን ኢትዮጵያ በይፋ የሚጠቀምበትን አማርኛን ረግጦ ጥሎ በራስ ቁዋንቁዋ ብቻ መናገርና መማር ወንዝ የማያሻግር በመሆኑ ልጆቻቸው እንዳይጎዱባቸው በመቆርቆር ነው።

ፖለቲካንና ጥላቻን ገሸሽ አድርገን አባታችን ኢትዮጵ ባሻሻላው እትዮጵያዊ ፊደሎች ለመጻፍ መልካም ፈቃድ ሊኖረን ይገባል። ምክንያቱም ለሰፊው ሕዝባችን እንግዳ በሆነው በላቲን ፊደል ከምንጽፍ ይልቅ በኢትጵያዊ ፊደል ብንጽፍ በርካታ ጥቅሞች እናገኛለን። አማርኛ ቋንቋ እና የግዕዝ ፊደሎች ኦሮሞን ወይም ሌላ ማንኛውንም ሰው አልገደሉም፣አልገረፉም፣ አላሰቃዩም። ይልቅስ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር እየተግባቡ አውቀት፣ ሃሳብ፣ ፍቅር፣ መረጃ እንዲለዋወጡ በማስቻል የተሻለ ሻይወት እንዲኖሩ ይረዷቸው ነበር እንጂ። ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በተጨማሪ በሰፋት የሚነገር እንድ ‹‹ብሔራዊ›› ቋንቋ ማወቅ ለግል ህይወት እና ለሀገር እድገት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

እናም ሀገራችንን ስንገነባ የሁሉንም ኢትዮጵያውያንን እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ እንጠቀማለን። በግንባታ ጥረታችን ሁሉ በፍጥነት ለማደግ ገንቢዎቹ ብሔራቸው ምንም ይሁን ምን ችሎታው ያላቸው ነው መሆን ያለባቸው። ዘር ለሥራ ቅጥር እና ለሹመት መስፈርት መሆን የለበትም። አውቀት፣ ክህሎት፣ አቅም፣ የሙያ ብቃት እና የሥራ ፍቅር ናቸው ለቅጥር እና ለሹመት መስፈርት መሆን ያለባቸው። ዘር ብቻውን ቤት፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ግድብ አይሠራም ወይም የታመመ አያክምም። እነዚህን ተግባራት ማከናወን የሚችሉ የተማሩ ኢንጅነሮች እና የሰለጠኑ ሀኪሞች ናቸው። የስነዘርኳቸው ሀሳቦች በሥራ ላይ ቢውሉ አገራችን ባጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ትጠቀማለች። ያለፈውን ቅራታ መቆፈር የዛሬውን ችግር አይፈታም። ያለፈውን ስንቆፍር ብንውል አመድ ብቻ ነው የምናፍሰው። አመድ ደግሞ ለማንም ምንም አይፈይድም። ነገን የተሻለ ለማድረግ በዛሬው እውነታ ላይ በቀና ልቦና፣ ባስተዋይ ኅሊና፣ በጥሩ መንፈስ እና በጋለ ፍላጎት ማቀድ አለብን። የወቅቱ እውነታ ለሰላም፣ ለእርቅ፣ ለፍቅር እና ለጋራ መግባባት ይጣራል። የጋራ ተጠቃሚዎች እንድንሆን ይህንን ጥሪ እንቀበል። በመደምደሚያዬ ላይ አጽንኦት ሰጥቼ ማስተላለፍ የምፈልገው ይሕን ሀቅ ነው።

## Notes:


The Extent of Amara Participation in the Dynasties of Ethiopia

1.Wikipedia, 2015.

2. ibid., 2015.

3*መፅሐፈ ሱባኤ ዘበአማን ካልዑአዲስ አበባ+በራስ ህትመት+ ገፅ*.59

. Aman Belai, Metsihafe Subael Kale, p.59.

4. Aman Belai. ibid., p.140.

5. Aman Belai. Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik. p.208.

6.Aemro Nigusse, Tintawi Ye Ethiopia Ye Selam Tibeka Tarik, p.6.

7.Aman Belai, *Metsehafe Subae*, pp. 49-51.

8.Aman Belai.ibid., p.167.

9. Amabn Belai. ibid. pp., 169-173.

10. Aman Belai. ibid., p.181.

11. Aman Belai. *Metsahife Abrihit*. p.144.

12. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik. p.116.

13. Aman Belai. *Metsihafe Abrhit*. pp. 118—119.







14 Aman Belai. Yetintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik. p.116.

15 Aman Belai. Hezbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tari, p.30.

16. Tsehafe Tizaz Gebre-selassie. *Tarike Zemen Dagmawi Minilik*. p.22.

17. Aman Belai.*Metsihafe Abrihit*, p.143.

18. Aman Belai. loc.cit.

19. Belai, Aman, Yetintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik. p. 200

20. Aman Belai ibid., p.185

21. Bairu Tafla, *Atsme-giogis and His Works*, p. 280.

22. Bairu Tafla. ibid., p. 284.

23. Belai, Aman, ibid., p. 209.

24. F. Josephus, *Jewish Antiquities*, ed. J. Thaceray and R. Marcus, Loeb Classical

Library, London, 1961, Vol. VIII, pp. 165-175.

25. *The Holy Bible*, I Kings X: 1-10.

26. Aman Belai, Metsihafe Subae Zebea`man Kale, pp.59-60.

27.*The Holy Bible*, Mathew, 12, 42., Luke, 11, 31.

28.ibid., I, Kings, 22.

29. ibid., I Kings, 22, 48.

30. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik, p.62.

31.N.Pearn and V. Barlow, *Quest for Sheba*, London, 1964, pp. 250-251.

32 Sergew Hable Selassie, Ancient and Medival Ethiopian History to 1270, pp. 38-39.

33 Aman Belai, *Metsihafe Subae Zebeaman Kale* pp.116-117.

34. Aman Belai, Metshafe Subae Ze Be Aman Kale, pp. 305-306.

35. Aman Belai. Ye Tintwa Ye Ethiopia Tinsae Tarik, pp. 60-61

36. Mohammed Hassen. *The Oromo of Ethiopia*. p. 133.

37. Mohammed Hassen, ibid. p. 177-178.

38. Mohammed Hassen.ibid. p. 81.

39. Aman Belai, Yetinantinawa Ethiopia Negestat Tark, pp. 249-250.

40. Aman Belai, ibid. p. 307.

41. Tekletsadki Mekuria, Atse Tewodros ina Ye Ethiopia Andinet, p.186.

42. Belai, Aman, ibid. pp. 265—266.

43 Bairu Tafla, *Atsme-giorgis and His Works* , p. 564.

44 Aman Belai,ibid., p. 22.

45. Tekle-tsadik Mekurai, ibid., p. 275.





46. Berihun Kebede, *Ye Atse Haile Selassie Tarik* pp. 147-148.

47. Aman Belai. *Metsehafe Subae Kale*, p. 308.

48. Aman Belai, Hizbawi Kedamawi Ye Ethiopia Mestawet Tarik, pp. 37—3

49. Teshafe Tiza Gebre-selassie, *Tarike Zemen Ze Dagmawi Menilik*, p.34.

50. Gebreselassie. ibid., p.277.

51. Gebreselassie. ibid., p. 220.

52. Tilahun Birhane-selassie Bete, Ye Hayangaw Kiflezemen Ethiopia, andenga metsihaf,

pp., 130-131.

53. Berihun Kebede, ibid., p. 155.

54. Aman Belai, Yetinatinawa Ethiopia Negestat Tarik, p.180.

55. Aman Belai, Ye Tintwa Ethiopia Tinsae Tarik, p. 68.

56. Aman Belai. Hzbawl Kedamawi Ye Ethiopia Tarik, p. 42.

# ዋቢ መፃህፍት በከፊል


አማን በላይ ፥ የጥንትዋ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክአዲስ አበባ፥ቦሌ ማተሚያ ቤት፥1985::

መፅሐፈ ሱባኤ ዘበአማን ካልዑአዲስ አበባ፥በራስ ህትመት፥1998::

ህዝባዊ ቀዳማዊ የኢትዮጵያ መስታወት ታሪክ፥አዲስ አበባ፥ በራስ ህትመት፥1888::

መፅሐፈ አብርሂት፥አዲስ አበባ፥አስካለ ማተሚያ ቤት፥2000::

የትናትናዋ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ፥በራስ ህትመት፥አዲስ አበባ፥1989::

አእምሮ ንጉሤ፥ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ፥አዲስ አበባ፥

ት.መ.ማ.ማ.ድ.፥2000::

አስራት ቦጋለ፥ ኢትዮጵያና ዕድልዋ(1ኛ መፅሐፍ)ፓሪስ፥በራስ ህትመት፥1996

Bairu Tafla. Asma Giyorgis And His Work, Sttutgart, Franz Steiner Verlag Wiesbaden GMBH, 1987.

ባሕሩ ዘውዴ፥ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ 1847 እስከ 1983*፥ አዲስ አበባ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፥1999::

Bahrey, Ameida, Huntingord & Beckingham, Introduction by Donald L. Levin, History of the Galla (Oromo) of Ethiopia, Oakland,Califomia, African Sun Publishing, 1993.







በሪሁን ከበደ፥የዐፄ ኀይለሥላሴ ታሪክአዲስ አበባ፥ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥1993::

Bonnie K. Holcomb and Sisai Ibssa. *The Invention of Ethiopia*, Trenton, NJ, The Red Sea Press, 1990.

Bowersock, G.W., The Throne of Adulis, Oxford, Oxford University Press. 2013.

Budge, E.A. Walllis (Sir) The Kebra Nagast, (translated from the Ethiopic) London, Oxford University Press,1922.

Cotter, George, Proverbs and Sayings of the Oromo Peoples of Ethiopia and Kenya, London, UK, The Edwin Mellen Press. 1992

Fikre Tolossa. The Hidden and Untold History of The Jewish People and *Ethiopians,* Berkeley, Califomia. Fast Images, 2010

ኀብረሥላሤ (ፀሐፌ ትእዛዝ)፥ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ፥ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፥አዲስ አበባ፥ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኀይለሥላሤ ማተሚያ ቤት፥1959::

ጌታቸው ኀይሌ፥የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፥ሚነሶታ፥ኮሌጅቪል፥1995::

J.L.Krapf. *Vocabulary of the Oromo Language*, London, printed for the church missionary society, 1842.

ሀብተማርያም አሰፋ፥የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች፥ አዲስ አበባ፥

ሳጽሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መዛሬያዎች፥ አዲስ አበባ፥ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፥1999::

ሰይኩን ብርሁኑ፥የግዕዝ መማሪያ፥ ዋሺንግተን ዲሲ፥ Signature Book Printing Inc., 2006.

ልሳነወርቅ ገብረጊዮርጊስ፣ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሴት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ፣ አዲስ አበባ Maison Des Etudes Ethiopiennes/Tigrai Institute of Languages, 1997::

Marcus, Harold G.. *A History of Ethiopia,* Berkeley, University of Califomia Press. 1994.

*መንግሥቱ ደስታ* (አምባሳደር)፣ግርማዊትእቴጌጣይቱብጡልብርሃን ዘ ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ፣ቼምበር ማተሚያ ቤት 1999::

*መፅሐፍ ቅዱስ፣የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መፃህፍት፣*አዲስ አበባ፣United Bible Society, 1980.

Sergew Hable Sellassie, Ancinet and Medieval Ethiopian History to 1270, Addis Ababa, United Printers, 1972.

Mohammed Hassen. *The Oromo of Ethiopia*, Trenton, NJ, The Red SeaPress, 1994.

ጳውሎስ ኞኞ፣*አጤ ቴዎድሮስ፣*አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተማያ ቤት፣1985

*ዳግማዊ አጤ ምኒልክ፣*አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ቤት፣1984::

*ታዬ ገብርማርያም* (አለቃ)፣ *የኢትዮያጵያ ሕዝብ ታሪክ፣*ኡፕሳላ ዩኒቨርሲቲ፣ ስዊድን፣1987::

ተክለፃድቅ *መኩሪያ፣የኢትዮጵያ ታሪክ፣* ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል፣ አዲስ አበባ፣በተስፋ ማተሚያ ቤት፣በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኀይለሥላሴ በ 28ኛው ዘመነ መንግሥት::

የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ አዲስ አበባ፣በብርሃንና ሰላም ቀ ኀ ሥላሤ ማተሚያ ቤት1965::

*ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣*አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣1982::

ዐፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣አዲስ አበባ፣ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣1981::

ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣1983::

ታደሰ ዘወልዴ (ቀኛዝማች)፣*ጣይቱ ብጡል፣*አዲስ አበባ፣ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣1980::

"NewYork Times", Saturday, October 21, 2006

*The Joumal of Oromo Studies*, volume 12, Numbers 1 & 2, July 2005, The University of Michigan-Flint, Flint Michigan.

*The Joumal of Oromo Studies*, volume 13, numbers 1 & 2, July 2006. The University of Michigan-Flint, Flint, Michigan.

*The Kibre Negest*, Oxford University Press, London, 1932

ጥላሁን ብርሃነሥላሴ፣ *የ 20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ፣*አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1998::

ተድላ ዮሐንስ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣አጣሊያ በኢትዮጵያ ከወልወል እስከ ጎንደር፣ አዲስ አበባ፣ማንኩሳ አሳታሚ ኀ.የተ.የግ.ማኅበር፣2004::

ይልማ ደሬሳ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፣አዲስ አበባ፣ Far East Trading I.L.C (P.P.) 1999.

Ullendorf, E., *The Ethiopians*,London. Oxford University Press,1960

ዘውዴ ረታ፣ተፈሪ መኮንን፣ ረጅሙ የስልጣን ጉዞ፣ አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣1997::

የቀዳማዊ ኀይለሥላሴ መንግሥት፣ New Delhi, Laxmi Publications LTD. 2012.

; 

## <u>ስለ መልከፀዲቅ ተጨማሪ ማብራሪያ</u>

ስለ የሳሌም (ኢየሩሳሌም) ንጉሥ መልከፀዲቅ ስናወሳ የእሱን ማንነት አስመልክቶ ውዥንብር አለ;; መልከጸዲቅ በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በኦሪት ዘፍጥረት (11. 18-21)፣ በቅዱስ ዳዊት መዝሙር (109-110. 4) እና የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ እብራውያን (ምእራፍ 7) ተጠቅሶአል;; --

በኦሪት ዘፍጥረት (14. 18-21) ስለ አብርሃም እና መልከፀዲቅ እንዲህ ይላል;--

››አብርሃም ከሎዶጎምርንና ከእሱ ጋር የነበሩትን ነገሥታት ወግቶ ከተመለሰም በሁዋላ የሶዶም ንጉሥ የንጉሥ ሸለቆ በሆነው የሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ;; የሳሌም ንጉሥ መልከፀዲቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ;; እርሱም የልኡል እግዚአብሄር ካህን ነበረ;; ባረከውም (አብርሃምን)– አብርሃም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልኡል እግዚአብሀር የተባረከ ነው;; ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልኡል እግዚአብሄርም የተባረከ ነው፣ አለውም;; አብርሃምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው;;››

በዳዊት መዝሙር ደግሞ (109—110‹ 4) እግዚአብሄር አብ፣ በዳዊት አፍ ውስጥ ስለ እየሱስ ክርስቶትስ ዘላለማዊ ካህንነት ምሎአል--

››እንደ መልከፀዲቅ ሥርዐት አንተ የዘላለም ካህን ነህ ብሎ፣ እግዚአብሄር ማለ፣ አይፀፀትም;;; ..

ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ (እብራይስጥ 7) በመጀመሪያ ስለ መልከፀዲቅ፣ ቀጥሎም መልከፀዲቅ ምሳሌው ስለ ሆነው ስለ እየሱስ ክርቶስ ይናገራል;; እንዲህ ሲል--

..የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሄር ካህን የሆነው ይህ መልከፀዲቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አስራትን አካፈለው;; የስሙም ትርጉዋሜ በመጀመሪያ የፅድቅ ንጉሥ ነው;; ሁዋላ ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው;;›› (ስለ እየሱስ ክርስቶለ ማንነት ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ እያይዞ ሲናገር) አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት፣ ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል;;››





ስለ እየሱስ ክርቶስ ቅዱስ ጳውሎሰ ሲናገር ››አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም›› ያለውን ቆንጽሎ በማውጣት እያሌ መጽሃፍ ቅዱስን እናውቃለን የሚሉ ሰዎች ይህን አባባል ለኢየሩሳሌም ንጉሥ ለ መልከፀዲቅ በመስጠት ››መልከፀዲቅ አባትና እናት ስሌለውና ዘመኑ ጥንት፣ ትውልዱ ቁጥር፣ ህይወቱም ፍጻሜ ስሰሌለው መልከፀዲቅ ከአናትና አባት የተወለደ እጥንትና ሰጋ የነበረው ሰው አይደለም;; እሱ ራሱም ልጆች ሊወልድ አይችልም፤›› ይላሉ;; ነገር ግን ቅዱሰ ጳውሎስ ››አባትና እናት፣ የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት፣ ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በአገዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል;;›› የአለው ሰለ እየሱሰ ክርስቶስ እንጂ ስለ ሳሌም ንጉስ እነዳልሆነ አይገነዘቡም;; የእየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ንጉሥ መልከፀዲቅ የተባለው ትልቅ ሰው ግን የዛሬ 4000 ዐመት በክህነት እና ንጉሥነት ኖሮ ሞቶአል;; በመሞቱም ህይወቱም፣ መንግሥቱም ከህነቱም አልፈዋል;; ሞቶአል የምለውም ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ነበር፣ ስለሚል ነው;; የት ነው ይህን የሚለው? በዛው በእብራውያን ምእራፍ 7 ቁጥር 4. እንዲህ ይላል--

››የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አሰራት የሰጠው **ይህ ሰው** (ይህ ሰው የሚለውን በአፅንኦት እንየው፤) አንዴት ትልቅ አንደነበረ እስኪ ተመልከቱ;;›› አዎን ሰው ሰለነበር ሞቶአል;; መንገሥትና ከህነቱም አልፈዋል;; እሱ ምሳሌ የሆነለት የአየሱሰ ክርቶስ መንግሥት፣ ህይወት እና ከህነት ግን ዘላለማዊ ናቸው;; እሱ የማይሞት ዘላለማዊ ነወና;; አባታችንን፣ ማለትም የኢትዮጵን አባት መልከፀዲቅን፣ ቅዱሰ ጳውሎስ ››ይህ ሰው ትልቅ እንደነበረ እሰቲ ተመልከቱ፤›› ባለው ደስ እያለኝ ከእሱ አባባል እስማማለሁ; አዎን በአባታችን ትልቅነት ሁላችንም የኢትዮጵ ልጆች ኢትየጵያውያን ልንደሰት እና ልንኮራ ይገባል;; ቅዱለ ጳውሎስ፣ አባታችንን መልከፀዲቅን ትልቅ ሰው ካለባቸው ምክንያቶች ዋነኛው የእየሱስ ክርቶስ ስርዐተ-ክህነት እነስተኛው የዕብራዊው የሌዊ ስርዐተ-ክህነት ሳይሆን የአባታችን የኢትዮጵ አባት፣ ስለዚህም የኛ አባት የሆነው ትልቁ የመልከፀዲቅ ስርዐተ-ክህነት መሆኑ ነው;; እሱ አባታችን ስለሆነ ከእብራውያኑ ከነ ሙሴና እና ከነ ቅዱስ ጳውሎስ የበለጠ ስለ እሱ ማንነት መረጃ አለን;; በመጀመሪያ ነገር፣ ከቅዱስ ጳውሎስ አስቀድሞ ስለ መልከፀዲቅ በጥቂቱም ቢሆን የጻፈው ሙሴ ነው;; ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ሙሴ በጻፈው ላይ ተመርኩዞ ከተበ;; ሙሴ ራሱ መረጃውን ያገኘው ከኛው ከኢትዮጵያውያን ነው;;

እንዴት ቢባል፣ እንደ መልከፀዲቅ ካህን ከነበረው ከመልከፀዲቅ ዝርያ፣ ከኢትዮጵዊው አማቱ ከየቶርአብ ጋር 40 ዐመት ሙሉ በኢትዮጵያ ሲኖር እኛ የአባታችንን የመልከፀዲቅን ትውልድ ታሪክ በዝርዝር የዘገበንበትን መጽሃፈ ዣንሸዋ ን አግኝቶ ስለ አነበበ;; ሙሴ

አስቀድሞ የኛን መጽሃፍ ማንበቡን ራሱ አምኖአል፣ መሰከሮአልም። ይህንንም የመሰከረው በ መጽሃፈ ሆልቆ (21፥ 14) ነው። ይህን እውነት አንባቢው በቀና ልቦና ሊመረምረው ይችላል።


በዛው በ እብራውያን 7 እና 8 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ፣ በእግዚአብንር ቀኝ የተቀመጠ የዘላለም ሊቀ-ካህን አለን የሚለውም ፈጣሪን እየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንጂ ሰው የሆነውን አባታችንን መልከፀዲቅን ሊሆን አይችልም። ለአብርሃም ህብስትና ወይንጠጅ ያበረከተለት (ከማንም አስቀድሞ ያቆረበው ማለት ነው፣) ሊቀ-ካህኑ አባታችን መልከፀዲቅ እንጂ እየሱስ ክርስቶስ ራሱ ስጋ ለብሶ፣ ገዝፎና ታይቶ አልነበረም። እየሱስ ክርስቶስ ከ ቅድስት ማርያም ስጋ ነስቶ የዛሬ 2000 ዐመት ከመወለዱ በፊት ስጋ ሆኖ ገዝፎ ለሰው ተከስቶ ነበር፣ ማለት የስህተት ስህተት ነው። ከሴት ሳይወለድ ስጋ ለመሆን ቢፈቀድ ኖሮ ለምን ከቅድስት ማሪያም ተወልዶ የበውን ልጅ ከሃጥያቱ ለማዳን አቀደ?

በእርግጥ መልከፀዲቅ አባታችን ስጋ ለባሽ ሰው ነበር። ሰው ስለነበረ ነው ከእናትና አባት የተወለደውና ራሱም ልጆች የወለደው። ከመጽሃፍ ቅዱስ በፊት በተጻፈው፣ ሙሴ እኛ ዘንድ ሳለ ባነበበው ዣንሸዋ በተባለው መጽሃፋችን ውስጥ የአባታችን ትውልድና ልጆች የዘር ሃረግ ተመዝግቦአል። በዚህ መጽሃፋችን ውስጥም መልከፀዲቅ ከናምሩድ፣ ማለትም የባቢሎንን ግንብ ከገነባው ታላቅ ንጉሥ ዘር ይጠቅሳል። እንዲህም ይላል -- »ናምሩድ አዳማን ወለደ፣ አዳማ ራፌልብን፣ ራፌልብ ቄናን፣ ቄና ደግሞ ኄራን። ኄራ በክህነት ስሙ መልከፀዲቅ የተባለው ነው። ኄራ (መልከፀዲቅ) በበኩሉ እናታችንን ሳሌምን (የነገሥባትን ከተማ በእሰዋ ስም ነው ሳሌም ወይም ኢየሩሳሌም ያለው፣) አግብቶ ከእሰዋ ዐራት ሴቶችና ሶስት ወንደች ልጆች ወልዶአል። የወንዶቹ ስሞች ኢትኤል (አባይን ተከትሎ ሄዶ ጣና ላይ ሰፍሮ በሁዋላ ›ኢትዮጵ‹ የተባለው አባታችን) ሃሙኤል (ሃሙራቢ ተብሎ ወደ ባቢሎን ተጉዞ የሃሙራቢን ህጎች Hamurabi's Code of Lawን የሰጠው) እና አቡመሊክን (የፍልስጥኤማውያን ንጉሥ የሆነውን) ወልዶአል። ከእሱ አብራክ እኛን ኢትዮጵያውያንን ያስገኘን እግዚአብሄር ይከበር ይመስገን። ታዲያ ይሄ ሁሉ ለምን መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ አልሰፈረም? ሙሴ መጽሃፍ ቅዱስን ከመጻፉ ወይም ከማጻፉ በፊት ይህን ታሪካችንን ጠንቅቆ ያውቃል። አንቦታልና። ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ለምን በኦሪት ዘ ፍጥረት ውስጥ እንዳላካተተው ትክክለኛውን መልስ ሊሰጠን የሚችለው ነቢዩ ሙሴ ብቻ ነው። እሱ ስላልከተበው ግን የኛ እውነተኛ ታሪክ የለም ማለት አይደለም። መጽሃፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት የእኛን ጉዳይ እኛው ከትበነዋል። ስለዚህ፣ እሱ ስላልከተበው ብዙ አይጨንቀንም። ይህ ለሁሉም ሰው ግልጽ ሊሆን ይገባል።





መጽሀፍ ቅዱስን *መሜፈ ቂልቂሉ* ብለው በገዕዝ ፊደላት ተርጉመው፣ የኦሮሞው ተውላጅ ፓስተር ኦናሲሞስ ነሲብ የዛሬ 120 ዓመት በአጼ ምኒልክ ዘመን ያሳተሙት የኦሮምኛ መጽሀፍ ቅዱስ፣ የገዕዝ-ኢትዮጵያ ፊደላት ካላቲኖቹ በተሸለ ኦሮምኛን ለማስተናገድ እንደሚችሉ አረጋግጠዋል፡፡ የዛሬ 120 ዓመት ይህን ማድረግ ከተቻለ፣ ዛሬ የግዕዝ ፊደላት የኦሮምኛን እና የሌሎቹንም የኢትዮጲያ ቋንቋዎች እንዲያስተናግዱ ተመቻችተው ስለተቀረጹ በኦሮሞዎች በኩል በጎ ፍቃደኝነት ከአለ፣ አሁንማ በጣም ይቻላል፡፡ ከ *መሜፈ ቂልቂሉ* ርዕስ ገጽ ከ እዚህ በታች ተቀምጦአል፡፡



# መጫፈ ፡ ቊልቊሉ ።

እንስ ፡


መጫፊት ፡ ከኩ ፡ ሞፈቲፈ ፡ ከኩ ፡ ሃራ ።

አፋን ፡ ኦሮሞት ።


ሂኬ ፡

ኦኒሲሞስ ፡ ነሲብ ፡

ነሞ ፡ ብዩ ፡ ኦሮሞ ።




የራስ አሉላ ደብዳቤ በአማርኛ



FACSIMILE LETTER FROM RAS ALULA    *To face page 66.*

ከአፍሪካ የግራ ብብት ስር እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ ያለው ውቂያኖስ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ

ዛሬ የህንድ ውቅያኖስ የሚባለውም ድሮ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል ነበር። ምክንያቱም ደቡብ ህንድ የኛ ስለነበረች።





ከሁለቱ መቶ ዓመታት በፊተ ላአላይ እና ታህታይ ኢትዮጵያ ተሰኝቶ መላው አፍሪካ ኢትዮጵያ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ



ከአፍሪካ የግራ ብብት ስር እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ ያለው ውቀያኖስ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ

ዛሬ የህንድ ውቅያኖስ የሚባለውም ድሮ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ይባል ነበር፡፡ ምክንታቱም ደቡብ ህንድ የኛ ስለነበረች፡፡




ከሁለተ መቶ ዓመታት በፊተ ላአላይ እና ታህታይ ኢትዮጵያ ተሰኝቶ መላው አፍሪካ ኢትዮጵያ ይባል እንደነበር የሚመሰክር ካርታ





ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ

ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ፣ /ፒ.ኤች.ዲ./ ገጣሚ፣ ጸሐፌ-ተውኔት እና ከ60 በላይ መጽሐፎችንና መጣጥፎችን በአማርኛ፣ በጀርመንኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች አሳትሞ ለንባብ ያበቃ ምሁር ነው።
በጀርመን እና በአሜሪካ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ አስተምሯል።

*** *** *** ***

ኦሮሞዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማለትም የዛሬ 500 ዓመት አካባቢ ከእስያ ተነስተው በማደጋስካር አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የውጪ ወራሪዎች ተደርገው አጉል ስም ይሰጣቸዋል። ኦሮሞው መጤ ነው ወይንስ ሃገር-በቀል?

አማራውን እወክላለሁ ብሎ ያወጀ ንጉሠ-ነገሥትስ ይኖር ይሆን?

አማሮች፥ ንጉሠነገሥታት እና ንግሥተነገሥታት ሆነው ላለፉት 3000 ዓመታት እንደገዙት እንደሰለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት ተቆጥረዋል። አማሮች ይህን ሁሉ ነበሩን?

ለመሆኑ በአለፉት 700 ዐመታት ኢትዮጵያን የገዛ ኦሮሞው ነው ወይንስ አማራው?

እንዴው ለነገሩ በኢትዮጵያ ሥርወ-መንግሥታት ውስጥ የአማሮች ተሳትፎ ምን ያህል እና እስከ ምን ድረስስ ነበር?

እስከነአካቴው አማራ የሚባል ህዝብ አለ ወይስ የለም?

ንግሥተ-ሳባስ ተረት ነች ወይንስ እውን?

ለኦሮሞዎች የሚበጀው በላቲን ወይንስ በኢትዮጵያ ፊደላት መጻፍ? እነዚህን ሁሉ ዐቢይ ጉዳይዎች መመርመር የዚህ መፅሃፍ ዋና ዓላማ ነው።

ዋጋ $ 25

PRINTED@FASTIMAGING BERKELEY,CA